አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በባህር ዳር ከተማ የታዋቂ አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ

በ
ሐረገወይን ሽዋረጋ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሰኔ 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማረኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በባህር ዳር ከተማ የታዋቂ አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ

ሐረገወይን ሽዋረጋ GSR /6062/03

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2004 ዓ.ም

# በባህር ዳር ከተማ የታዋቂ አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማረኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ

ሐረገወይን ሽዋረጋ GSR /6062/03

አማካሪ ሰላማዊት መካ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማረኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በባህር ዳር ከተማ የታዋቂ አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ

በ

ሐረገወይን ሸዋረጋ GSR /6062/03

ሰኔ 2004 ዓ.ም

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ስም ሰላማዊት [illegible] ፊርማ ----------

ፈታኝ ስም [illegible] ፊርማ ----------

ፈታኝ ስም ቴዎድሮስ ገብሬ ፊርማ ----------

ማውጫ

ገፅ

ምስጋና.......................................................................................i
አጠቃሎ.......................................................................................ii
ምእራፍ አንድ.......................................................................................1
መግቢያ.......................................................................................1
1.1.የጥናቱ ዳራ.......................................................................................3
1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት.......................................................................................4
1.3.የጥናቱ አላማ.......................................................................................4
1.4.የምርምር ጥያቄዎች.......................................................................................5
1.5.የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ.......................................................................................5
1.5.1.1. ቃለ መጠየቅ.......................................................................................6
1.5.1.2. ምልከታ.......................................................................................6
1.5.1.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ.......................................................................................7
1.6.የጥናቱ ወሰን.......................................................................................7
1.7.የጥናቱ ጠቀሜታ.......................................................................................8
1.8. የመረጃ አቀባዮች የናሙና አመራረጥ ዘዴ.......................................................................................8
1.9.ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንዉን.......................................................................................9
1.9.1.ቅድመ ዝግጅት.......................................................................................9
1.9.2.የመስክ ክንውን.......................................................................................9
1.10.በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦዎች.......................................................................................13
1.10.1.በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮች.......................................................................................13
1.10.2.የተወሰደ መፍትሄ.......................................................................................15
ምእራፍ ሁለት.......................................................................................16
ክለሳ ድርሳን.......................................................................................16
2.1.ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት.......................................................................................16
2.1.1.ግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ.......................................................................................16

2.1.2.የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት....................................................................24
2.1.2.1.የዶክትሬት ጥናቶች....................................................................24
2.1.2.2.የሁለተኛ ድግሪ ጥናቶች....................................................................24
2.1.2.3.የመጀመሪያ ድግሪ እና ሌሎች ጥናቶች....................................................................25
ምእራፍ ሶስት....................................................................27
3.1.የሶስቱ አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ እና የቃላዊ ግጥሞች ይዘት ትንተና...........27
3.2. የአዝማሪ ወርቁ ታዬ የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ትንተና....................29
3.3. የአዝማሪ ምግብ ግድየለው የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ትንተና............52
3.4. የአዝማሪ ማሾ የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ትንተና....................70
ምእራፍ አራት....................................................................84
ማጠቃለያ....................................................................84
ግኝት እና ይሁንታ....................................................................87
ግኝት....................................................................87
ይሁንታ....................................................................88
ዋቢ. ጽሑፎች....................................................................89
አባሪዎች....................................................................i
አባሪ አንድ፣የቃል ግጥሞች ስብስብ....................................................................i
አባሪ ሁለት፣የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር....................................................................xxxvi
አባሪ ሦስት፣የባህርዳር ካርታ ....................................................................xxxviii
አባሪ አራት፣የፎቶግራፎች ዝርዝር ....................................................................xxxix
አባሪ አምስት፣የባህል እና ቱሪዝም ጥናት ....................................................................XLvii
አባሪ ስድስት፣ሙዳዬ ቃላት....................................................................XLiX

ምስጋና

ከርዕስ መረጣ ጀምሮ የጥናት ስራው እስኪጠናቀቅ ድረስ ከጎኔ በመሆን በቅንነት ለረዳችኝ ውድ አማካሪዬ ረ.ፕሮፌሰር ሰላማዊት መካ ላደረገችልኝ ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የጥናቱን መረጃ በምሰበስብበትም ወቀትም ሆነ ትምህርቴን በማስተማር ከጎኔ ሆና ለዚህ ያበ ቃችኝን ውድ እናቴን እጅግ አመሰግናለሁ።እንዲሁም በገንዘብ፣በሀሳብ እና በማቴሪያል ከጎኔ ሆነው ለዚህ ላበቁኝ ወንድሞቼ ከነቤተሰቦቻችሁ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

በአባሪ ሁለት ላይ የሰፈራችሁ መረጃ አቀባዮቼ በሙሉ ለዚህ ጥናት ግብአት የሚያስፈልገ ኝን መረጃ በበጎ ፈቃደኝነት በመስጠት ስለተባበራችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

አቶ ስለሺ አባተ፣አቶ ዋልተንጉስ መኮንን፣ወ.ሮ አስቴር ሙሉ፣አቶ ለማ ንጋቱ፣መምህር ወንድወሰን አዳነ እና ዶክተር ሥርግው ገላው እንደሁለተኛ አማካሪ በመሆን ብዙ ነገር እረድታችሁኛል አመሰግናለሁ፡፡

ይህን ጥናት ለማሳካት እንድችል በገንዘብ ለረዳችሁኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አካላት ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ባህር ዳር ከተማ የምትኖሩት ዘመዶቼ አቶ ወርቁ፣ወ.ሮ ወርቅነሽ ዘለቀ፣ሳሙኤል ወርቁ፣ ወ፣ሮ ለተይ ከፈለ፣አቶ ዳንኤል ከፈላ እና እትዬ ምንትዋብ መስፍን በቆይታዬ ወቅት ላደረ ጋችሁኝ መስተንግዶ እና አቀባበል ሁላችሁንም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በዚህ ጥናት ምክንያት ባጋጠመኝ ችግር ከጎኔ በመቆም ስትተባበሩኝ ለነበራችሁ ኮሚሽነር ሙልጌታ፣ኮማንደር አሰፋ፣መርማሪ አማረ እና የባህር ዳር ከተማ የፖሊስ ኮሚሽነር፣የባህር ዳር ክልል ባህል እና ቱሪዝም መስሪያ ቤት፣ክልል መስሪያ ቤት፣የሴቶች ጉዳይ መስሪያ ቤት ኃላፊዎችና ሰራተኞች እንዲሁም ለአቶ ክንዴ እና መሪ ጌታ ፍሰሐ ላደረጋችሁልኝ መልካም አቀባበል እና ቅን ትብብር ከልብ አመሰግናለሁ።

በታሰርኩ ወቅት ስልክ በመደወል ስለእኔ በመታገል ሲከራከሩ፣ሲያፅናኑኝ ለነበሩ ለክፍለ ትምህርቱ ሀላፊ ለአቶ አብርሀም አለሙ እና ለአማካሪዬ ሰላማዊት መካ ምስጋናዬ የላቀ ነው።እንዲሁም ሲያፅናኑኝ ለነበሩ የክፍል ጓደኞቼ ዘላለም፣ወንድወሰን አንዱአለም፣ቀለም ወርቅ ተክሌ እና ከሁሉ በላይ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

አጠቃሎ

ይህ ጥናት በባህር ዳር ከተማ ታዋቂ አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥም ክዋኔ ላይ ያተኮረ ነው።በጥናቱ ቅኝት ቀደም ሲል በአዝማሪ ላይ የተጠኑ የመመረቂያ ጽሑፎች ተዳሰዋል።ባህላዊ ሙዚቃ በዋነኛነት የሚገኘው በአዝማሪዎች ዘንድ ነዉ።እናም ይህ ባህላዊ ሙዚቃ በአሁኑ ሰአት ወጥነቱን እንደያዘ አለወይ የሚለው ጥያቄ ያጭርብኝ ስለነበርና በባህር ዳር ከተማ አዝማሪዎች ላይ የተጠና ጥናት አለመኖሩ እንዳጠና ምክንያት ሆኖኛል።የጥናቱ ዋና አላማ የአዝማሪ ባህላዊ የሙዚቃ ክዋኔ በባህር ዳር ከተማ አዝማሪዎች ምን እንደሚመስል ማሳየት ሲሆን ይህን ባህላዊ የሙዚቃ ክዋኔ በባለታሪኮቹ ተረኮች መግለፅ፣ሙያው ለባህል ያለውን አስተዋፅኦ ማመላከት..ወዘተ የሚሉ ዝርዝር አላማዎች አሉት።ጥናቱ አዝማሪነት ለማህበረሰቡ ምንድን ነው?በማህበረሰቡ የፎክሎር ዘውጎች እንዴት ይገለጻል?የሚሉ የምርምር ጥያቄዎችን ይመልሳል።የባህሉን ለውጥ በማንፀር ለማጥናትም ይጠቅማል።ጥናቱን ለመቀንበብ ተረካዊ ንድፈ ሀሳብን የተጠ ቀምኩ ሲሆን መረጃዉን ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅ እና ተሳታፊ ምልከታ ዘዴን ተጠቅሜአ ለሁ።በዚህም መሰረት በቪዲዮ፣በፎቶ ግራፍ፣ በቴፕ እና በመቅረፀ ድምፅ ለጥናቱ የሚሆን ግብአት ተሰብስቧል።የጥናቱ ግኝትም በአሁን ሰአት በባህር ዳር ከተማ የሚገኙ አዝመሪዎች በማህረሰቡና በሌሎች ተቋማት ዘንድ ተቀባይነታቸው እየጨመረ መምጣቱን ያሳያል።

በመሆኑም አዝማሪዎቹ በፊት ሳይጋበዙ የዝግጅት ቦታዎችን ፈልገው በመሄድ ይሰሩ ነበር።በአሁን ሰአት ግን ዝፈኑልኝ ተብለው እና በርከት ያለ ክፍያ ተከፍሎአቸው በባህል ምሽት ቤት እና በሰርግ ላይ ይሰራሉ።በፈቃዳቸውም ያለክፍያ በሀይማኖታዊ ክብረ በአላት ላይ ይከውናሉ።በተጨማሪም በመንግስታት አቀባበል ስርአት ላይ ይሳተፋሉ። ነገር ግን በእነዚህ አዝማሪዎች በመሸምደድ፣በመሻሻል እና በአዲስ ፈጠራ የሚደረሱና የሚተላለፉ ቃል ግጥሞች በታዳሚው ፍላጎት ላይ በመመስረታቸው እና የቋንቋ መረጣ አነስተኛ መሆኑ ቃል ግጥሞቹ ስነ ውበታቸውን እምቅነታቸውን እና ቅኔያዊነታቸውን እንዲያጡ ሆነዋል።እንዲሁም በቃል ግጥሞቹ ውስጥ በሚገቡ ባእድ ቃላት የተነሳ ጉራማይሌነት ይታይባቸዋል።የቃል ግጥሞቹ ይዘት በፍቅር፣በፉከራ፣በምስጋና እና በምክር..ወዘተ ላይ ያተኮረ ሲሆን ከዚህ ሙያ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ የባህል ምሽት ቤቶች ባህላዊ ያልሆኑ ቁሶችን ማካተታቸው ባህልን በማስተዋወቅ ላይ የሚያሳድረዉ አሉታዊ ተፅእኖ ቀላል አለመሆኑን በመጥቀስ ጉዳዩ በሌላ ጥናት በስፋት ሊጠና እንደሚችል በመጠቆም አልፋለሁ።

## ምዕራፍ አንድ

### መግቢያ

አዝማሪነት የማህበረሰቡን ባህላዊ የሙዚቃ ጥበብ የሚያሳይ ሙያ ነው፡፡ነገር ግን ይህ የአዝ ማሪነት ሙያ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ተቀባይነት ዝቅተኛ መሆኑን የሚያስረዱ የዲፕሎማ የመጀመሪያ፣የሁለተኛ እና የዶክትሬት ድግሪ ጥናቶች ለዚህ ጥናት ተዛማጅ ቅኝት በማደርግ በት ወቅት ለመመልከት ችያለሁ።ይህን ተቀባይነትን የሚያሳጣ ሁኔታ ሙያው በአሁኑ ሰአት በባህል እና ቱሪዝም በመታቀፉና በአዝማሪዎቹ ያላሳነሰ ጥረት እየተለወጠ በመሄድ ላይ ይገኛል።ስለዚህ ጉዳይም ቃለ መጠይቅ ያደረኩላቸው አዝማሪዎች እና በባህልና ቱሪዝም የተጠና አንድ ጥናት ያመላክታል።"አዝማሪነት በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና የመገናኛ ዘርፍ እየሆነ የመጣ ሲሆን...።"በማለት ጥናቱ ያስረዳል።(34፣2004)እንዲሁም ስለዚሁ ጉዳይ የአማራ ክልል ባህል እና ቱሪዝም የሙዚቃ ባለ ሙያ የሆነው አቶ አበባው ሲያስረዳ"የሙያው ዘርፍ በራሳቸው ጥረት፣በሚዲያ ዘንድ በተሰጣቸው ጊዜ አማ ካኝነት ሙያው በበለጠ እያደገ እና እየታወቀ መጥቷል።ከመታወቅም ባሻገር የዚሁ ሙያ ማሰልጠኛ ለመክፈት ቦታ በመጠየቃቸው ይህንንም ለማድረግ በጥረት ላይ እንደ ሚገኝ ሁኔታውን አስረድቶኛል"።([1]ቃለ፡8፡2004)

ለጥናቱ ግብአትነት ከተሰበሰቡት ቃለ መጠይቆች እንደሚያመላክቱት በባህር ዳር ከተማ ውስጥ ሙያው እንዲያድግ ካደረጉ ሰዎች መካከል ለዚህ ጥናት የተመረጡ አዝማሪዎች እንደሚገኙበት ለመረዳት ችያለሁ።ይህንን ሁኔታ የባህል ምሽት ሰራተኛ የሆነው አቶ ባይለየኝ ሲያስረዳ "በእነሱ አማካኝነት ነው በባህር ዳር የባህል ምሽት ቤት እየታወቀ የሄደው።ይህም ክብራቸው ከፍ እንዲል እና በፊት ሳይጋበዝ ሄዶ የሚሰራው አዝማሪ አሁን እነሱ ስላሻሻሉት ተጋብዘው እና በረከት ያለ ክፍያ ተከፍሎአቸው ይሰራሉ በማለት ይናገራል"።(ቃለ፡7፡2004)ስለዚህ ከላይ በተነሳው ሀሳብ ውስጥ የአዝማሪነት ሙያ እየተራመደበት ያለውን የለውጥ ጎዳናን ለማየት ያስችላል።ይህም ጥናት ይህንን መሰረት በማድረግ በባህር ዳር ከተማ የአዝማሪነት ሙያ ገፅታን ለጥናቱ በተመረጡ አዝማሪዎች አማካኝነት ለማሳየት ላይ ይሞክራል።

ይህ ጥናት በአምስት ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን ምዕራፍ አንድ የጥናቱን ዳራ፣የጥናቱን አነ ሳሽ ምክንያት፣የጥናቱን አላማ፣የጥናቱ አስፈላጊነት፣የጥናቱን ወሰን እና ያጋጠሙ ችግሮችን

---

[1] ቃለ እያልኩ በአጭሩ የተጠቀምኩት ቃል ቃለ መጠይቅ ለማለት መሆኑን ለመግለፅ እወዳለሁ።

እንዲይዝ በማድረግ ይዋቀራል።ምዕራፍ ሁለት ደግሞ ክለሳ ድርሳናትን የሚይዝ ሲሆን በምዕራፍ ሶስት ውስጥ የምግብ ግድየለው፣የማሾ ፋንታዬ እና የወርቁ ታዬን የህይወት ታሪክ እና ቃል ግጥሞቹን በመባያቸው በመከፋፈል ትንታኔ ይሰጣል።ምዕራፍ አራት ማጠቃለያውን ይይዛል።በምዕራፍ አምስት ደግሞ ግኝት እና የመፍትሄ ሀሳቦች ይነሳሉ።በመጨረሻም የዋቢ መፃሕፍት ሰፍረው የተለያዩ አባሪዎች አንድ ሁለት በማለት ይቀመጣሉ።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

አዝማሪነትን ማህበረሰቡ ከዝማሪዎች ክዋኔ በመነሳት ባህላዊ ዘፋኝ፣አወዳሽ፣ባህላዊ ተጫ ዋች... ወዘተ በማለት ከባህላዊ የሙዚቃ ጥበብ ውስጥ ይፈርጀዋል።ደስታ ተክለ ወልድም ስለ አዝማሪ ምንነት ሲገልፅ(1962፡496)አዝማሪ የሚለው ቃል ከሙያው ባህሪ እና ማህበ ረሰቡ ለሙያው ከሚሰጠው ግምት በመነሳት ያዘመረ፡የሚያዘምር፡ዘፋኝ፡ባለ ማሲንቆ.... ወዘተ በማለት ይገልፀዋል።ይህ ባህላዊ የሙዚቃ ጥበብ ባህላዊ ሙዚቃን፡ባህላዊ ቁስ፡ሀይ ማኖታዊ ክብረ በአላትን፡የሰርግ አውዶችን...ወዘተ የተለያዩ አውዶችን አቅፎ በመያዙ የፎክሎር ዘውግ በሆነው ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ውስጥ ይመደባል።ይህ ሙያ መቼ እን ደተጀመረ ለመናገር አስቸጋሪ ነገር ነው።ነገር ግን ይህ አለማዊ ባህላዊ የሙዚቃ ጥበብ በመንፈሳዊው ውስጥ ሳይፈጠር እንደማይቀር የሚ ሰነዘሩ መላምቶችን እናገኛለን።

አሸናፊ ስለዚህ ጉዳይ ሲያስረዳ"የአዝማሪነት ሙያ ወይም አለማዊ ሙዚቃ በመንፈሳ ዊው ውስጥ ሳይፈጠር አይቀርም በማለት ይናገራል"።(1976፣297፣1971፣55) ቀደም ሲል የተደረጉ ጥናቶችም እንደሚያመላክቱት አዝማሪነት ከቀደሞ ነገስታት ጋር አብሮ የነበ ረና እስከ አሁንም ድረስ የቀጠለ ሙያ ነው ይላሉ።ስለዚህም በእነርሱ አማካኝነት ባህላዊ ውን የሙዚቃ የታሪክ አመጣጥ፣ለውጥ እና እድገት ለማወቅ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን እንረ ዳለን።እንዲሁም ከሙዚቃው ባሻገር ባህላዊው የሙዚቃ መሳሪያ፣መጠጥ፣አልባሳት እና ምግቡ ባህላዊነቱ ተጠብቆ እንዲቆይ ትልቅ የሆነ ሚና ይጫወታል፤ለቱሪስት ባህሉን በማስ ተዋወቅም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ያበረክታል።

ነገር ግን ማህበረሰቡ ለአዝማሪዎቹ ያለው ክብር ዝቅተኛ በመሆኑ ከማደግ ይልቅ እየጠፉ መምጣታቸውን ከጥናቶቹ እንረዳለን፡፡እንዲሁም ቃላዊ ግጥም ከትዉልድ ወደ ትውልድ በእነዚህ አዝማሪያን አማካኝነት ሲተላለፍ ቆይቷል፡፡በዚህ አማካኝነትም የማህበረሰቡን ማን ነት ለመረዳት ስለሚያስችሉ ለአዝማሪዎች ተገቢውን ክብር ልንሰጣቸው እንደሚገባ ጥናቶቹ ያመላክታሉ፡፡በአሁን ሰአት እነዚህ አዝማሪዎች በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች እና ከተ ሞች ውስጥ ይገኛሉ።አዝማሪዎች በብዛት ከሚሰፍሩባቸው ከተሞች መካከል አንዷ የባህር ዳር ከተማ ናት።ባህር ዳር የአማራ ክልል ዋና ከተማ ስትሆን በዚች ከተማ ውስጥ ከሰባ እስከ ሰማኒያ የሚደርሱ አዝማሪዎች ይኖራሉ ተብሎ ይገመታል።እነዚህ አዝማሪዎች ህብረትን በመፍጠር እየጠፉ ያለውን የአዝማሪ ባህል ለመታደግ ማህበር አቋቁመዋል።ይህ

ማህበር ከወጣት እስከ አዛውንት የእድሜ ደረጃ ድረስ ያቀፈ ሲሆን ከአባላቱ መካከል የማህበሩ ሀያ ሶስቱ ሴቶች ቀሪዎቹ አስራ ስድስቱ ደግሞ ወንዶች ናቸው።ማህበረሰቡም በሰርጉም ሆነ በሌላ የደስታ ጊዜው አዝማሪዎቹን በመጋበዝ በአሉን ያደምቃል።

ስለዚህ ከዚህ በፊት በአዝማሪ ላይ ተመስርተው የተጠኑ ጥናቶች በባህር ዳር ከተማ አዝማሪዎች ላይ የተጠኑ ባለመሆናቸው፣የአዝማሪ ክወና አንድ አካል የሆነውን ሀይማኖታዊ ክዋኔውንም ሆነ ቃል ግጥሙን ባለመመልከታቸው እና የመንግስታትን የአቀባበል ስነስርአት ክዋኔን ባለማየታቸው ከእኔ ጥናት የሚለዩ ሆነዋል።እንዲሁም በአጠኑበት መቼት ውስጥ የነበረውን የሙያውን ለውጥ ባለመመልከታቸው እነዚህ ጉዳዮች በዚህ ጥናት በማካተት የሚተነተኑ ይሆናሉ።

## 1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ባህላዊ የሆነው የሙዚቃ ጥበብ የሚገኘው በአዝማሪያዎች ዘንድ መሆኑ ይታወቃል።እናም ይህ ባህላዊ ሙዚቃ እና አውዱ በአሁን ሰአት ሳይበረዝ ወጥነቱን እንደ ያዘ አለ ወይ የሚለው አዝማሪን ርእስ ጉዳያቸው አድርገው የተሰሩ ጥናቶችን ስመለከት ጥያቄ ያጭርብኝ ስለነበር ይህን ጥናት እንዳጠና አነሳስቶኛል።

እንዲሁም በባህር ዳር ከተማ አዝማሪዎች ላይ የተጠና ጥናት ባለመኖሩ ይህን ክፍተት ለመሙላት ጥናቱን እንዳጠና ምክንያት ሆኖኛል።

## 1.3.የጥናቱ ዋና አላማ

ስለዚህ የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአዝማሪ ባህላዊ ሙዚቃዊ ክዋኔ በባህር ዳር ከተማ አዝማሪዎች ዘንድ ምን እንደሚመስል ማመላከት ሲሆን በዚህ ዋና አላማ ስርም የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት።

- ይህን የአዝማሪ ባህላዊ የሙዚቃ ጥበብ በባለታሪኮቹ ተረኮች አማካኝነት ማሳየት።
- የተመረጡ የሶስት አዝማሪዎች ቃል ግጥሞች በመባያቸው ከፋፍሎ ይዘታዊ ትንታኔ በማድረግ ትኩረታቸውን ማመላከት።
- የሶስቱን አዝማሪዎች የባህል ምሽት ቤት እና የሰርግ ክዋኔን ማመላከት።እንዲሁም በሌሎች ጥናቶች ብዙም ትኩረት ያልተሰጠዉን የጥምቀት፣አመታዊ በአል፣የሰባሩ

የጊዮርጊስ ጥምቀት(ሀይማኖታዊ ክዋኔ) እና የመንግስታትን አቀባበል ስርአተ ክዋኔን ማሳየት።

- የአዝማሪዎቹን ባህላዊ የሙዚቃ ለመዳ፣ተስተላልፎ፣አደራረስ እና ክዋኔ መግለፅ።
- በሶስቱ አዝማሪዎች እና እነርሱ በሚከውኑበት አከባቢ የሚከወነው ይህ ባህላዊ ሙዚቃ አጠቃላይ ክዋኔ(ቃል ግጥሙ፣ቁሱ…ወዘተ)በመመርመር የሙዚቃዉን ባህላዊ ለውጥ ማመላከት።
- የአዝማሪ ሙያ ለባህል እድገት ያለውን አስተዋፅኦ በእነዚህ አዝማሪዎች አማካኝነት ማሳየት የሚሉ ናቸው።

## 1.4.የምርምር ጥያቄዎች

እነዚህ አላማዎችን ከግብ ለማድረስ ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሂደት ይመልሳል።

- አዝማሪነት ለማህበረሰቡ ምንድን ነው?
- አዝማሪነት በማህበረሰቡ የፎክሎር ዘውጎች እንዴት ይገለጻል?
- በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ቁሳዊ፣መንፈሳዊ፣ማህበራዊ እና ባህላዊ ተቋማት በአዝማሪዎች እንዴት ይታያሉ?ይገለጻሉ?
- የአዝማሪ ሙያ ለባህል እድገት ያለው አስተዋፅኦ ምንድን ነው?

## 1.5.የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

አንድ የፎክሎር አጥኚ መስክ ወጥቶ መረጃውን ከመሰብሰቡ በፊት ቅድመ መስክ ዝግጅት ያስፈልገዋል።ይህ ቅድመ መስክ ዝግጅትም ጥናቱ ስለሚደረግበት አካባቢና ስለጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ አስቀድሞ ማወቅ ነው።እኔም ይህን እንዲሆን ስል ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት በተለያዩ ቤተመፃህፍት ውስጥ ጥናቱ ስለሚደረግበት የባህር ዳር ከተማና ስለአዝማሪዎች ለማወቅ የሚያግዙኝን ፅሁፎች አንብቤያለሁ አሰሳም አድርጌባቸዋለሁ።እንዲሁም ስለጥናቴ ርዕስ በተለያየ ደረጃ እውቀት ያላቸውን ሰዎች አነጋግሬ ቅድመ መስክ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ።ከዚያ በኋላ ወደ መስክ በመሄድ ጥሬ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ።በዚህ መሰረት ለጥናቴ የሚሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይና ካልዓይ ምንጮች የተሰበሰቡ ናቸው።

በካልዓይ ምንጮች ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የታተሙና ያልታተሙ ፅሁፎች እና ጥናቶች ከቤተመፃህፍት እንዲሁም ከኢንተርኔት የተሰበሰቡ ሲሆን፣በቀዳማይ የመረጃ ምን

ሙች ደግሞ ለዚህ ጥናት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች ለመሰብሰብ በዋናነት ቃለመጠይቅ
እና ምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ጥናቱ ተጠቅሟል።

### 1.5.1.. ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ አንድ መረጃ ሰብሳቢ ለመረጃ አቀባዩ ጥያቄዎችን እያቀረበ መልስ የሚቀበልበ
በት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው።በዚህ ጥናትም ቃለ መጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ
አገልግሏል።በዚህ በኩል በባህር ዳር ከተማ ታዋቂ የሆኑ ሶስት አዝማሪዎችን በሀላፊያቸው
በኩል ቀጠሮ በመያዝ እና በማግኘት መደበኛ ቃለ መጠይቅ አድርጌአለሁ።እንዲሁም ከዚህ
ሙያ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የማህበሩ ሀላፊ፣ከባህል እና ቱሪዝም የሙዚቃ ባለ ሙያ እና
ከዶ.ር ስርግው ገላው ጋር ቀጠሮ በመያዝ መደበኛ ቃለ መጠይቅ አድርጌአለሁ።

በተጨማሪም ለዚህ ጥናት የተመረጡ አዝማሪዎችን ታዋቂነት ለማረጋገጥ ከተለያዩ ሰዎች
ጋር መደበኛ እና ኢ መደበኛ ቃለ መጠየቅ አድርጌአለሁ።በዚህም ሰባት የቴፕ ካሴት እና
ሰባት ሲዲዎች ሰብስቤአለሁ።በዚህም ቃለ መጠይቅ አማካኝነት ቃል ግጥሞችን ለመሰብሰብ
ተችሏል።ከአራት ቁልፍ መረጃ አቀባዮች እና ከዘጠኝ ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች መረጃ
ለመሰብሰብ ተሞክሯል።

### 1.5.2. ምልከታ

የዚህን ጥናት መረጃ ከግብ ለማድረስ ከቃለ መጠየቅ ባሻገር የምልከታ ዘዴን ተጠቅሜአ
ለሁ።የአዝማሪዎቹን ክዋኔ በቃለ መጠየቅ ማግኘት ስለማልችል ተሳታፊ ምልከታ መረጃን
የመሰብሰቢያ ዘዴን መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።በዚህም ዘዴ አማካኝነት በምሽት
ቤት፣በሰርግ፣በጥምቀት አመታዊ በአል ላይ በመገኘት እና አዉዱን በመመልከት በማስታ
ወሻ፣በቴፕ፣በመቅረፀ ድምፅ፣በፎቶ ግራፍ እና በቪዲዮ ካሜራ መረጃዉን ለመቅረፅ ተች
ሏል።ሆኖም የዋናው ጥምቀት፣የሚካኤል ጥምቀት እና የሰባሩ ጊዮርጊስ ጥምቀት በተፈጠ
ረው ችግር ምክንያት የተደመሰሰ ቢሆንም የባለ እግዚአብሄር አመታዊ ባአል ላይ በመገኘት
በቪዲዮ በመቅረፅ ማሳያ የሚሆን መረጃን ሰብስቤአለሁ።

በመስክ ላይ መረጃ ለመሰብሰብ ሦስት አይነት መቼቶች እንጠቀማለን።እነርሱም ተፈጥሯዊ፣
ቅንብር ተፈጥሯዊ እና አርቴፊሻል መቼቶች በመባል ይታወቃሉ።በመሆኑም የህይወት ታሪ
ኩን ለመሰብሰብ አርቴፊሻል መቼትን በመጠቀም የሰበሰብኩ ሲሆን ሌላውን ግን በቦታው

ተገኝቼ በተፈጥሮ መቼት ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡በዚህ ሁኔታ መረጃውን ሰብስቤ ካጠናቀቅኩ በኋላ ቀጣዩ ተግባሬ መረጃ ትንተና ነበር፡፡

### 1.5.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ

መረጃዎች ከቀዳማይና ካእላይ የመረጃ ምንጮች ከተሰበሰቡ በኋላ ቀጣዩ ተግባር የመረጃ ትንተና ነው፡፡በመሰረቱ ባህላዊ ሙዚቃን አስመልክቶ መረጃዎችን ለመተንተን የሚጠቀሙ የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች አሉ፡፡ይሁንና ተረካዊ ንድፈ ሀሳብ የንግግር አይነትን እና የተለያየ ሁነትን፣ገጠመኞችን እና የሰው ልጆችን ድርጊትን በአንድነት ማሳያ መንገድ ስለሆነ ከበርካታ ንድፈ ሀሳቦች ውስጥ በተሻለ የመረጃውን አውዳዊ ክወና ስለሚያሳይልኝ ተጠቅሜዋለሁ።

እንዲሁም ይህ ቲወሪ መረጃን ለመሰብሰብ አይነታዊ የምርምር ዘዴን በማዛመድ ይጠቀማማል።አይነታዊ ምርምር በዋናነት መረጃን ለመሰብሰብ ከሚጠቀምባቸዉ ዘዴዎች መካከል ቃለ መጠይቅ፣ተሳታፊ ምልከታ፣ተሳታፊ ያልሆነ ምልከታ…ወዘተ ይካተታሉ።ስለዚህ መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ ላይ እንደጠቀስኩት የህይወት ታሪክን እና ክዋኔን ለመሰብሰብ አንደኛው መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ የሆነዉን ቃለ መጠይቅ ተጠቅሜአለሁ፡፡እንዲሁም ክዋኔዉ ሲከወን በቦታው በመገኘት እና አውዱን በመመልከት ተሳታፊ የምልከታ ዘዴን ተጠቅሜአለሁ፡፡

በዚህ መሰረት የመረጃ አቀባዮቹን የህይወት ታሪክ መሰረት በማድረግ የአዝማሪ ህይወትን ለማጥናት በቃለመጠይቅና በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በሚገባ አጠናቅቄአለሁ።የተሰበሰቡ ቃል ግጥሞቹንም በይዘታቸው በመከፋፈል ተረካዊ ቲወሪን በመጠቀም ትንተና ሰጥቻለሁ።

## 1.6.የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ወሰንም በባህር ዳር ከተማ ታዋቂ የሆኑትን የምግብ ግድየለው፣የማሾ ፋንታዬን እና የወርቁ ታዬን የህይወት ታሪክ፣ቃላ ግጥሞች፣ክዋኔያቸውን እና አውዱን ማመላከት ነው።እናም በነዚህ አዝማሪያን አማካኝነት የባህር ዳር ከተማ የአዝማሪ ባህላዊ የሙዚቃ ጥበብ ምን እንደሚመስል ማሳየት ላይ የተወሰነ ነው።

## 1.7.የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት መጠናቱ የተለያየ ጠቀሜታ ይኖረዋል።እነርሱም፦

- የባህሉን ለውጥ በማነፃፀር ለማጥናት ይጠቅማል።
- በቃል የምናገኘው ቃል ግጥም ከሰው ወደ ሰው ከዘመን ወደ ዘመን በሚሸጋገርበት ወቅት የመሸራረፍ ሁኔታ ያጋጥመዋል።ስለዚህ ቃል ግጥሞቹን ቀርሶ በማስቀመጥ በተወሰነ ደረጃ ወጥነቱን ለመጠበቅ ይረዳል።
- እንዲሁም በቃል ግጥሙ አማካኝነት ማህበረሰቡ ስለ ነገሮች ያለውን አመለካከት እና የማህበረሰቡን ማንነት...ወዘተ ለመመልከት እና ለመረዳት ያስችላል።
- በተጨማሪም በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ጥናት ለማካሄድ ለሚፈልጉ አጥኝዎ ች በመነሻነት ያገለግላል።

## 1.8. የመረጃ አቀባዮች የናሙና አመራረጥ ዘዴ

በባህር ዳር ከተማ ከእዝራ የአዝማሪያን ማህበር አባላት መካከል በፆታ፣በእድሜ፣በልምድ፣በችሎታ እና በማህበረሰቡ እንዲሁም በማህበሩ እውቅና ያላቸውን በማፈላለግ ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃ አቀባዮቹን ለመምረጥ ችያለሁ።እንዲሁም ከፆታ አንፃር ከቁልፍ መረጃ አቀ ባዮቹ መካከል ሁለቱ ሴቶች ሲሆኑ ሌሎቹ ወንዶች ናቸው።እነዚህ መረጃ አቀባዮች በተለያየ የዕድሜ ደረጃ የሚገኙ ሲሆን የትምህርት ደረጃቸውም የተማሩ እና ያልተማሩ በሚለው ውስጥ ይካተታሉ።በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው እውቅና እና ሙያዊ ደረጃ ስንመለከት የአዝ ማሪ ማህበር ሀላፊ፣ታዋቂ አዝማሪዎች፣የባህል እና ቱሪዝም የሙዚቃ ባለሙያ፣የቤት እመ ቤት፣አስተናጋጅ እና አስተማሪዎች ይገኙበታል።

ከእነዚህ የመረጃ አቀባዮች ውስጥ የአዝማሪ ማህበር ሀላፊ የሆነው እና ታዋቂ አዝማሪዎች ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ናቸው።ቁልፍ ያስኛቸው ምክንያትም ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ አስ ፈላጊ እና ብዙ መረጃዎችን በመስጠታቸው ነው።ሌሎቹ የመረጃ አቀባዮች ደግሞ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያለውን መረጃ በመስጠት የተባበሩኝ ናቸው።

በዚህ መንገድ ከተመረጡት ከሁሉም የመረጃ አቀባዮች በቃለ መጠይቅ፣በምልከታ፣በፎቶ ግራፍ፣በመቅረፀ ድምፅ፣በወክማን ቴፕ እና በቪዲዮ በመቅረፅ እንዲሁም ለመቀረፅ ፈቃደኛ

ያልሆኑትን ደግሞ በማስታወሻ ደብተር ሀሳባቸውን በመመዝገብ መረጃ ለመሰብሰብ ተች ሏል።

## 1.9.ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን

ማንኛውም የመስክ ስራ ወይም ክንውን በመጀመሪያ ቅድመ ዝግጅት ያስፈልገዋል።ስለዚህም ወደ ድህረ መስክ ከመሄዱ በፊት ቅድመ መስክ ዝግጅት ተደርጓል።

### 1.9.1.ቅድመ ዝግጅት

አንድ አጥኚ ከቀዳማይ ምንጮች ለጥናቱ መሰረት እና ገንቢ የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰ ሰብ ቅድመ መስክ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልገዋል።በመሆኑም ከመስክ ስራ በፊት ስለ አዝ ማሪ ምንነት፣ታሪካዊ አመጣጥ የሚያወሱ እና ከርእሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናቶች እንዲሁም ዳሰሳ፣መፅሀፎችን ከቤተመፃህፍት፣ከኢንተርኔት እና ከግለሰቦች እጅ በማሰባሰብ መረጃዎችን ለማግኘት ተሞክሯል።

### 1.9.2.የመስክ ክንውን

የመስክ ቅድመ ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ጥር 1 ቀን 2003 ዓ.ም ሰኞ ቀን የአማራ ክልል ዋና ከተማ ወደ ሆነችው ባህር ዳር ተጓዝኩ።ባህር ዳር ከአዲስ አበባ ከተማ በየብስ 565 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ናት።ማክሰኞ ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም ጠዋት ከ3 ሰአት በፊት አዲስ አበባ እያለሁ ቅድመ መረጃን ሲያቀብለኝ ለነበረው የማህበሩ ሀላፊ አቶ ትእዛዙ አስናቀው ዘንድ ደውዬ ቀጠሮ ያዝን።ከዚያ በኋላ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስነ ፅሁፍ እና ፎክሎር ክፍል የተፃፈልኝን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ ወደ ቀጠሮው ቦታ ሄድኩ።

በማግስቱ ጠዋት ረፅቡ ጥር 3 ቀን 2004 ዓ.ም ላይ በተባልኩት ሰአት በቦታው በመገኘት ከአዝማሪ ማሾ ፈንታዬ ጋር ለመገናኘት እና ለመተዋወቅ በቃሁ።በመቀጠልም የያዝኩትን ቡቴፕ እና መቅረፀ ድምፅ ትክክል መሆኑን ፈትሼ አንድ ካሴት የወሰደ ቃለ መጠይቅ በማ ድረግ በአርቴፊሻል መቼት የመጀመሪያ መረጃዬን ሰበሰብኩ።ጥር 4 ቀን 2004 ዓ. ም ጠዋት ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ከአዝማሪ ወርቁ ጋር ተገናኘን።ከሱም ጋር አንድ ካሴት የወሰደ የቃለ መጠይቅ ቀረፃ በማድረግ በአርቴፊሻል መቼት ሁለተኛ መረጃዬን ሰበሰብኩ።በዚያኑ እለት ከሰአት በኋላ ስምንት ሰአት ላይ ወደ አዝማሪ ምግብ ግድየለው ቤት በመሄድ አንድ ካሴት የወሰደ የቃለ መጠይቅ ቀረፃ በማድረግ በአርቴፊሻል መቼት ሶስተኛ መረጃዬን ሰበሰ

ብኩ፡፡በመቀጠልም አዝማሪዎቹ ሲከውኑ የቪዲዮ፣የቴፕ የፎቶግራፍ ቀረፃ ለመቅረፅ ከምሽቱ 2 ሰአት በፊት አንድ አስር ደቂቃ ቀድሜ በባላገሩ የባ ህል ምሽት ቤት ተገኘሁ።ትንሽ እንደ ቆዩ የመጀመሪያው ገቢ አዝማሪ መዝፈን ጀመረ።በዚህ ጊዜ ውስጥ ገብቼ በመቀመጥ ሁኔታ ውን በአይኔ መቃኘት ጀመርኩ።ዘፈኑ ሞቅ ሞቅ ሲል ወደ 2-30 ገደማ ሲሆን አቶ ትእዛዙ እና አዝማሪዋ ማሾ መጡ፡፡ከዚያም ማሾ ቀጣይ ተረኛ ስለነበረች መዝፈን ስትጀምር ቀድሜ ሁሉንም መቅረጫዬን አስተካክዬ ስለ ነበር በቴፕና በቪዲዮ መቅረፅ ጀመርኩ፡፡የተወሰነ ድባ ቡን በቪዲዮ ቀረፅኩ።

ነገር ግን የምሽት ቤቱ መብራት በጣም ፈዛዛ ስለሆነ ለመቅረፅም አስቸጋሪ ሆነብኝ።ስለዚህ ፓውዛ መብራት አብርቼ ትንሽ ቀርፅኩ።ነገር ግን ከውጭ የሚገባው ታዳሚ መብራቱን አይቶ አንገባም በማለቱ ባለቤቷ ስለ ከለከሉ በዚህ ሁኔታ ቀረፃው ተስተጓጎለ፡፡እኔ ግን እዚ ያው በመቆየት በቴፕ እየቀዳሁ ሁኔታውን እየተመለከትኩ ማሾ ከውና እስከምትጨስ እስከ ምሽቱ አምስት ሰአት ድረስ አብሬ አመሸሁ።በዚህ ሁኔታ በተፈጥሮ መቼት የተወስነ መረጃ ሰበሰብኩ፡፡ጥር 5 ቀን 2004 ዓ.ም ዳሞት የባህል ምሽት ቤት ተገኘሁ፡፡ተረኛው አዝማሪ ገብቶ ሁሉ ነገር ትንሽ ሞቅ እንዳለ አቶ ትእዛዙ እና አዝማሪ ወርቁ መጡ፡፡አዝማሪ ወርቁ ጀማሪውን አዝማሪ ተከትሎ መከወን ሊጀምር ሲል እኔ ቀድሜ ፓውዛው ከመብራቱ በፊት ያለውን ድባብ በደንብ ባይታይም መቅረፅ ጀመርኩ፡፡ከዚያም አዝማሪ ወርቁ መከወን እንደጀ መረ አዝማሪ ምግብ ግድየለው መጣች ከአዝማሪ ወርቁ ቀጥላ በመግባት ሁለቱ እየተቀባበሉ ሲከውኑ በቴፕ፣በቪዲዮ በመቅረፅ እና ፎቶ በማንሳት ማሾ ስትከውን የቀረፅኩትን ጨምሬ በተፈጥሮ መቼት ተጨማሪ መረጃዬን ሰበሰብኩ፡፡

ሌላው አዝማሪዎቹ የሚከውኑበት ቦታ ሰርግ ላይ ነበር፡፡አዝማሪ ወርቁ እና ማሾ ሰርግ ላይ ተጋብዘው የሚሰሩት ከባህር ዳር ከተማ ውጭ ስለ ነበር ሄጄ መመልከት አልቻልኩም(አዲስ አበባ እና መራዊ)፡፡ነገር ግን ጥር 6 ቀን 2004 ዓ.ም አዝማሪ ምግብ ግድ የለው እዚያው በባህር ዳር ከተማ የግንድ ሰፈር ትከውን ስለነበር ከሷ ጋር ተቀጣጥረን ወደ ሰርጉ አብሬ ሄድኩ፡፡ከቀኑ 6 ሰአት ከወንዱ ቤት ተነስተን ወደ ሴቷ ቤት ከዚያም እስከ መናፈሻ አብሬ በመሄድ መረጃዬን በቪዲዮ እና በመቅረፀ ድምፅ በመቅረፅ በተፈጥሮ መቼት መረጃዬን ሰብ ስቤ ተመለስኩኝ፡፡በመቀጠልም ጥር 7 ቀን 2004 ዓ.ም ከምሽቱ 1 ሰአት ላይ ወደ ባላገሩ ባህላዊ ምሽት ቤት በድንገት በመሄድ እዚያ ተቀጥረው ከሚሰሩ አንዱን በመጥራት ስለ አዝማሪዎቹ እውቅና እንዲነግረኝ ጠየኩት።ከእሱ እና በባህር ዳር ከተማ ከወጣቶች አዝማሪ

ዎች ታዋቂ ከሆነው ከአዝማሪ ስለሺ ጋር በተመሳሳይ መልኩ 40 ደቂቃ የወሰደ ቃለ መጠይቅ አድርጌ በአርቴፊሻል መቼት መረጃዬን ሰበሰብኩ።በማግስቱ ጥር 8 ቀን 2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 3 ሰአት ላይ የአዝማሪዎቹ ሊቀመንበር ወደሆነው አቶ ትእዛዙን ጋር በመሄድ ስለ አዝማሪዎቹ እውቅና እንዲሁም ለዚህ ጥናት ይጠቅሙኛል ብዬ ያሰብኳቸውን ጥያቄዎች ጨምሬ በመጠየቅ ወደ አንድ ሰአት ከህያ የወሰደ ቃለ መጠየቅ ከሱ ጋር በማድረግ በቴፕ እና በመቅረፀ ድምፅ በመቅረፅ በአርቴፊሻል መቼት መረጃዬን በመሰብሰብ አጠናከርኩ።

በተጨማሪም ስለ አዘማሪዎቹ ታዋቂነት የሰፈራቸውን ሰው እና ባህል ምሽት ቤት የሚታደመው ሰው ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ስላልሆነ በማነጋገር ለመረዳት ጥረት አድርጌአለሁ። በመቀጠልም ከሰአት በኋላ ወደ ባህር ዳር ከተማ ክልል ባህልና ቱሪዝም በመሄድ ከርእሴ ጋር የሚመለከተውን አቶ አበባውን ከሙዚቃ ክፍል አገኘሁ።ከሱ ጋርም ከአዝማሪዎች ጋር በተገናኘ ጉዳዮች ላይ አንድ ካሴት የወሰደ ቃለ መጠይቅ አደረኩ።እንዲሁም በአዝማሪዎች ላይ ያደረጉት ብዙ ጥናት ስለሌለ አንድ ጥናት ብቻ አግኝቼ ኮፒ በማድረግ በአርቴፊሻል መቼት መረጃዬን የበለጠ በመሰብሰብ አጠናከርኩ።በስተመጨረሻም የቀረኝ የነበረው ሌላው አዝማሪዎቹ የሚከውኑበት የቤተክርስያን የጥምቀት ስነስርአት ነበር።በዚህ ክብረ በአል ላይ ባህሉና አውዱ ስለማይፈቅድ የሚከውነው ወንድ ብቻ ነው።ለእኔ ጥናት የተመረጡ አዝማሪዎች ደግሞ በባህር ዳር ከተማ ታዋቂ የሆኑ ሶስት አዝማሪያን በመሆናቸውና ከእነርሱም መካከል ደግሞ አንዱ ብቻ ወንድ በመሆኑ ክዋኔው ሲከውን መመልከት ነበረብኝ።

ስለዚህ አዝማሪ ወርቁ ጥር 12 ቀን 2004 አ.ም የቅዱስ ሚካኤል የጥምቀት ታቦት አጅቦ ስለሚሸኝ እዚያ ልንገኛኝ ተቀጣጠርን።የጥምቀት ቀን ከመድረሱ በፊት እንዴት መቅረፅ እንደምችል አዝማሪዎቹና በቅርብ የማውቃቸውን ሰዎች ጠየኩኝ።የተሰጠኝ መልስ ሁሉም ሰው ነው የሚቀርፀው ችግር የለውም የሚል ነበር።እኔ ግን ብዙም ሳልጠጋ ጥር 11 ቀን 2004 ዓ.ም የጥምቀት እለት በመገኘት ለጥናቴ ማጠናከሪያ የሚሆን የጥምቀትን አውድ ምን እንደሚመስል፣እንዴት እንደሚከወን፣ሌሎች አዝማሪዎች እንዴት እንደሚከውኑት ስመለከት ቆየሁ።ከዚያም ሁሉም ሰው በሚቀርፅበት ቦታ በመሆን በመንገድ እና መስቀል አደባባይ ላይ የተወሰነ መረጃ በተፈጥሮ መቼት በቪዲዮ ቀረፅኩ።በመቀጠልም በማግስቱ የሚካኤል እለት አዝማሪ ወርቁ ጋር በተቀጣጣጠር ነው መሰረት ወደ እዚያው አመራሁ።በዚያን እለት ፀጥታ የሚያስከብሩትን እና ነጭ ነጠላ ለብሰው ከፊት ከፊት እየሄዱ የሚያስተናግዱትን አስተናጋጆች በማስፈቀድ እንድቀርፅ ጠየኳቸው።እነሱም ዳር ዳሩን እየሄድኩ እንድቀርፅ ፈቀዱልኝ።አዝማሪዎቹ ያሉት ከቅዱስ ታቦቱ ፊት ስለሆነ፣ከፊታቸው ዲያቆናት፣አባቶች፣አስተናጋ

ጆች፣የሰንበት ተማሪዎች፣ማህበረ ቅዱሳን፣ዘማሪዎች ስላሉ እና ከነሱ በፊት ጠበንጃ ያነገቱ አባቶች በብዛት መኖራቸው አዝማሪውን ለይቶ ለመቅረፅ አስቸጋሪ ነበር።ያም ሆኖ እያስፈቀ ድኩ የምችለውን ያህል በተፈጥሮ መቼት ቀረፅኩ።ከአማካሪዬ ጋር ክወናው እንዲታይ በሚል ሌላ ክዋኔ ላይ እንድገኝ ተነጋገርን።በዚህም መሰረት ለአዝማሪው ደውዬ ሌላ ቦታ የሚከውንበት ካለ ብዬ ጠየኩት።እሱም በ18 ሰባሩ ጊዮርጊስ ላይ ታቦቱን እንደሚያጅብ ነገ ረኝ።በዚህም መሰረት ጥር 18 ቀን 2004 ዓ.ም የጊዮርጊስ እለት በቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ቀድሜ ተገኘሁ።ከዚያም ከአዝማሪዎች እና ከዘመዴ ጋር በመሆን እኔ የመጣሁት ከዩኒቨር ስቲ መሆኑን የትብብር ደብዳቤ እንዳለኝ፣ህጋዊ መሆኔን በመግለፅ እንዲሁም የጥናቴን አር እስት እና አላማ በመንገር እንዴት መቅረፅ እንደሚቻል ጠየኳቸው።

እነሱም ምንም ችግር እንደሌለው ገልፀውልኝ ለዲያቆናቱ ነገሯቸው።እነሱም ምንም ችግር የለም ራቅ ራቅ እያልሽ ብቻ ታቦቱን ሳትቀርቢ መቅረፅ ትችያለሽ ብለው ፈቅዱልኝ።እኔም በተባልኩት መሰረት ጫማዬን አውልቄ፣ነጠላ ተከናንቤ ስቀርፅ፣እነሱም እኔ በማልደርስበት ቦታ ሲቀርፁልኝ ጫማዬን ይዘውልኝ ሲያግዙኝ ቆዩ።ከዚያ በመሀል የእግዚአብሄር ቃል ልን ሰማ ተቀመጥን ትንሽ እንደቆየን ነጠላ ከለበሱት መሀል መጥቶ ጠራኝና ሀይማኖትሽ ጴንጤ እንደሆነ ተጠቁመናል በማለት የቪዲዮ ካሜራዬን ያለ እኔ ፈቃድ ሲደበድቡኝ ብለው ወሰዱ ብኝ።በመቀጠልም አንድ ክፍል ውስጥ አስገብተው የዚህ እምነት ተከታይ ስላልሆንሽ የቀረ ፅሽው ላንቺ አይገባም ኦርተዶክስ ብትሆኝ ኖሮ እንሰጥሽ ነበር አሉኝ።እኔም አስፈቅጃችሁ የለም ወይ ስል አላስፈቀድሽንም እንዴውም ደፍረሽናል ብለው የፈቀዱልኝንም ካዱኝ።እሺ ይህን ሁሉ ከካዳችሁኝ አጥፍቻለሁ ብዬ ከአንድም ሶስት ጊዜ ይቅርታ ብጠይቅ ይቅርታ አናደርግም ተባልኩ።ከዚያም ካልደመሰስን አንሰጥሽም ብለው ሊደመስሱብኝ ሲሆን ካሜራው እናንተ ጋር ይቆይ ብዬ ለአንደኛ ፖሊስ ጣቢያ አመለከትሁ።ነገር ግን እዚህም ቦታ የተላለፈ ብኝ ብያኔ ይደምሰስ የሚል ነው።እንዴውም ለተወሰነ ሰአት በቁጥጥር ስር እስከመሆን(መታ ሰር) መሰደብ(ሀይማኖታችንን ወባ ልታደርጊው ነው) እና ቃልሽን ስጪ ተብዬ እስከ መገደድ ድረስ ችግር ደረሰብኝ።በዚህ ሁኔታ እያለሁ ኮማንደሩ እና ኮሚሽነሩ ነገሩ ሲደርሳቸው ስልክ ደውለው አስለቀቁኝ።

በዚህ ሁኔታ መረጃዬን ለመቀበል የሴቶች ጉዳይ፣ፖሊስ ኮሚሽነር፣ክልል፣ፀጥታ አስከባሪ፣ ባህል እና ቱሪዝም አመለከትኩ።ነገሩ ግን እያደር እየከረረ ሲሄድ የሀይማኖት አባቶች በኔ ጉዳይ ላይ ስብሰባ አደረጉ(የፕሮቴስታንት፣የካቶሊክ፣የሙስሊም፣የአድቬንቲስት፣የኦርተዶክስ) ከኦርተዶክስ በቀር ሌሎቹ አባቶች ይሰጣት እና ትሂድ ቢሉ ኦርተዶክስን ወክለው የተገኙት

አባት እኔ ብፈቅድም ነገሩ በኮሚቴ ስለተያዘ እኔ መወሰን አልችልም አሉ።ከፈለግሽ እኛ ወጣቱን ሰብስበን አዝማሪውን ጥሪና አብሮን ሆ እያለ መቅረፅ ትችያለሽ አሉኝ።እኔም ይህ ሁኔታ የማይሆንበትን ምክንያት ለመሪ ጌታው ጭምር አስረዳኋቸው።አዝማሪዎች ሌላ ጊዜ እናንተ ሆ እያላችሁ አብረው ከውነው አያዉቁም።ስለዚህ እኔ በጥናቴ ውስጥ አዝማሪዎች እንደዚህ ይከውናሉ ብል ውሸታም ነው የሚያደርገኝ።ስለዚህ አይሆንም እነሱ የሚያጅቡት ታቦት ነው በማለት ነገርኳቸው።ነገር ግን ፈቃደኛ ሊሆኑ አልቻሉም።ስለዚህ መፍትሄ ማሰብ ጀመርኩ።የባለ እግዚአብሄር አመታዊ በአል ላይ ፈቃድ ካለው ጋዜጠኛ ጋር በመሆን በድጋሚ ለመቅረፅ አሰብኩ።ከዚያም እግዚአብሄር እረድቶኝ እንደ ምንም በተፈጥሮ መቼት ተቀረፀ።

ምክንያቱም የፍርድ ቤት ቀጠሮ ቢያንስ እስከ ሶስት ወር ስለሚፈጅ፣ጊዜዬ ስለሚበላሽ እና ሁኔታውም ጥሩ ስላልነበር እስከ ጥር 30-5-2004 ዓ.ም እስከ ቀኑ 12 ሰአት ድረስ በዚህ ሁኔታ እንደምንም ቆየሁ።ከዚያም ለዲፓርትመንት ሀላፊው እና ለአማካሪዬ አሳውቄ የጊዮርጊስ(ሰባሩ ጥምቀት)፣የሚካኤል(ጥምቀት) እና የጥምቀት ቀን በተፈጥሮ መቼት የቀረፅኩት በመሉ ተደምስሶ መታወቂዬ፣የትብብር ደብዳቤ፣ካሜራዬ ተመልሶልኝ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።በአጠቃላይ ከጥር 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥር 30 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ በባህር ዳር ከተማ ውስጥ ቆይታ አድርጌአለሁ።በዚህም ጊዜ ከላይ እንደገለፅኩት ሁኔታውን አስቸጋሪ ስለነበር የቻልኩትን ያህል መረጃውን ላለማስደምሰስ ሞክርኩኝ።ይመለከተዋል የሚባል ቦታ ሁሉ ብዙ ተንገላትቼ ከአቅሜ በላይ ስለሆነ የተደመሰሰብኝ ተደምስሶ ሌላው መረጃዬን በመያዝ የካቲት አንድ ቀን ወደ አዲስ አበባ ከተማ ተመልሻለሁ።

## 1.10.በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦች

### 1.10.1.በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮች

በመስክ ቆይታዬ ወቅት መረጃ ለመሰብሰብ የተለያዩ ችግሮች ያጋጠሙኝ ቢሆንም የተለያየ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በመጠቀም የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ጥረት አድርጌአለሁ። በመስክ መረጃ ስብሰባዬ ወቅት ካጋጠሙኝ ችግሮች መካከል የመጀመሪያው የባህል ምሽት ቤቱ መብራት በጣም ፈዛዛ በመሆኑ ምክንያት ለቪዲዮ ቀረፃ አስቸጋሪ ነበር።ስለዚህም በመፍትሄነት ፓውዛ መብራት ለመጠቀም ብሞክርም ታዳሚዉ መብራቱን አይቶ አንገባም በማለቱ እና የባህል ምሽቱ ባለቤት ስለ ከለከሉ ለመቅረፅ ተቸግሬ ነበር።

ሁለተኛው ደግሞ በጥምቀት ክብረ በአል ላይ አዝማሪዎቹ የሚከውኑት ከታቦቱ ፊት ለፊት እየሄዱ ነበር።ስለዚህ ከአዝማሪዎቹ ፊት ለፊት ደግሞ ዲያቆናት፣አባቶች፣ሰንበት ተማሪዎች እና አስተናጋጆች ስለነበሩ ካለው ህዝብ ብዛት የተነሳ እና በስተ ቀኝ እና በስተግራ በፖሊስ ስለታጠረ ከርቀት አዝማሪውን ለይቶ ለመቅረፅ አስቸጋሪ ነበር።በተጨማሪም ሌባው በራሱ አስቸጋሪ ነበር።

በመጨረሻ የሚነሳዉ ችግር የባህር ዳር ጊዮርጊስ ገዳም ቤተክርስቲያን ሰዎችን እስከ ዲያቆናት ድረስ እኔም ሆንኩ አዝማሪዎች በሰባር ጥምቀት ላይ ለመቅረፅ ጥናት መሆኑን ነግረን አስፈቀድን።ከዚያም ሁሉም አይደል የሚቀርፀው ብለውኝ እየተባበሩኝ በቪዲዮ ስቀርፅ ከቆየሁ በኋላ ሀይማኖትሽ ፕሮቴስታንት(ጴንጤ)ነሽ ተጠቁመናል በማለት የቪዲዮ ካሜራዬን ያለ ፈቃዴ ሊደበድቡኝ ብለው ወሰዱብኝ።

በመቀጠልም አንድ ክፍል ውስጥ አስገብተው የዚህ እምነት(የኦርተዶክስ)ተከታይ ስላልሆንሽ የቀረፅሽው ለአንቺ አይገባም አንሰጥሽም አሉኝ።እኔም አስፈቅጃችሁ ነው የጀመርኩት ብል አላስፈቀድሽንም ደፍረሽናል ብለው የፈቀዱልኝንም ካዱኝ።እሺ ይህን ሁሉ ከካዳችሁኝ አጥፍቻለሁ ይቅርታ ብል ይቅርታ አናደርግም ተባልኩ።ከዚያ ካልደመሰስን አንሰጥሽም በማለት ሊደመስሱብኝ ሲሉ ካሜራው እናንተ ጋር ይቆይ ብዬ ለአንደኛ ፖሊስ ጣቢያ አመለከትኩ። ነገር ግን እዚህም ቦታ የተላለፈብኝ ብያኔ ይደምሰስ የሚል ነው።እንዴውም ለተወሰነ ስአት በቁጥጥር ስር እንስከመሆን(መታሰር)፣መሰደብ(ሀይማኖታችንን ወባ ልታደርጊው ነው እየተባልኩ እስከመሰደብ) ደረስኩ።እኔ መረጃውን ለምንም እንደማላውለው ፈርሜ፣የስራሁትን ኮፒ ሊያዩ ዋስ ልጥራ ብል አይቻልም ተባልኩ።

በዚህ ሁኔታ መረጃዬን ለመቀበል የሴቶች ጉዳይ፣ፖሊስ ኮሚሽነር፣ክልል፣ፀጥታ አስከባሪ ብሄድም ነገሩን ወደ ሀይማኖት እና ወደ ፖለቲካ ቀይረው እይደር እየከረረ ሄደ።ከዚህ የተነሳ የሀይማኖት አባቶች (የፕሮቴስታንት፣የካቶሊክ፣የሙስሊም፣የአድቬንቲስት፣የኦርተዶክስ) በኔ ጉዳይ ስብሰባ አደረጉ።ከኦርተዶክስ በቀር ሌሎቹ ይሰጣት እና ትሂድ ቢሉም ኦርተዶክስን ወክለው የተገኙት አባት እኔ ብፈቅድም ነገሩ በኮሚቴ ስለ ተያዘ እኔ መወሰን አልችልም አሉ።ከዚያም ከነኮሚቴው ኮሚሽነሩ ጋር ተጠርተው ቢባሉ እንቢ ስላሉ ወደ ፍርድ ቤት ነገሩ ይመራ ተባለ።

ምክንያቱም እነሱ ፍርድ ቤት ካልሄደልን ስላሉ።ከዚያም እኔ ሄጄ የምመለስበት ቀን ደረሰ። የፍርድ ቤት ጉዳይ በትንሹ እስከ ሶስት ወር ስለሚፈጅና ጊዜዬም ስለሚበላሽ፣ሁኔታውም

ጥሩ ስላልነበር (ህዝብ ሰላማዊ ሰልፍ ይውጣ ስለተባለ) እና እንዲዉም በስተመጨረሻ ነገሩ እየተባባሰ ሄዶ ከተማ ውስጥ ቀይ ሻቢያ ታቦት ስትቀርፅ ተገኝች እየተባለ መወራት ስለተጀመረ ለህይወቴ መስጋት ጀመርኩ።የኔም መመለሻ ጊዜዬ ደረሰ።ስለዚህ ለዲፐርትመንት ሀላፊው እና ለአማካሪዬ ሁኔታዉን አሳውቄ የጊዮርጊስ(ሰበር ጥምቀት)፣የሚካኤል(የጥምቀት) እና የጥምቀት ቀን የቀረፅኩት በሙሉ ተደምስሶ መታወቂዬ፣የትብብር ደብዳቤ እና ካሜራዬ ተሰጥቶኝ ተመለስኩ።

## 1.10.2.የተወሰደ መፍትሄ

ለመጀመሪያዉ ችግር ከአዝማሪዎቹ ሀላፊ ጋር በመመካከር በሌላ ቀን እኔ በማጠናዉ የአዝማሪ ወርቁ የባህል ምሽት ቤት ዉስጥ ፓውዛው በርቶ በቴፐ፣በቪዲዮ በመቅረፅ እና ፎቶ በመቅረፅ በዚህ ሁኔታ በተፈጥሮ መቼት ሌላ መረጃዬን ሰበሰብኩ።

ለሁለተኛዉ ችግር ሁኔታዉን ከአማካሪዬ ጋር በመመካከር እና የበለጠ በትክክል ክወናው እንዲታይ በሚል ሌላ የከበራ ክዋኔ ላይ እንድገኝ ተነጋገርን።በዚህም መሰረት ለአዝማሪው ደውዬ ሌላ ቦታ የሚከውንበት ካለ ብዬ ጠየኩት።እሱም በ18 ሰባሩ ጊዮርጊስ ላይ ታቡቱን እንደሚያጅብ ነገረኝ።ነገር ግን ከላይ እንዳነሳሁት በድጋሚ በተፈጠረዉ ችግር ምክንያት ለሁለተኛዉ እና ለሶስተኛዉ መፍትሄ የሚሆን የባለ እግዚአብሄር አመታዊ በአል ላይ ፈቃድ ካለው ጋዜጠኛ ጋር በመሆን ለማሳያ የሚሆን ትንሽ ነገር ድጋሚ እንደምንም ቀረፅኩ።

## ምዕራፍ ሁለት

### ክለሳ ድርሳን

### 2.1.ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

ይህ ንኡስ ርዕስ ጥናቱን የሚመለከቱ የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች ከጥናቱ ዋና ዋና ክፍሎች ማለትም ከአዝማሪ፣ከአዝማሪነት እና ከቃል ግጥም አንፃር እየተቀኙ የሚቀርቡበት ነው።

### 2.1.1.ግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ(Personal expriance narrative theory)

የሰው ልጆች ታሪክን ይፈጥራሉ።የታሪኩንም ሁነት በማዋቀር ስለራሳቸው ሆነ ስለሌሎች ይተርካሉ።ግላዊ ተረካዊ ንድፈ ሀሳብ የግል ታሪክን መንገሪያ ነው።

Dolald ስለ ግለ ተረክ ሲናገር ግላዊ ተረክ የሚታየው ወይም የሚጎላው በግል ማብራሪያ ነው።የሰው ልጆች በአለም ውስጥ ሲኖሩ ያካበቱት ልምድ እና በኑሮአቸው ወቅት ከሌሎች ሰዎች ጋር የነበራቸው ተራክቦ አንዳንድ ጊዜ ጠቃሚ ወይም ትርጉም ያለው ሆኖ ያገኙታል።ስለዚህ ይህንን የህይወት ልምድ(ተመክሮ) ለሌሎች ሰዎች ይተርኩታል በማለት ያስረዳል።ከዚሁ ጋር አያይዞ Labov እና Waletzkyን በመጥቀስ ተረክ አንዱ የህይወት ልምድን የመግለጫ ዘዴ ነው በማለት ይገልፃል።(5፡1996)

እንዲሁም Catherine Kohler Riessman ግለ ተረክ አጥሮች የህይወት ታሪክን፡ታሪክን እና ማህበረሰብን ማብራሪያ ማሳያ ዘዴ ነው በማለት ያስረዳል።(5፡2000)

ስለዚህ ከላይ ካሉት ጥቅስ ሀሳብ እንደምንረዳው አዝማሪዎቹ ማንነታቸውን እና የህይወት ተመክሮአቸውን ለሌሎች ሰዎች ለማካፈል የየግል የህይወት ታሪካቸውን ይተርካሉ።ታሪካቸውን በሚተርኩበት ወቅት ገጠመኞቻቸውን፣ገጠመኞቹ የፈጠሩባቸውን ስሜት እና ልምዳቸው ጎልቶ የሚታይ ይሆናል።አዝማሪዎች የሚኖሩት በማህበረሰቡ ዘንድ እንደመሆኑ የራሳቸውን ታሪክ ከመተረክም ባለፈ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለ ማህበረሰቡ ያነሳሉ።በዚህም የህይወት ታሪክ ትረካ አማካኝነት ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸውን መስተጋብር፣ማህበረሰቡ ለእነርሱ ያለውን አመለካከት፣ይህም አመለካከት ያሳደረባቸውን ጥሩና መጥፎ ስነልቦናዊ ሁኔታ እና እነርሱም ለማህበረሰቡ ያላቸዉን አተያይ መመልከት ይቻላል።ስለዚህ በተዘዋዋሪ የዚያን

ማህበረሰብ ማንነት፣ስለ ሌሎች ያለውን አመለካከት፣የማህበረሰቡን የአኗኗር ባህል፣ኢኮኖሚ፣ፖለቲካ፣እምነት፣የማህበረሰቡን መስተጋብር፣ማህበረሰቡ የሚወደውና የሚጠላውን እንዲሁም የማህበረሰቡን አጠቃላይ እንቅስቃሴ እና ሁኔታ ለመረዳት ያስችላል።

ስለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ P,Sikes and K,Gale Moen Cres wellን ጠቅሰው ሲያስረዱ "የህይወት ታሪክ ጥናት፣የጭንቅላት ቅርስ ጥናት ወይም የስነ ዝርያ ሰብእ ጥናት የሚታዩት በተረክ ቅርፅ ነው"።በማለት ይናገራሉ(2፣2006)

እንዲሁም The Concise Oxford Dictiona ary Literary of Terms የተባለው መዝገበ ቃላት

> ተረክ ማለት እውነታን ወይም ልቦለዳዊ ሁነትን መንገር ማለት ነው።ወይም እንደ ገና የተራኪውን ትረካ መዘርዘር መተረክ ማለት ነው።ተረክ አጭጭር ሁነቶችን፣ እረጅም ታሪኮችን፣ህይወት ታሪኮች፣የግል ማስታወሻዎች....ወዘተ የሚያካትት ሲሆን ነገሮችን አዛምዶ የማጥናት ባህሪ አለው።ስለዚህ የተረክ ስልት ታሪክን የመንገሪያ እና ግጥምን የመተረኪያ ዘዴ ነው በማለት ያስረዳል።(165-166፣2001)

ይህም ማለት የህይወት ታሪክ ካልተተረከ በስተቀር ሊታይ አይችልም።ስለዚህ ለመታየት የግድ መተረክ ያስፈልገዋል።እንዲሁም ተራኪዎቹ የህይወት ታሪካቸውን እና ገጠመኞቻቸውን አቀናብረው እንዴት ይተርካሉ፣ቃል ግጥሙን አስከስታውን እንዴት ይከውናሉ ‑የሚለውን የማሳያ መንገድ ነው።ስለዚህ እያንዳንዱን ድርጊት፣ሁነት እና እንቅስቃሴ እንዴት እንደሚነገር፣እንደሚከወን እና ያለውን ጠቀሜታ በግለ ተረካዊ ቅርፅ በመተረክ ማሳየት ይቻላል ማለት ነው።በመሆኑም የተረክ ባህሪያዊ ስልትን በመከተል አጠቃላይ ስለሆነው የአዝማሪዎቹ ባህላዊ የሙዚቃ ጥበብ የበለጠ ለማወቅ እና ለመረዳት የህይወት ታሪኩን እና አጠቃላይ አውዳዊ ክዋኔውን በማዛመድ እመለከታለሁ።

ማለትም ስለ አዝማሪዎቹ ማንነት፣ሙያዊ ለመዳ፣የቃል ግጥም አደራረስ ችሎታ እና አጠቃላይ አውዱን ለመረዳት የህይወት ታሪክን አያይዞ ማጥናት የበለጠ ስለ ጉዳዩ ያለን እውቀት እንዲሰፋ ያደርጋል።ምክንያቱም ከዋኙ በሚደርሳቸው ቃል ግጥሞች ውስጥ ልናገኛቸው የማንችላቸውን የከዋኙ ሙያዊ ለመዳ፣ወደ እዚህ ሙያ የገባበትን መንገድ ...ወዘተ በህይወት ታሪኩ ውስጥ እናገኛለን።በተቃራኒው ደግሞ በህይወት ታሪኩ ውስጥ የማናገኛቸውን ነገሮች በቃል ግጥሞቹ እና በክወናው ወቀት ይንፀባረቃሉ።ለምሳሌ ስለሚገጥምበት ጉዳይ

ያለውን ዉስጣዊ ስሜት ከገፅታው እና ከሁኔታው በክዋኔው ወቅት በመገኘት ለመረዳት ያስችለናል። ስለዚህ ክዋኔው፣ቃል ግጥሙ፣አውዱ እና የህይወት ታሪኩ እርስ በርስ የተያያዙ እና ግንኙነት ያላቸው ነገሮች ናቸው። ማለትም ቴክስቱ፣አውዱ፣ታዳሚው እና ክዋኔው በአንድነት የተጣመሩ ነገሮች ናቸው። ስለዚህ ሁሉንም ነገሮች በአንድነት በማያያዝ መመልከት ስለምናጠናው ጉዳይ ያለን ምልከታ እንዲሰፋ ያደርጋል። ቴክስቱን፣የህይወት ታሪኩን፣አውዱ(ኮንቴክስቱ)፣የታዳሚው ምላሽ(ቴክስቸሩን)...ወዘተ አንዱን በአንዱ ውስጥ በመደባለቅና በማዛመድ ስለሚጠናው ጉዳይ የበለጠ እውቀት ማግኘት ያስችላል ማለት ነው።

ስለዚህም ይህ ጥናት ይህን ጉዳይ ይመለከታል። ግላዊ ተረክ ንድፈ ሀሳብ የህይወት ታሪክን ማሳያ መንገድ ስለሆነ እንዲሁም ከላይ እንደተጠቀሰው ተረካዊ ንድፈ ሀሳብ ነገሮችን በማዛመድ ስለሚያጠና ይህንን ንድፈ ሀሳብ ተጠቅሜአለሁ። ምክንያቱም የእኔ ጥናት የአዝሪዎቹን የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔን በማዛመድ ስለሚያጠና ነው። እንዲሁም እነዚህ አዝማሪዎች የህይወት ታሪካቸውን እንዴት አቀናጅተው ይተርካሉ የሚለውን የሚመለከት በመሆኑ ይህንን ንድፈ ሀሳብ ተጠቅሜአለሁ። ተራኪዎቹ የህይወት ታሪካቸውን ሲናገሩ ልምዳቸውን፣እሴታቸውን፣አመለካከታቸውን፣እምነታቸውን እና የኑሮ ዘይቤያቸውን አብረው በአንድነት ይገልፃሉ። ስለዚህ ከላይ ለማሳየት እንደሞከርኩት ስለምናጠናው ሰው አጠቃላይ ሁኔታ በሚገባ ለማወቅ ይረዳል ማለት ነው።

እንዲሁም እነዚህ አዝማሪዎች የህይወት ተረካቸውን በሚተርኩበት ወቅት ቃል ግጥም ይገጥማሉ። ይህን የአዝማሪው መገለጫ የሆነው ቃል ግጥምን እንዲህ ነው ብሎ ለመበየን አስቸጋሪ ነው። ይህንንም ያደረገው ጉዳይ በተፃፈ እና ቃላዊ በሚባለው ግጥም መካከል ያለው ድንበር ወይም መለኪያ ይህ ነው ሊባል አለመቻሉ ነው። ይህን በተመለከተ ፈቃደ ሲያስረዳ "ቃል ግጥም ማለት አደራረሱ፣አከዋወኑ፣ተስተላልፎው እና አቀራረሱ ብዙ ጊዜ በቃልና በመዜም የሆነ፣በዘፈን፣በሙሾ፣በእንጉርጉሮና በሌሎች ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርፆች ዉስጥ የሚገኝ ህዝባዊ ግጥም ነው በማለት ይገልፃል።(1991፣86)

እንዲሁም ፊኔጋን ስለዚህ ጉዳይ ስትገልፅ"ቃል ግጥም በአደራረሱ፣በከዋወኑ እና በተላልፎው አሻሚ እና አከራካሪ የሆነ ባህሪ እንዳለው አንድ የሆነ ብያኔ ለመስጠት አስቸጋሪ እንደሆነ ታስረዳለች።"(1977፣19)ስለዚህ በአዝማሪዎቹ ዘንድ የሚከወነው ቃል ግጥም የከሌ የማይባል ነገር ግን ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የማህበረሰቡ መገለጫ የሆነ የስነ

ቃል ዘርፍ መሆኑን እንረዳለን።አዝማሪዎቹ ይህንን ቃል ግጥም በተለያየ መንገድ ይደር ሱታል።

በመሆኑም የእነዚህ አዝማሪያንን ክዋኔ፣አደራረስ እና ተስተላልፎውን ቃል ግጥሞቹን በመ ተረክ በምን መልኩ እንደተደረሰ ለማየት እና ለመመርመር ያስችለናል።ከዚሁ ጋር በተ ያያዘ የሚነሳው ሌላዉ ጉዳይ ይህ ቃል ግጥም በሚከወንበት ወቅት ታዳሚው በተለያየ መልኩ ምላሽ ይሰጣል።ምላሹንም በመጮህ፡በማጨብጨብ፡ በመሳቅ፡በመዳነስ...ወዘተ ይገልፃል።ይህ ድርጊት ደግሞ የሚገዝፈው ወይም ተጨባጭ የሚሆነው በክዋኔ ቅርፅ ሲከወን ብቻ ነው።ለምሳሌ አንድ ወገኑ የሞተበት ሰው በማልቀስ ማዘኑን እና የውስጥ ስሜቱን ያንፀባርቃል።ስለዚህ ይህ ክዋኔ ሲተረክ እና በቃል ግጥሙ ውስጥ የሚገኙት ትእምርቶች እየተፈቱ ሲተነተኑ ረቂቅ ሆኖ የማይታየው ነገር ጎልቶ ይታያል ማለት ነው።`ስለዚህ እነዚህ ቃል ግጥሞች በሚከውኑበት ወቅት የሚነሱት አርእስተ ጉዳይ የሚ መለከተው ታዳሚ በመሳቅ፡በማልቀስ፡በማጨብጨብ በመሸለም የማይታየውን ድብቁን ስሜቱን ሳይውቀው ይገልፃል።ወይም ፈንቅሎት ይወጣል።

ስለ ክዋኔ ምንነት Martha C.Sims ስትገልፅ "አብዛኛውን ጊዜ የማይታዩ የማይጨበጡ እሴቶችን፡እምነቶችን፡አመለካከቶችን ክዋኔ እንዲታዩ እና ተጨባጭ እንዲሆኑ ያደርጋ ቸዋል"።(96,2005) በማለት ትናገራለች።እንዲሁም Finnegan ስለ ክዋኔ ምንነት ስት ገልፅ "ክዋኔ አንድ ሁነት ሲከወን በጊዜው ተጨባጭ እንዲሆን ያደርገዋል"በማለት የMartha C.Sims ሀሳብ ትጋራለች።(1992፡87)

ስለዚህ ይህ በክዋኔ ቅርፅ አማካኝነት ከረቂቅነት ወደ ተጨባጭነት የተቀየረዉ የአዝማ ሪው እና የማህበረሰቡ አመለካከት፡እሴት፡የአኗኗር ዘይቤ፡እምነት፡ስነ ልቦናዊ፡ኢኮኖሚ ያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ የአዝማሪዎችን የህይወት ታሪክ እና አጠቃላይ አውዱን በማ ያያዝ በአንድነት በምንተርክበት ወቅት ጉልህ ሆኖ የሚታይ ይሆናል።ስለዚህ የዚህ ሀሳብ ተግባር ከእኔ ርእሰ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ ጥናቴን በተረክ ቅርፅ ለማሳየት ተረካዊ ንድፈ ሀሳብን ተጠቅሚአለሁ።ምክንያቱም ተረካዊ ንድፈ ሀሳብ የሰው ልጅ ድር ጊቶችን፡ሁነቶችን እና ክስተቶችን በአንድ ላይ ማሳያ መንገሪያ መንገድ በመሆኑ ነው።

ሌላው ከክወና ጋር በተያያዘ ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ ክዋኔው የሚከወንበት አውድ ነው። አውድ ማለት ክዋኔው በሚከወን ወቅት ያለውን አጠቃላይ ድባብ የሚይዝ እና የሚያሳይ ማለት ነው።ማለትም ከዋኙን፣ቁሱን፣ያለውን ስሜት፣ድርጊቱን፣ታዳሚውን...ወዘተ ያጠቃል ላል።

ስለዚህ ሁኔታ Dan Ben Amos(1993,215),Martha C. Sim and Marry Haford (137,2005 1995፥53) ስለ አውድ ንድፈ ምንነት ሲናገሩ-

> አውድ መቼ ተከወነ፣የት ቦታ፣ሁኔታውን፣የአድማጩን የትኩረት አቅጣጫ፣የከዋኙን አገላለፅ፣የከዋኙን የፊት ገፅታ፣የአድማጩን ተሳትፎ እንዲሁም እንቅስቃሴውን፣መቼቱን፣ ማህበራዊ ሁኔታው፥ክዋኔው እና ከዋኙ ከአድማጭ ወይም ከታዳሚው ጋር ያላቸውን ግንኙነት እና ስነ ልቦና ሁኔታውን ሁሉ የያዘ ማለት ነው።በማለት ይገልፃሉ።

ስለዚህ ከላይ ካለው ጥቅስ እንደምንረዳው የአዝማሪዎቹን የህይወት ታሪካቸውን፥ክዋኔያቸውን እና ፋይዳውን ሁሉንም ሁኔታ አቅፎ የያዘ አውድ ማለት ነው።ስለ አውድ አይነቶች Dan Ben Amos እንደገለፀው አውዶች ብዙ ቢሆኑም ነገር ግን በዋነኛነት የምናነሳቸቸው ባህላዊ እና ማህበራዊ(ሁኔታዊ)አውድ ናቸው።ባህላዊ አውድ የምንለው የአከባቢያ ክዋኔያዊ ሁኔታን የሚያሳይ ሲሆን መቼቱን፥ከዋኙን፥ታዳሚውን፥ምልክቶችን፥የድምፅ ለውጥን...ያካተተ አውድ ነው በማለት ይናገራል።ማህበራዊ አውድ ደግሞ ከቡድን፥ከማህበረሰቡ፥ከባህል እና ከማህበረሰቡ የተግባቦት ሁኔታ ጋር የተያያዘ ነው በማለት ያስረዳል። እንዲሁም Moen Denzin ጠቅሶ ስለ ተረክ እና ስለ አወድ ሲያነሳ "ተረክ የሚታየው አውዱ እና ማህበራዊ ተራክቦው ሁለቱ ሲዋሀዱ ነው"።(8፥2006) በማለት የአዉድን እና የተረክን ጥብቅ ቁርኝት ያመላክታል።ስለዚህ ተረክን አጉልቶ የሚያሳየው ነገር የአውዶች ውህደት መሆኑን እንገነዘባለን።

አዉድን ስናነሳ በድንገት የሚፈጠሩ ወይም የመከወኛ ቀን፥ቦታ፥ሰአት እና ጊዜ ተወስኖላቸው የሚፈጠሩ የአውድ አይነቶች አሉ።ለምሳሌ ሰርግ እና ሀይማኖታዊ ክብረ በዓሎችን መጥቀስ ይቻላል።እነዚህ ክብረ በዓሎች በተወሰነላቸው ቀን፥ጊዜ፥ቦታ እና ሰአት የሚከወኑ ናቸው።ነገር ግን ጠዋት ከእንቅልፋችን ስንነሳ እንደ ምን አደርክ ለመባባል የምንፈጥረው ድንገቴ አውድ ግን በተወሰነ ጊዜ፥ሰአት፥ቦታ እና ቀን የሚከወን አይደለም።

በተመሳሳይ መልኩ አዝማሪዎችም የሚከውኑበት አውድ የተለያየ ነው።የህይወት ታሪካቸውን ሲተርኩልን የሚፈጠረው አውድ እና ቃል ግጥሞቻቸውን የሚከውኑበት አውድ የተለያየ ነው።እንዲሁም አዝማሪዎቹ ቃል ግጥሞቻቸውን የህይወት ታሪካቸውን ሲተርኩ ከሚያነሱት ጉዳይ ጋር በተያያዘ በመሀል በመሀል ጣልቃ እያስገቡ ቃል ግጥም ይገጥማሉ።ደግሞም ሙያቸው በሚፈቅደው ቦታም ይከውናሉ።

ከላይ እንደገለፅኩት አውዳዊ ልዩነት ሁሉ በአውዱ አማካኝነት የሚፈጠረው ድባብም በከዋኔው ወቅት እንደሚተላለፈው መልእክት ይለያያል(ይለዋወጣል)።ለምሳሌ የፉከራ ቃል ግጥም በሚከወንበት ሰአት የሚኖረው አውድ ወኔን የሚቀሰቅስ፣ማንነትን የሚያሳይ በመሆኑ ከታዳሚው የሚኖረው ምላሽ አብዛኛውን ጊዜ ደመቅ ያለ ስሜት የተላበሰ ነዉ። የእንጉርጉሮ ቃል ግጥም በሚከወንበት ወቅት ደግሞ ትካዜ የሀዘን ድባብ የተላበሰ ነው።

ስለዚህ አውዱ እና የቃል ግጥሙ ይዘት እንደሚፈጥረው ሁኔታ እና እንደሚከወንበት አውዳዊ መቼት በታዳሚውም ሆነ በከዋኙ ላይ የሚፈጥረው አጠቃላይ አወዳዊ ስሜት የተለያየ ነው።ለምሳሌ በሀይማኖታዊ ክብረ በአል አውድ ላይ በመገኘት የሚፈጥረው ስሜት እና በሰርግ አውድ፣በለቅሶ አዉድ ላይ መገኘት በታዳሚው ውስጥ የሚፈጠረው ስሜት የተለያየ ነው።ማለትም በሁለቱም አውዶች ውስጥ ታዳሚው የሚያገኘው ነገር ይኖራል።እርሱም በለቅሶ አውድ ላይ የተገኘው ታዳሚ ያለውን ፍቅር በእንባው በመግ ለፁ እርካታን ያገኛል።በሀይማኖታዊ ክብረ በአል ላይ የተገኘውም የሆዱን ብሶት ለአም ላኩ በመንገር እርካታን ያገኛል።ነገር ግን ከእነዚህ ሁለት አውዶች የሚገኘው የእርካታ መጠንም ሆነ የሚፈጥረው አውዳዊ ድባብ የተለያየ ነዉ።ምክንያቱም በሀይማኖታዊው ክብረ በአል ላይ የሚገኘው ታዳሚ ለአምላኩ ከተናገረ በኋላ አምላኩን በመታመን ከዚያ ሀሳብ ያርፋል።

በለቅሶ አውድ የሚገኘው የታዳሚ እረፍት ግን ጊዜያዊ ነው።ምክንያቱም"የእናት ሞት እና የድንጋይ መቀመጫ እያደር ይቆረቁራል እንደሚባለው"የሞተው ወገን በተለያየ ነገር በታሰበ ቁጥር በውስጡ የሚፈጠር ስሜት አለ።ይህም አውድ ከከወናው እና ከፋይ ዳው ጋር እጅጉን የተያያዘ በመሆኑ አብሮ በግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ አማካኝነት ይገለፃል ይተረካል።በተረክ ቅርፅ በመተረኩም የበለጠ የሚታይ ይሆናል።

እነዚህ ከላይ የተነሱት ክዋኔዎች እና አውዶች የራሳቸው የሆነ ፋይዳ አላቸው።ምክንያቱ ቱም ፎክሎር ያለ አንዳች ፈይዳ አይከወንም አውድም አይፈጥርም።የህይወት ታሪኩ፣ ክዋኔው እና አውዱ ለምን ይከወናል፣ለምንስ አውዱ ተፈጠረ ስንል የራሱ የሆነ ተግባ ራዊ ፋይዳ ይኖረዋል።ስለ ፋይዳ ምንነት Finnegan ስታነሳ 1992፣118 ላይ-

> ፋይዳ ስንል ብዙ እና የተለያየ ነው።ስነ ልቦናዊ፣ማህበራዊ ተግባቦት፣ማህበራዊ ሰነድ፣ትእምርት፣ግላዊ የሆነ ጥበባዊ ገለፃ፣የስልጣን ተዋረዳዊ ግንኙነት፣ርዕዮተ አለም መግለጫ፣ከማህበረሰቡ ጋር ቁርኝት ያላቸው ተፈጥሮአዊ ሰብአዊነት፣ጥበብ እና ታሪክ...ወዘተ ያጠቃልላል።በማለት ትገልፃለች።

እንዲሁም Oring ስለ ፋይዳ ምንነት ሲገልፅ ፋይዳ ከክዋኔ ተለይቶ መታየት እንዳለበት በመግለፅ ፋይዳ ማለት ክዋኔው ሲከወን የሚገኘው ጠቀሜታ መሆኑን ያስረዳል።(1976፣ 6)

ስለዚህ ከላይ የተነሱትን ሀሳቦች በመንተራስ ክዋኔን እና ፋይዳን በመለየት በማን፣መቼ... ጥያቄዎችን ይዘን የአዝማሪዎቹን ክዋኔ፣የህይወት ታሪክ፣በክዋኔው አማካኝነት የሚፈጥረ ውን አጠቃላይ አውዳዊ ድባብ በአንድነት አዋህደን በመያዝ በግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ስንተርክ ፋይዳዉን መመልከት እንችላለን።ስለሆነም የግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ የሰው ልጆችን የግንዛቤ ደረጃ፣ተግባቦት፣ማህበራዊ ግንኙነት ለማወቅ መሰረታዊ ነገር ነው።እንዲሁም እንደትረካው እና እንደ ክዋኔው ሁኔታ ስለ ሚተርኩት ስለሚከውኑት ነገር ያላቸውን እውቀት ለመገንዘብ ያስችላል።

ምክንያቱም ስለ ጉዳዩ ብዙ መናገር ካልቻሉ እውቀታቸው የተገደበ መሆኑን ከአነጋገራቸው እንረዳለን።እንዲሁም በሚተርኩበት ወቅት እና በሚከውኑበት ጊዜ የተረክ አወቃቀር ስልታቸ ውን፣አተራረካቸውን፣ስለ ሁነቱ የሚሰጡትን መረጃ...ወዘተ ከትረካቸው ለመረዳት ያስችለ ናል።በተጨማሪም ምስል ከሳች ቃላትን፣ዘይቤን፣ተምሳሌትን፣ድግግሞሽን...በንግግራቸው እና በክዋኔአቸው ውስጥ ተጠቅመዋል ወይ የሚለውን የግላዊ ተረክ ንደፈ ሀሳብ ለማየት እንችላ ለን።

በሌላ በኩል ደግሞ ታሪካቸውን በሚተርኩበት ሰአት በሚገባ ግልፅ አድርገዋል ወይ፣አጫ ጭር አረፍተ ነገሮችን ይጠቀማሉ ወይ፣የሀሳብ ፍሰቱ እና ቅደም ተከተሉ በሚገባ ተጠብ ቋል ወይ፣ንግግሩ በሰሚው ዘንድ ምስል መፍጠር ይችላል ወይ፣ስነ ውበት አለው ወይ.... ወዘተ የሚለውን ለማየት የግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ ይረዳናል።

ከዚህም በተጨማሪ ቃል ግጥሙን ስንተነትን እና ስንተርክ ከዋኙ ምን ሊል እንደፈለገ ተገንዝበን ለመተረክ እና ቃል ግጥሙን በየምድቡ ለመከፋፈል ይጠቅማል።እንዲሁም የግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ ክዋኔው እንዴት እንደተከወነ፣የመከወኑ ፋይዳ ምን እንደሆነ፣ አስበውበት እና ሳያስቡበት የሚያደርጉትን ድርጊት፣ስሜታቸው እና ሁኔታዎች አስገድ ዷቸው የሚፈፅሙትን ድርጊት፣መቼቱን እና አጋጣሚዎች የሚፈጥሩትን ሁኔታን ለማሳ የት ያስችለናል።ፈቃደ ከዚሁ ሀሳብ ጋር በተያያዘ የስነቃል አጠቃላይ ተግባራትን በአ ምስት አበይት ክፍሎች አስቀምጧቸዋል።እነሱም የመግለጥ፣የማጠናከር፣የመትከል፣የማም

ለጫ፣የማስተማር የመቆጣጠር ተግባራት ናቸው፡፡(1991፣17) ስለዚህ ማህበረሰቡ የስነ ቃል አካል በሆነው ቃል ግጥም አማካኝነት የሚወደውን ነገር ቀጣይነት እንዲኖረው ያጠናክርበታል፣የሚያወግዘውን ይቃወምበታል፣ውስጣዊ ስሜቱን እና ሀሳቡን ያንፀባርቅ በታል፣ያስተምርበታል፣ይመክርበታል፣ያሞግስበታል።

በመሆኑም ተረክ ክዋኔው ሲከወን በጊዜው የነበረውን አውዳዊ ሁኔታ ለመግለፅ፣የአዝማሪ ዎቹን ሙያዊ ህይወት ለመመልከት፣የህይወት ጎዳናቸውን ለማንፀባረቅ፣የማህበረሰቡን ማህበራዊ ግንኙነት ለመፈተሽ ይጠቅማል።አለበለዚያ ታዳሚውም ሆነ አዝማሪዎቹ ምንም ጥቅም ሳያገኙበት እንዲያው በዘፈቀደ ጊዜያቸውን፣ገንዘባቸውን እና ጉልበታቸ ውን አያባክኑም።ከሚከወነው ክዋኔ የሆነ አንዳች ፋይዳ ሊያገኙበት ይገባል።

ለዚህ ነው ፎክሎር ያለ አንዳች ጠቀሜታ የማይከወነው።ስለዚህ አዝማሪዎቹ ያለ ምንም ጥቅም እና ተግባር አይከውኑም።ክዋኔው የራሱ የሆነ ማህበራዊ፣ግላዊ፣ትእምርታዊ፣ስነ ልቦናዊ፣ታሪካዊ፣ማህበራዊ እና የተለያየ ፋይዳ አለው።በመሆኑም የህይወት ታሪካቸው ተረክ፣የቃል ግጥሙ ክዋኔ፣የታዳሚው ሁኔታ፣ምግቡ፣መጠጡ እና አጠቃላይ አውዱ አብሮ ተገጣጥሞ በአንድ ላይ በግላዊ ተረክ አማካኝነት ይታያል፣ይተረካል፣ይነገራል ማለት ነው በሌላ አነጋገር በአዝማሪዎቹ አማካኝነት የሚነገረው የህይወት ታሪካቸው ተረክ፣ከታሪካ ቸው ጋር አቀናብረው የሚናገሩት ገጠመኝ፣የሚከውኑት አጠቃላይ አውዳዊ ክዋኔ እና ፋይዳው በአንድነት ሆኖ በተረክ ቅርፅ ይነገራል፣ይታያል፣ይተረካል።በዚህም የማይታየው ነገር ይጎላል ማለት ነው።

### 2.1.2.የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

ከዚህ በታች የማነሳቸው ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ የሚመሳሰሉ እና የሚለ ያዩ ሁለት የሁለተኛ እና አንድ የዶክትሬት ድግሪ ጥናቶች ናቸው።እንዲሁም የመጀመሪያ ዲግሪ እና ከዚያ በታች የሚገኙ ጥናቶችን ጠቅለል ባለ ሁኔታ የምመለከት ይሆናል።እነዚህ ጥናቶች ከእኔ ጥናት ባሻገር እርስ በራሳቸው የሚመሳሰሉበት እና የሚለያዩበት ነገሮች አሏ ቸው።ጥናቶቹም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ስነጽሑፍ እና ፎክሎር፣በውጭ ቋንቋ ዎችና ስነ ጽሁፍ፣በሶሻል አንትሮፖሎጂ፣በኢትዮጵያ ስነጽሑፍ እና ቋንቋዎች እና በሙ ዚቃ የትምህርት ክፍሎች የተጠኑ ናቸው።

#### 2.1.2.1. የዶክትሬት ጥናት

አሸናፊ ከበደ-"The Music Of Ethiopia.Its Development and Cultural Setting".በሚል ርዕስ በ1971 ዓ.ም ለዶክትሬት ድግሪ ማሟያነት ያቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ ነው።ይህ ጥናት ይህንን ርእሰ ጉዳይ በአስር ገፅ ብቻ ነው የተመለከተው።እሱም ስለ አዝማሪ ምንነት፣ስለ አዝማሪ አመጣጥ እና በማህበረሰቡ ዘንድ ስላላቸው ቦታ ማንሳቱ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለ ዋል።ከዚህ በስተቀር ቃላዊ ግጥም በመሰብሰብ አለመተንተኑ፣ክዋኔውን፣ተስተላልፎውን..... አለማሳየቱ፣ከኔ ጥናት ይለየዋል።ነገር ግን ያነሳቸውን እነዚህን አርዕስቶች በሚገባ ተመልክ ቷቸዋል።

ከላይ የቀረበው ጥናት ስለ አዝማሪ ሙያ በተወሰነ ትኩረት አድርጎ የተሰራ ቢሆንም ቃል ግጥሙን፣ክዋኔውን፣ለመዳውን፣ተስተላልፎውን...ወዘተ ባለመመልከቱ ከኔ ጥናት ይለያል።

#### 2.1.2.2. የሁለተኛ ዲግሪ ጥናቶች

ከፍያለው አዘዘ- "Minstrels In Addis Ababa In The Social Life of Gonderian Inzat a" በሚል ርእስ በ1998 ዓ.ም ለማስተርስ ድግሪ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው።ይህ ጥናት በዋነኛነት የአዝማሪዎቹን ቃል ግጥሞች በአይነታቸው መከፋፈል፣አዝማሪዎች ከሌሎች ክፍለ ሀገራት ወደ አዲስ አበባ እንዴት እንደሚመጡ፣ማህበረሰቡ ለአዝማሪዎች የሚሰጣቸ ውን ስያሜዎች፣የት የት ቦታ እንደሚከውኑ፣የአዝማሪዎቹን ማህበራዊ መስተጋብርን መመ ርመር፣አዝማሪዎች የሚቀኙት ቃል ግጥም ያለውን ፋይዳውና የስራ ህይወታቸውን መመል ከት ላይ ያተኮረ ነው።ከእኔ ጥናት ጋር ስለ አዝማሪዎቹ አመጣጥ እና ምንነት እንዲሁም

ክዋኔውን መመልከቱ ያመሳስለዋል።ነገር ግን በሚጠናበት ስፍራ፣የአዝማሪዎቹን የህይወት ታሪክ ባለመመልከቱ እና አዝማሪዎቹን ባለመምረጡ፣የአዝማሪዎችን ባህላዊ ሙዚቃ ለውጥ ባለመመልከቱ፣ሀይማኖታዊ እና የመንግስታትን አቀባበል ክዋኔ ባለማየቱ ከኔ ጥናት ይለያል። ተዛማጅ ቅኝት በሚያደርግበት ጊዜ ጥናቶቹን ክርቲካሊ አላያቸውምክሪቲካሊ(በሂሳዊ መንገድ አላያቸውም)፣ንድፈ ሀሳቡን በሚገባ ተጠቅሞ ተንትኗል።

አበበ ማለደ "በጎንደር ዙሪያ ወረዳ በቡርባክስ ቀበሌ የአዝማሪነት ሙያና የዘፈን ግጥሞች" በሚል ርእስ በ2002 ዓ.ም ለማስተርስ ድግሪ መመረቂያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው።የዚህ ጥናት ትኩረት የአዝማሪዎቹን ታሪካዊ ዳራ ማጥናት፣ማህበራዊ መስተጋብራቸውን መመርመር እና ግጥማቸውን እና ቁሱን ማጥናት ላይ ነው።ስለ አዝማሪ ማንሳቱ፣ግጥሞቹን መመልከቱ ከኔ ጥናት ጋር ሲያመሳስለው በጥናቱ ቦታ፣የዚህን ባህላዊ ሙዚቃ ለውጥ ባለመመልከቱ፣የሀይማኖት እና መንግስታት አቀባበል ክዋኔ አለማየቱ ከኔ የተለየ ያደርገዋል።

በዚህ ጥናት ውስጥ አንዳንድ አላስፈላጊ መንደርደሪያዎችን እናገኛለን።ተዛማጅ ፅሁፎችን ክሪቲካሊ(በሂሳዊ መንገድ አላያቸውም)።ጥቅሶችን መርጦ የማስቀመጥ ችግር ተመልክቻለሁ።እንዲሁም ለቲዎሪው የራሱን ትንታኔ በብዛት አለመስጠት(ቲሪውን ብቻ ማስቀመጥ)እነዚህን የመሳሰሉ ችግሮችን በዚህ ጥናት ውስጥ ይስተዋላሉ።ከዚህ ባሻገር ግን አጥኚው በጥናቱ ላይ እንደተመለከትኩት ስለ ጉዳዩ ለማወቅ እና ጥሩ ነገር በጥናቱ ለማምጣት ያደረገውን ጥረት፣ትግል እና መፍጨርጨር ጥናቱ አመላካች ነው።የጥናቱ ቋንቋ ጥሩነት፣ነገሮችን ከተለያየ አቅጣጫ መመልከት የመሳሰሉ ጠንካራ ጎኖቹ ከድክመቱ ያመዝናሉ።

ከላይ የቀረቡት ሁለት ጥናቶች ስለ አዝማሪ ሙያ ላይ ትኩረት አድርገው የተሰሩ ቢሆኑም ጥናታቸውን ባካሄዱበት ስፍራ፣የአዝማሪዎቹን የህይወት ታሪክ አያይዘው ባለማጥናታቸው እና በታዋቂ አዝማሪዎች ላይ ባለመስራታቸው፣የዚህን የአዝማሪ ባህላዊ ሙዚቃ ጥበብ ለውጥ ባለመመልከታቸው፣ሀይማኖታዊ እና የመንግስታትን አቀባበል ክዋኔን ባለማየታቸው ከኔ ጥናት ይለያሉ።ከዚህ በተጨማሪ በዚህ እርሰ ጉዳይ ላይ የተጠኑ በመጀመሪያ ድግሪ ስድስት ጥናቶች ሲኖሩ በዲፕሎማ ደረጃ ደግሞ ሁለት ጥናቶች ይገኛሉ።

### 2.1.2.3. የመጀመሪያ ድግሪ ጥናቶች

አልማዝ አበበ- "አዝማሪ እና ግጥሞቹ በየጁ አውራጃ"1974፣ኑር ሁሴን ሙሀመድ-"በሮገራ አከባቢ የሚሰሙ የአዝማሪ ግጥሞች ይዘታዊ ትንተና"1986፣ቆንጂት ወልደ ማሪያም"Major

Themes In The Play Azmari"1998፣መንገሻ አማረ- "የወገል ጤና አዝማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ቃላዊ ግጥሞች"1992፣አንለይ ሙሉ -"የአዝማሪ ታደለ የህይወት ታሪክና ቃላዊ ግጥሞች"1995 እና ህሊና ፍቃዱ- "Survey Of Ethiopian Female Azimaris In Addis Ababa"2006 ናቸው።

የእነዚህ ጥናቶች ትኩረት ስለ አዝማሪው ምንነት፣አመጣጥ፣በማህበረሰቡ ዘንድ ስላለው ቅቡልነት፣ስለ ማሲንቆ አመጣጥ እና ቃል ግጥሞቹን በየመደባቸው ከፋፍሎ ይዘታዊ ትንታኔ ማድረግ፣አዝማሪዎች ታሪክን አጣቅሶ ለማጥናት ጠቃሚ መሆናቸውን፣ማህበረሰቡ ለእነዚህ አዝማሪዎ ዝቅተኛ አመለካከት እንዳለው ማሳየት ነዉ።እንዲሁም ስለ ቃላዊ ግጥም ምንነት ተስተላልፎ፣የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ መንፈሳዊ እና አለማዊ በመባል እንደሚከፈል፣የአዝማሪ ሙዚቃ ከአለማዊው ውስጥ እንደሚመደብ፣ሴት አዝማሪያን ጥሩ ድምፅ እንዳለቸው በዚህም የታዳሚውን ትኩረት የመያዝ ችሎታ እንዳላቸው ወዘተ... ማመላከት ነው።በተጨማሪም ከክርስትና መምጣት በኋላ የአዝማሪ ሚና እያደገ እና አለማዊ ሙዚቃ እየሆነ እንደመጣ፣ይህ ሙያ በማህበራዊ፣ፖለቲካ ላይ ትልቅ አስተዋፅኦ ስላለው በዚሁ መስክ ጉልህ ሚና እንዳላቸው በሚሉ ጉዳዮች ላይ ያውጠነጠኑ ጥናቶች ናቸው፡፡

የጥናቶቹ ደካማ ጎን በመረጃ ያልተደገፈ ሀሳብ ማስቀመጥ፣አላማው እና አነሳሽ ምክንያቱን መደበላለቅ፣የጥናት ዘዴን አለመግለፅ እና የዋቢ ፅሁፍ አፃፃፍ አቀማመጥ...ወዘተ ችግሮች ይታይባቸዋል።ጥናቶቹ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው የአዝማሪዎችን ግጥም መሰብሰባቸው፣በይዘት በመከፋፈል ተንታኔ ማድረጋቸው፣ስለ አዝማሪ አመጣጥ ማናሳታቸው፣ማህበረሰቡ ስለ አዝማሪ ያለውን አመለካከት መመልከታቸው፣አንድ ጥናት የህይወት ታሪክ አያይዞ ማጥናቱ ነው።ክዋኔዉን፣አደራረሱን እና የዚህን ባህላዊ ሙዚቃ ለውጥ...ወዘተ አለመመልከታቸው ከእኔ ጥናት ይለያቸዋል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

### 3.1.የሶስቱ አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ እና የቃላዊ ግጥሞች የይዘት ትንተና

በመጀመሪያ ወደ ህይወት ታሪኩ እና ወደ ቃል ግጥሙ ትንታኔ ከመግባቴ በፊት የምተነትናቸው ቃል ግጥሞችን ማን እንደሚከውናቸው፣መቼ እንደሚከወኑ፣የት ቦታ እንደሚከወኑ፣እንዴት እንደሚከወኑ እና ለምን ፋይዳ እንደሚከወኑ እንዲሁም ገጣሚዎቹ የህይወት ታሪካቸውን እንዴት ይተርካሉ፣የህይወት ታሪካቸውን በሚተርኩበት ወቅት ገጠመኞቻቸውን እና ቃል ግጥሞቻቸውን አቀናብረው በመሀል እንዴት ያቀርባሉ የሚለውንም እመለከታለሁ።በመሆኑም በምዕራፍ ሁለት ለዚህ ጥናት መቀንበቢያነት ያነሳሁትን በግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ(ቲወሪ)በዚህ ትንተናዬ ውስጥ እያሰናሰልኩ አቀርባለሁ።

በዚህ መሰረት ከዚህ በታች ከእያንዳንዱ አዝማሪ የህይወት ታሪክ ጋር ተቀናብረው የሚቀርቡት ቃል ግጥሞች በእነዚህ ሶስት አዝማሪያን በምሽት ቤት፣በሰርግ፣በጥምቀት እና በአመታዊ በአል ወቅት የተቀጿቸው ናቸው፡፡በባህል ምሽት ቤት ከቀረቡት 118 ቃል ግጥሞች፣ከሰርግ 104፣በጥምቀት እና በአመታዊ በአል ላይ 104 የሚሆኑ የሀይማኖት ቃል ግጥሞችን ሰብስቤአለሁ፡፡በአጠቃላይ 327 ቃል ግጥሞች በዚህ ጥናት ተሰብስበዋል።እነዚህ ቃል ግጥሞች አዝማሪያኑ ከሌላ ሰው ሰምተው በመድገም፣በማሻሻል እና አዲስ በመፍጠር የሚገጥሟቸው ናቸው፡፡

ቃል ግጥሞቹ በባህሪያቸው አሳተፊ በመሆናቸው ግጥሞቹን በማቅረቡ በኩል አዝማሪያኑ ብቻ ሳይሆኑ ታዳሚዎቹም ተሳታፊ ነበሩ።ይህም ታዳሚው የተሰማውን የሆዱን ስሜት አዝማሪውን "ተቀበል" በማለት በቃል ግጥም አማካኝነት ያንፀባርቃል፡፡እነዚህ አዝማሪያን ከራሳቸው ፈጠራ በተጨማሪ ከታዳሚው የተቀበሉትን ቃል ግጥም ደግመው ይከውናሉ።ስለዚህ ቃል ግጥሞቹ የተለያየ ጉዳይን ያነገቡ እና የማህበረሰቡን ስሜት እና ትንፋሽ የሚያንፀባርቁ አድርጓቸዋል፡፡

እንዲሁም ለዚህ ጥናት የተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች የሚገጠሙበት አውድ ላይ የሚታደሙት ሰዎች ካልተማረው እስከ ከተማረው ህብረተሰብ ድረስ የሚያካትት መሆኑ፣አዝማሪዎች አበብዛኛውን ጊዜ ታዳሚውን ማስደሰት እና ማዝናናት ላይ ማተኮራቸው እንዲሁም ቅኔያዊ የሆኑ ቃል ግጥሞችን የሚፈልጉት አብዛኛውን አዛውንቶች መሆናቸው እና ይህሙያ ለአዝማሪዎቹ መተዳደሪያቸው መሆኑ ኪነ ጥበቡን እና ባህሉን ከመጠበቅ ይልቅ ወደ ንግድነት እንዲያደላ አድርጎታል።

በዚህም ምክንያት አብዛኛዎቹ ቃል ግጥሞቹ በእምቅነታቸው፣በቋንቋ መረጣቸው እና ቅኔያዊነታቸው ደካማ ሆነው እናገኛቸዋለን።አዝማሪዎቹ ቃል ግጥሞቹን በሚደርሱበት እና በሚከውኑበት ወቅት ሙሉ በሙሉ ሸምድደውና አስታውሰው በመድገም የሚገጥሙበት ሁኔታ አለ።ለምሳሌ-

እኔስ ደስ ይለኛል የአርሶ አደሩ ኑሮ
እሸቱ ከማጀት ወተቱ ከጓሮ

በሌላ በኩል ደግሞ የተወሰነ የሀረግ ለውጥ አድርገውበት(አሻሽለውት)የሚደርሱበት ሁኔታም አለ።የበለጠ ሀሳቤን ግልፅ ለማድረግ በምሳሌ ላሳይ-

ራስን መቻል ነው ጥሮ ተጣጥሮ
ሁል ጊዜ በሞግዚት አይገኝም ኑሮ(የበፊቱ)

ቶሎ ቶሎ ብሎ ራስን መቻል ነው
ከዘመድ መጠጋት የበኋላ ጠብ ነው(የአሁኑ)

ከዚህም ባሻገር አዝማሪዎቹ ከሚፈጠረው አውዳዊ ሁኔታ በመነሳት የሚፈጥሯቸው አዳዲስ ቃል ግጥሞችም አሏቸው።ለምሳሌ-

አገሬ ኢትዮጵያ የተባረከች
አሁን ሰው አግኝታ በጣም አድጋለች

የአምስት አመት እቅድ አልቀረም ተለፍቶ
መጣ የጨመረ የሴቶች ተሳትፎ

አዝማሪዎቹ እነዚህን ቃል ግጥሞች በጊዜው ከነበረው አውድ በመነሳት ፈጥረው የገጠሟቸው ናቸው፡፡ተሻሽለው ወይም በመታወስ ተደግመው የተገጠሙ አይደሉም፡፡ስለዚህ የእነዚህ ሶስት አዝማሪያን ቃል ግጥሞች በመታወስ፣በመሻሻል እና አዲስ ፈጠራ እየታከለባቸው የተገጠሙ ቃል ግጥሞች ናቸው፡፡ይህንን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች የእነዚህን ሶስት አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ ከቃል ግጥሞቻቸው፣ከክዋኔው፣አውዱ እና ከፋይዳው ጋር አብሮ በማቀናጀት ከዚህ በታች መተንተን ይሆናል፡፡

## 3.2. የአዝማሪ ወርቁ ታዬ የህይወት ታሪክ

አዝማሪ ወርቁ ታዬ ተወልዶ ያደገው ጎንደር አከባቢ በምትገኘው በርቧክስ ወረዳ ውስጥ ሲሆን የ57 አመት የእድሜ ባለ ፀጋና የሶስት የልጆች አባት ነው።አዝማሪው የተወለደው ገጠር ውስጥ ስለነበርና በተለይ ወንድ ከሆነ የሚፈለገው ለከብት ጥበቃ እና ለእርሻ በመሆኑ ትምህርት አልተማረም፡፡ነገር ግን ግጥም መግጠም የተፈጥሮ ስጦታ ስለሆነና እየቆየም የሚዳብር በመሆኑ ሙያውን ለመልመድ አልተቸገረም።እርሱም ስለዚህ ሁኔታ ሲተርከልኝ "ባልማርም ከተማረው እኩል ግጥም የመግጠም ችሎታ አለኝ"በማለት ይናገራል።(ቃለ፡4፡ 2004)

ይህ አዝማሪ በአብዛኛው ቃል ግጥሞችን የሚደርሰው አስታውሶ በመድገም ነው፡፡ይህ ማለት ግን ራሱ ፈጥሮ አይገጥምም ማለት አይደለም፡፡በተለይ አውዱን ለትንሽ ደቂቃ በመመልከት የተሰማውን ስሜት ወዲያው በቃል ግጥም አማካኝነት ያንፀባርቃል፡፡እንዲሁም ሌሎች አዝማ ሪያን ቀርቤ ሳነጋግር፣ቃለ መጠይቅ ሳደርግ እና አብሬአቸው በማሳልፍበት ወቅት ከሌሎች አዝማሪዎቸ ወርቁን ለየት የሚያደርገውን ነገር ተመልክቻለሁ።ይኸውም ከሌሎች አዝማሪ ዎች ይልቅ ቃል ግጥሙን አስታውሶም ይሁን ፈጥሮ ከአውዱ ጋር በማስማማት በፍጥነት የመከወን ችሎታው ነው።አውዱን በማየት ከገጠማቸው ቃል ግጥሞች መካከል አንዱን ለም ሳሌነት ላንሳ-

ሽሙንሙን ሽሙንሙን ሽሙንሙን በይልኝ
የያዘኝ አባዜ ገለል እንዲልልኝ

ይህን ቃል ግጥም የገጠመው ባህል ምሽት ቤት ውስጥ በሚከውንበት ወቅት ባለቤቱ የአበሻ ቀሚስ ለብሳ አምራ ተውባ ስለተመለከተ ነበር፡፡ሌላው የዚህ አዝማሪ ችሎታ ሁሉንም ታደሚ በአማከለ ሁኔታ አውዱን መቆጣጠር ይችላል፡፡ማለትም ትልቁንም ትንሹንም እንደ እድሜው ደረጃ በሚገጥመው ቃል ግጥም ያዝናናል፡፡እንዲሁም ቃል ግጥሞችን ፈጥሮ ይገጥ ማል።በአብዛኛው ፈጥሮ የገጠማቸው ቃል ግጥሞች የሚገኙት በፉከራው ላይ ሲሆን በጥቂቱ ደግሞ በሀይማኖት ዝማሬዎች ላይ ጣልቃ እያስገባ የሚጫወታቸው ናቸው፡፡ከፉከራው እና ከሀይማኖት ቃል ግጥሞቹ መካከል ለአብነት ያህል ላንሳ-

እስካልበዉና ኸረ ተው በለው ኸረ ተው በለው
እንቢ ካለማ ነፍጠኛ ጎጄ አናቱን በለው

እምላክ ወርዶ ከምድር
አዳምን ዋና ሊያስተምር
እከ እንትፍ ብሎ ቢያሳያቸው
ምራቁ አሳዘናቸው

ይህ አዝማሪ ወደ እዚህ ሙያ እንዲገባ የጎረቤቱ ግፊት እና በጎንደር ውስጥ መወለዱ ወሳኝ ምክንያቶች ናቸው።አዝማሪው እንደነገረኝ አብዛኛው አዝማሪዎች የሚገኙት በጎንደር ሀገር በመሆኑ አንዱ አንዱን በማየት ወደ ሙያው እንዲያዘነብል ያደርገዋል።ይህም አዝማሪ ወደ እዚህ ሙያ የገባው በዘር ሳይሆን ጎረቤቱን በመመልከት ነበር።ይህን በተመለከተ የህይወት ታሪኩን በሚተርክልኝ ሰአት እንዲህ ነበር ያለኝ።

> ወደ እዚህ ሙያ እንዳዘነብል ያደረገኝ ጎረቤቴ በማሲንቆ ሲጫወት ስሰማው ደስ ይለኝ ስለነበር ነው።ከዚህም በተጨማሪ አንድ ቀን አባቴ ማሲንቆ ያገኝና እቤት ይዞት ይመጣል።ከዚያም ያችን ማሲንቆ ገለባ ውስጥ ደብቄ ማታ ማታ እበረት ውስጥ ሁኜ እየተደበቅሁ ዝም ብዬ እደበድባለሁ።ከዚያም ጎረቤታችን ማሲንቆውን አዘጋጅቶ ሰጠኝ ቅኝቶቹን በጣቶቹ እነዚህ እነዚህ ይባላሉ እያለ አሳየኝ።እንዲሁም እነዚህን ቅኝቶች በድምፅህ ዝፈን ይለኛል።በዚህ ሁኔታ መለማመድ ጀመርኩ።ሌላው ደግሞ የሙዚቃ ስሜቱ ስላለኝ ከተማ ሄደን ጠላ አዘን ተቀምጠን አዳምጣለሁ።በተጨማሪም እንዴት እንደሚመታ ጣቱን እያየሁ ደጋግሜ በመደብደቤ እየገባኝ መጣ። ከዚያም ጉርምስና ሲሰማኝ መዝፈን ጀመርኩ።ትንሽ ቆይቼም ለአምስት አመት ኦሮሚያ ነቀምት ውስጥ ኪነት ሳሰለጥን ቆየሁ።በዚህ ጊዜ ወሰጋ ውስጥ ኦሮምኛ በማሲንቆ ብቻ ያለ ድምፅ እቀኝ ነበር።(ቃለ 4፣2004)

አዝማሪ ወርቁ እና ሌሎች አንዳንድ የባህር ዳር አዝማሪዎች እንደነገሩኝ ማህበረሰቡ ሙያውን በመናቅ እና በማግለል የሚያሳድርባቸው ዝቅተኛ የሆነ አመለካከት በሙያው ላይ ተፅእኖ አሳድሮባቸዋል።ነገር ግን አዝማሪ ወርቁ ችግሩን ተቋቁሞ ለሀያ ስምንት አመታት ያህል በዚህ ሙያ ውስጥ ሰርቷል።በአሁን ሰአትም እየሰራ ይገኛል።አዝማሪው ይህንን ሁኔታ ለመግለፅ የሞከረበትን ቃል ግጥም እንደ ምሳሌነት ላንሳ-

እኔ ምን ቸገረኝ አዝማሪ ቢሉኝ
የሰው ልጅነቴ ከአገር ሲገኝ

ይህ አዝማሪ በመፍጠርም ይሁን አስታውሶ በመድገም የሚገጥማቸው ቃል ግጥሞች አብዛኛ ዎቹ ህብርዊነት ያላቸው ናቸው።

ከላይ ያነሳሁትን ቃል ግጥም በምሳሌነት መመልከት ይቻላል።ቃል ግጥሙ አንድም እኔም እኮ ልክ እንደነርሱ የሰው ልጅ ነኝ የሚል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አመጣጤን ቢያጠኑ ታሪክን ቢያውቁ ሙያው ከጥንት የነበረ እና የተከበረ ነው የሚል ሀሳብን አምቆ የያዘ ነው ይህ የማህበረሰቡ ዝቅተኛ አመለካከት አሁኑም ሙሉ በሙሉ ባይቀረፍም በተወሰነ ደረጃ እያደር ባለው ለውጥ ግን ደስታው ዳግም እንደመወለድ ያህል ነው።ይህ ለውጥ ከመምጣቱ በፊት ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የገጠመውን ገጠመኝ ከህይወት ታሪኩ ጋር አቀናጅቶ ሲተር ክልኝ እንዲህ አለኝ።

> ሴቶች ስዘፍን ቴፕ እየከፈቱ ያበሳጩኝ ነበር።በዚህ ተናድጄ አንድ ቀን ለምን የቀን ስራ ሰርቼ አልበላም ብዬ ማሲንቆዬን ስቀድ ፖሊስ ያዘኝ።ለምን እንዲህ እንደማደርግ ከጠየቀኝ በኋላ ለምን ሰው እንዲህ አለኝ ብለህ እንዲህ ትሆናለህ ብሎ አበረታኝ። አሁን አሁን ግን ይህ የባህል ቤት ከመጣ በኋላ ሰው የዚህ ሙያ ምንነት እና ጠቀ ሜታ እየገባው መጥቷል።በአሁን ሰአት ህዝቡ እየተረዳው በመምጣቱ ዘመናዊውን እየተወ ወደ እኛ ለመዝናናት እየመጣ እና እየተለወጠ ነው።በማለት ለውጡን ይናገራል።(ቃለ፤4፤2004)

ይህ አዝማሪ በባህር ዳር ካሉ አዝማሪዎች የሚለየው ሌላው ችሎታው አራቱን ቅኝቶች ለይቶ መጫወቱ ነው።ሌሎች አዝማሪዎች እነዚን ቅኝቶች መጫወት ሲያቅታቸው ተፈልጎ እንዲገባ ይደረጋል።አንቺ ሆዬና አንባሰል እየተቀላቀሉ የሚያስቸግሩ ቅኝተቶች ናቸው። አዝማሪ ወርቁ ግን ከሌሎቹ በተሻለ ሳይሳሳት በትክክል ለይቶ ይጫወታቸዋል።

እነዚህ ቅኝቶች በተለይ በአዛውንቶች ዘንድ ተፋላጊ በመሆናቸው እሱን ይበልጥ ተፈላጊ እን ዲሆን አድርጎታል።አዝማሪው ይህንን ሁኔታ ሲያስረዳ "ሌላው አዝማሪ እኔ የምፈለግበትን ሙያ ለመማር ጥረት ያደርጋል።በእዚህም አርአያ እሆናለሁ" በማለት ከሌላው የሚለይበትን ይናገራል።(ቃለ፤4፤2004)።እንደዚሁም የባህር ዳር አዝማሪዎች ማህበር ሀላፊ የሆነው አቶ ትእዛዙ ይህንን ጉዳይ ሲያስረዳ "በተለይ ወርቁ አንባሰል፤አንቺ ሆዬ ሲጫወት በጣም ትልቅ ባለ ሙያ ነው።"በማለት ይናገራል።(ቃለ፤7፤2004)

በሌላ መልኩ ደግሞ አዝማሪው በእድሜ አንጋፋነት እና በሙያ ቀደምትነት ታዋቂ ሲሆን በአሁን ሰአት ዳሞት የተሰኘ የባህል ምሽት ቤት በመክፈት ለሌሎች አዝማሪዎች ማደጊያ በመሆን ባህሉ ተጠብቆ እንዲተላለፍ ትልቅ አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል።እንዲሁም ይህ አዝማሪ የህይወት ታሪኩን በሚተርክበት ሰአት የሚጠቀመው ቋንቋ እና አገላለፁ ከእርሱ አለመማር ደረጃ አንፃር ሲታይ ደህና የሚባል ነው።በምዕራፍ ሁለት ንድፈ ሀሳብ ላይ

እንደተንሳው የግላዊ ተረክ ቲወሪ ስለ ራስ እና ስለህብረተሰቡ መንገሪያ ነው።ስለዚህ አዝማሪው የህይወት ታሪኩን ሲተርክ በተያያዥነት ማህበረሰቡ ለእዚህ ሙያ ያለውን አመለካከት፣ይህም ዝቅተኛ የሆነ አመለካከት ያሳደረበትን ስነ ልቦናዊ ተጽእኖ፣ማህበ ረሰቡ ለሌሎች ያለውን አተያይ፣የማህበረሰቡንም ሆነ የራሱን ማንነት፣የእውቀት ደረጃ እና ገጠመኞቹን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ይገለፃል።

በአጠቃላይ ይህ አዝማሪ ፈጥሮም ይሁን ደግሞ የሚገጥማቸው ቃል ግጥሞች አንዳንዶቹ ከህይወቱ ተመክሮ ጋር የተቆራኙ፣ከሁኔታው፣ከአውዱ ጋር የተዋሀዱ፣አስቂና አስተማሪ የተ ለያየ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ናቸው፡፡ስለዚህ ከዚህ በታች ምእራፍ ሁለት ንድፈ ሀሳብ(ቲወሪ) ላይ እንዳነሳሁት የተረክ ንድፈ ሀሳብ ነገሮችን አዛምዶ ያጠናል።ስለዚህ የዚህን አዝማሪ አጠ ቃላይ ሁለንተና በበለጠ ለመገንዘብ የከወናቸውን ቃል ግጥሞች፣ክዋኔውን፣አውዱን፣ፋይዳ ውን ከህይወት ታሪኩ ጋር በማቀናጀት እመለከታለሁ።

የአዝማሪ ወርቁን ቃል ግጥም ከመተንተኔ በፊት ከዚህ በታች የሶስት አዝማሪያን አጠቃላይ የባህል ምሽት ቤት አወዳዊ ክዋኔ ምን እንደሚመስል ለማሳየት እሞክራለሁ።ቃል ግጥም ካልተከወነ በስተቀር ሊታይ አይችልም፡፡የባህር ዳር ከተማ አዝማሪዎችም የመከወኛ ቦታዎች አላቸው።ገንዘብ ተከፍሎአቸው እና ዝፈንልኝ ተብለው በመጠራት በሰርግ አውድ ላይ ይከ ውናሉ።እንዲሁም ባህል ምሽት ቤቶች ተቀጥረው ይሰራሉ።በአመት አንዴ ደግሞ በጥም ቀት እና ታቦት በሚወጣባቸው አመታዊ በአላት ላይ በመገኘት ይከውናሉ።በተጨማሪም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከተለያዩ ቦታዎች መንግስታት ወደ ባህርዳር ከተማ በሚመጡበት ወቅት የቅበላ ስነ ስርአት ላይ ይከውናሉ፡፡

ይህንንም በተናጠል፣ጥንድ እና በቡድን ሆነው ይከውናሉ።እነዚህ አዝማሪያን በቡድን ሆነው ሲከውኑ ያየሁት በባህል ምሽት ቤት ውስጥ ሲሆን ሁለቱ እየተቀባበሉ ሲዘፍኑ ሌላኛዋ አዝማሪ እስክስታ ትመታለች።በተመሳሳይ መልኩም የመንግስት እንግዶችን የሚቀበሉት በህብረት ሆነው በመከወን ነው።

አዝማሪዎቹ በባህል ምሽት ቤት ውስጥ ወደ ዋናው ክወናቸው ከመግባታቸው በፊት ማሲ ንቆ በትክክል መቀኝቱን እየደጋገሙ ያስተካክላሉ።ከዚያም የመጀመሪያው ገቢ በሰላም አውሎ ለዚህ ሰአት ያደረስከኝ አምላክ ተመስገን እያለ በዘለሰኛ እና መዲና መዝሙር ለብቻው ሆኖ ይከወናል።ማሲንቆውን ሲመታ ከቤት እንዳይወጣ መሬቱን በፊት እግሩ ረገጥ ረገጥ እያደረገ ቤቱን ይቆጣጠራል።ወንዱ አዝማሪ እየተጫወተ ትንሽ እንደቆየ ሞቅ ሲል ተረኛዋ ሴት አዝ

ማሪዋ ትተካለች።እሱ ማሲንቆ እየተጫወተ ባለ ከበሮው በሁለት ትንንሽ ዱላዎች ከበሮን እየመታ ይከውናሉ።ከዚያም የሁሉም ባህላዊ መሳሪያዎች ቅንብር በደንብ ሲስተካከል ከሴቷ አዝማሪ ጋር በአንድነት ወይም ጥንድ ሆነው ከወንዱ አዝማሪ ጋር መዝፈን ይጀምራሉ። እንዲህ እያለ በተናጠል እና ጥንድ በመሆን እሷ ስታበቃ እሱ እየተተካኩ ሲዘፍኑ ከቆዩ በኋላ በቅብብል ደግሞ መዝፈን ይጀምራሉ።በዚህ ጊዜ የአሽሙር ቃል ግጥምን በዜማ እየተ መላለሱ እንዲሁም ሴቷ ቃል ግጥሙን በንግግር ስታቀብለው እሱ ያንን ቃል ግጥም በዜማ እየተጫወተ በዚህ ሁኔታ እየከወኑ ይቆያሉ።

በዚህ ክወና ወቅት ቃል ግጥሙን ትተው በመሀል በመሀል የተለያየ የብሄር ዘፈኖችን ይዘፍ ናሉ።በዚህ ጊዜ ሌሎቹ ተተኪ አዝማሪዎች እና ሴቷ እስክስታ እየመቱ የበለጠ ያደምቁ ታል።ሙዚቃው ደምቆ እስክስታው ሲመታ ከመሰንቆው እና ከከበሮው ጋር ጥሩንባ አብሮ ከእነዚህ የሙዚቃ መሳሪያዎች ጋር ተዋህዶ ይነፋል።እኔ በነበርኩበት ሰአት ጥሩንባ ስትነፋ ያየኋት ሴት ነበረች።በመቀጠልም ወደ ቃል ግጥማቸው በመመለስ ቅድም ያንን ዘፈን እየተ ጫወቱ በአይናቸው ሲቃኙት እና በጆሮአቸው ሲያዳምጡት በቆዩት ታዳሚ ላይ ቃል ግጥም መግጠም ይጀምራሉ።በዚህ ጊዜ ከነሱ ቃል ግጥም ባሻገር ተቀበል እየተባሉ ከታዳሚው ቃል ግጥም እየተቀበሉ ይገጥማሉ።

አዝማሪያኑ ከታዳሚው የተቀበሉት ቃል ግጥም ልክ ከሆነ በቀጥታ ይገጥሙታል።ነገር ግን ካልገጠመላቸው ራሳቸው አስተካክለው አሻሽለው ይገጥሙታል።በዚህ አይነት ታዳሚውን እያሳቁ፣እያዝናኑ እና እየተሸለሙ ከቆዩ በኋላ በአንድነት ደግሞ የሌላ አገር ዘፈን ሲዘፍኑ ይቆያሉ።ከዚያም ተረኛ አዝማሪ ቦታውን ይይዛል።እነሱም አብረው እያጨበጨቡ ታዳሚውን ሲመለከቱ፣ሲያጠኑ፣ቃል ግጥም ሲያመቻቹና ሲፈጥሩ ይቆያሉ።እየከወኑ ያሉት አዝማሪዎች የእረፍት ጊዜ ሲደርስ ሴቷ በዘፈን ጀምራ ወደ ታዳሚው በመዞር ቃል ግጥም መግጠም ትጀ ምራለች።ቃል ግጥም በሚገጥሙበት ጊዜ ከቃላት ጀምሮ እስከ ስንኝ ድረስ በመደጋገም አድ ማጩ ለመልእክቱ ትኩረት እንዲሰጥ ለማድረግ እና አፅንኦት ለመስጠት ይጠቀሙበታል። በዚህ መልኩ ሌላኛው ተተኪ ተረኛ እየገባ ከሁለት ሰአት የጀመረ ክወና እስከ ሌሊቱ ስም ንት ሰአት ድረስ ቆይቶ ይጠናቀቃል።አዝማሪዎቹ ዘፈን፣ቃል ግጥም ሲከውኑ ታዳሚው የሚጠጣ መጠጥ (ቢራ፣ለስላሳ…) የሚበላ ምግብ እየተመገበ፣ሞቅ ሲለው እየጨፈረ፣በተገጠ መበት ቃል ግጥም እየሳቀ፣እራሱም ቃል ግጥም ተቀበል እያለ እየሰጠ ይቆያል።በዚህ ባህል ምሽት ቤት ውስጥ ወጣት፣አዋቂዎች፣ፈረንጆች፣ወንድ እና ሴት ሰዎች ይመጣሉ።

ቤቱን ባህላዊ ለማድረግ ጣራው ላይ ሳር ለብሷል፣የውስጡ ግድግዳ በሰሌን ተለብጧል፣ኮርኒሱ በሳጠራ ተደርጎ ቆዳ ተለጥፎበታል፣ልክ እንደ ጌጥ ከሰሌን የተሰራ ባርኔጣ፣ሰፌት፣አገልግል እና ጭራ ተሰቅሏል።መቀመጫው አግዳሚ ወንበር እና በቆዳ የተሸፈነ ባርጩማ ነው።ወለሉ ጥለት ባለው የጥጥ ጨርቅ መጋረጃ ተጋርዷል።ወቅቱ ገና አከባቢ ስለነበር የገና ዘፍ ውስጡ አለ።አዝማሪዎቹ የሚለብሱት የአበሻ ቀሚስ ወይም የአንድን ብሄር የሚገልጥ ባህላዊ ልብስ ነው።እንዲሁም ባህላዊ ጫማ፣ዱላና ጋቢ ነገር ይለብሳሉ።ፀጉራቸውን የሚሰሩት የሚለብሱትን ሀገር ልብስ የሚገልፅ ሹሩባ ነው።

ከላይ በዘረዘርኩት ክዋኔ መሰረት ከዚህ በታች ከአዝማሪ ወርቁ ታዬ በባህል ምሽት ቤት ሲከ ውን ከሰበሰኳቸው ቃል ግጥሞች መካከል በይዘታቸው ጎላ ብለው የሚታዩትን በመምረጥ ለመተንተን እሞክራለሁ።በምእራፍ ሁለት ቲወሪ ላይ የአውዱ ሁኔታ በተለያየ ምክንያት እን ደሚለያይ አንስቻለሁ።ስለዚህ የቃል ግጥም ይዘት የተለያየ እንደመሆኑ የሚከወንበትም አውድ እንዲሁ ይለያያል።ማለትም በሙገሳ እና በፉከራ ጊዜ ያለዉ ክዋኔ፣ፋይዳ እና አው ዳዊ ድባብ የተለያየ ነው።በመሆኑም ቃል ግጥሞቹ ሲከወኑ የሚኖራቸውን አውድ ከላይ ካነሳሁት አጠቃላይ አውዳዊ ክዋኔ የሚለይበት ሲኖር ቃል ግጥሞቹን ስተነትን የማሳይ ይሆናል።

## ሀ.የፉከራ ቃል ግጥሞች

አዝማሪው ከዚህ በታች የምናገኛቸውን አራት መንቶ ግጥሞችን ማንነትን ለመግለፅ እና ለማወደስ የሚገጥማቸው ሲሆን ቃል ግጥሞቹን ፈጥሮ እና አሻሽሎ የገጠማቸው ናቸው። ወደ ትንታኔ ከመግባቴ በፊት ቃል ግጥሞቹን ላንሳ-

[2]መንቶ 01 ኸረ አብዬ ኸረ አብዬ
አትበለኝ ችላ ያንተ ደም መላሽ እኔ ነኝና

መንቶ 02 ኸረ ዳኘዬ የሰደድ እንጨት
እባብ ልብ እንጂ የለውም አንጀት

መንቶ 03 የግሸ አባይ ልጅ የእረኛው ምላ
ያርበደብዳል ገና ሲነሳ

መንቶ 04 የሰሌ ወንድም የእንቆቆ ፍሬ
ልቡ ድፍን ነው እንደ ጥጥ ፈሬ

እነዚህ አራት መንቶዎች እና በዚህ ርእስ ስር በአባሪ ውስጥ የምናገኛቸው ቃል ግጥሞች በሚከወኑበት ወቅት ታደሚው ከነበረው ሁኔታ ጋር ተዳምሮ የዚያን ማህበረሰብ ማንነት በተወሰነ ለማወቅ ያስችላል።ምክንያቱም የቃል ግጥሞቹን የተለያየ ፍቺን ስንመለከት የመጀ መሪያው መንቶ አባቱን ለምን ጣል ጣል ታደርገኛለህ።ልጅህ ደም መላሽ እኮ ነኝ እያለ የሚ ለምን ሰው የሚያመላክተን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ያጠቃህን የምበቀልልህ፣የማጠቃልህ ልጅህ ነኝ የሚል ነው።

---

[2] መንቶ፣ሶስቶ...ወዘተ የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ዶክተር ፈቃደ አዘዘ ነው።መንቶ ማለት ሁለት ስንኝ ቃል ግጥሞች ማለት ነው።

ስለዚህ ጣል ጣል አታድርገኝ የሚል ሀሳብን የያዘ ነው።ምክንያቱም ደም መላሽ ማለት አን ድም የሰው ስም ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ተበቃይ፣ብድር መላሽ ማለት ነው። ይህ ማለት አንድ ሰው ሰውን ቢገድል የተገዳዩ ቤተሰብ እና ዘመድ ገዳዩን ወይም የገዳዩን አንዱን ቤተ ሰብ በመግደል ደማቸውን ይመልሳሉ።

ስለዚህ ይህ ቃል ግጥም የዚህን ማህበረሰብ ማንነት ያሳያል።የሁለተኛውም መንቶ ከዚሁ የብቀላ መንፈስና ስሜት ጋር የተያያዘ ነው።ምክንያቱም የመንቶውን ትርጉም ስናይ አንድም እባብ ልብ እንጂ አንጀት የሚባል የሰውነት ክፍል የለዉም ማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እባብ ለመንደፍ ካሰበ የሚያዝን አንጀት የለውም ማለት ነው። ይህም የሚያመክተው ልክ እንደ እዚህ እባብ ሁሉ ለጠላትህ ማዘን የለብህም ለማለት ነው።ለማጥቃት ለመበቀል በርታ፣አትፍራ፣አታፈግፍግ ማለት ነው።እባብ ማለት በልቡ የሚሳብ እንስሳ ነው።እባብ የሚወከለው በክፋት፣በተንኮል፣በድፍረት…ወዘተ እንደ መሆኑ በቃል ግጥሙ ውስጥ በውስጠ ታዋቂነት ልክ እንደ እባቡ ደፋር እና ጨካኝ እንዲሆን የእባቡን ባህሪ እንዲይዝ እና እንዲ ላበስ ሲገፋው ይታያል።ስለዚህም በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ የምሰላ ዘይቤን እናገኛለን ማለት ነው።ምክንያቱም ልክ እንደ እባቡ ሁን ምሰል የሚል ድምፀት ስላለው ነው።ይህ ቃል ግጥም የማህበረሰቡን ማንነት ከማንፀባረቁ ባሻገር ወኔን ለመቀስቀስም ያገለግላል።ሌላው በዚሁ ቃል ግጥም ውስጥ የምናገኘው የሰደድ እንጨት ማለት የበረሀ እንጨት ማለት ነው።በቃል ግጥ ሙም ውስጥ ሀይለኝነትን ለማሳየት የገባ ነው።

ሶስተኛውም መንቶ ከዚሁ ሀሳብ ጋር በተያያዘ መልኩ የግሽ አባይ ልጅ ገና ለግጥሚያ ሲነሳ ያስፈራል፣ያስደነግጣል፣ያሸብራል ማለት ነው።ይህንኑ ሀይለኛነቱን በበለጠ ለማሳየት የእረኛው ምሳ የሚል ቃል በግጥሙ ውስጥ እናገኛለን።ምክንያቱም እረኛ ምሳውን የሚበ ላው ውሎ በመሆኑ ይህም ጥንካሬውን፣ረሀብ የማይፈታው መሆኑንና ሀይለኛነቱን ያሳ ያል።ስለዚህ የግሽ አባዩ ልጅ ልክ እንደዚህ ነው ማለቱ ነው።ጀግና መሆኑን መግለፁ ነው።

በስተመጨረሻ የምናገኘው አራተኛው መንቶ የሚያወሳው ይህ በሶስቱ መንቶዎች ውስጥ የተ ነሳው ጀግና ልቡ ልክ እንደ ጥጥ ፍሬ ድፍን መሆኑን ያሳያል።ማለትም ልቡ ደንዳና ነዉ፣ አይፈራም፣ለአፍታ እንኳን ደንገጥ አይልም ማለት ነው።እንዲሁም በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ የምናገኘው የእንቆቆ ፍሬ ለኮሶ በሽታ ለመድሀኒትነት የሚጠጣ በፈዋሽነቱ ፍቱን የሆነ የፍሬ አይነት ነው።ስለዚህ ይህንንም ፍሬ በቃል ግጥሙ ውስጥ በማምጣት ሀይለኝነ ቱን በበለጠ በማሳየት ለማጠናከር ነው።ስለዚህ በንድፈ ሀሳቡ(ቲወሪ)ላይ እንዳነሳሁት ቃል

ግጥሞቹን ይዘን መልእክታቸውን፣ክወኔውን እና ፋይዳውን በምንተርክበት ወቅት ከቃል ግጥሞቹ ትርጉም በተጨማሪ ስለ አዝማሪው እና ስለ ማህበረሰቡ ማንነት፣ይህ ማህበረሰብ እኔ እንዲህ ነኝ ሲል ሌላውን የሚያይበትን አተያይ መመልከት ያስችለናል።በተጨማ ሪም የማህበረሰቡንም የአኗኗር እሴት፣ባህል፣አስተሳሰብ፣አመለካከት እና የእውቀት ደረጃ ለማወቅ ይረዳናል።

እንዲሁም የዚህን ማህበረሰብ ሀይለኛነትን ለመግለጽ፣የሚጠቀማቸውን ውክልናዎች እና ነገሮችን የሚመስሉባቸውን ተምሳሌቶች፣ማህበረሰቡ ከነዚህ ውክልናዎች ጋር ያለውን ትስስር ያሳያል።ከዚህም ባሻገር ይህ ማህበረሰብ በፊት ከአባቶቹ የወረሰው የተበቃይነት ስሜት እስከ አሁን ድረስ ርዝራዡ ያልጠፋ ነገር መሆኑን ያሳየናል።በተጨማሪም ስለ ፈሪ ያለውን አተያይ በተረኩ አማካኝነት ለማየት እንችላለን።

አዝማሪው እነዚህን ቃል ግጥሞች ሲገጠም የተመለከትኩት በዳሞት የባህል ምሽት ቤት ውስጥ ሲሆን ቃል ግጥሙን የተገጠመው የተለያየ የብሄሰሰብ ዘፈን እና ጭፈራ ከተካሄደ በኋላ ነበር።ይህ ቃል ግጥም የሚገጠመው በወንዱ አዝማሪ ሲሆን በመጀመሪያ ያለምንም የሙዚቃ መሳሪያ ጎራዴ ይዞ ሲፈክር ይቆይና በመሀል በመሀል ቁርጥ ቁርጥ በሚል ዜማ በከበሮ እና በማስንቆ እየታጀበ ፉከራውን ይቀጥላል።በዚህ ጊዜ ከዋኙ ባህላዊ ልብስ ለብሶ ነበር።ታዳሚው የብሄርረሰብ ዘፈን ላይ ከነበረው ተሳትፎ በበለጠ ሁኔታ እና ላቅ ባለ ስሜት ሙሉ ጆሮውን ሰጥቶ አንዳንዱ ሳይታወቀው በስሜት እየጮኸ አንዳንዱ እያጨበጨበ አንዳ ንዱ ደግሞ ተቀምጦ ያዳምጥ ነበር።

## ሊ.ስለ አባይ ግድብ የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

ቀጥሎ የቀረቡት ቃል ግጥሞች ደግሞ ሁሉም የሚያወሱት ስለ አባይ ወንዝ ነው።አዝማሪ ው በአሁን ሰአት አንገብጋቢ በሆነው ጉዳይ ላይ ተመስርቶ በመፍጠር እና ከታዳሚው ዘንድ ተቀበል ተብሎ በማሻሻል የገጠማቸው ቃል ግጥሞች ናቸው።

መንቶ 01 የውጩ ካንፓኒ እንግዲህ ለምናችን
አባይ ተገድቧል የጀርባ አጥንታችን

መንቶ 02 ኸረ አባይ ወርቁ ኸረ አባይ ወርቁ አለም ዞሮ እንደገና
አባይ ወንዛችን የኛማ የኢትዮጵያ ቀለበት ነውና።

መንቶ 03 ኸረ እንደምን አለህ ከማገኘው ገንዘብ አምስት አስር ብዬ
ቦንዱን እገዛለሁ ለግድቡ ብዬ።

ሁሉም መንቶዎች የሚያወሱትም ሆነ የመገጠማቸው ምክንያት ከላይ እንዳነሳሁት የአባይ ግድብ ነው።የመንቶዎቹን ትርጉም ስንመለከት በመጀመሪያው መንቶ ውስጥ ያለው የጀርባ አጥንታችን የሚለው ቃል ሁለት ትርጉም አለው።የቃል ግጥሙ ቀጥተኛ ትርጉም የአባይ ወንዝ የጀርባ አጥንታችን ነው የሚል ሲሆን ውስጣዊ ትርጉሙ ደግሞ የአባይ ወንዝ ግድብ ሲገደብ አገራችን ከግድቡ በምታገኘው ገንዘብ ታድጋለች።ስለዚህ የእኛ የዜጎቿም ኑሮ አብሮ ይለወጣል።በመሆኑም ከዚህ በኋላ የሰው አገር እርዳታ አያስፈልገንም የሚደግፈን አባይን አግኝተናል የሚል ነው።

ሁለተኛው መንቶ ደግሞ የአባይ ወንዝ ረጅም በመሆኑ ብዙ ሀገራትን ያካልላል።እንዲሁም የኢትዮጵያን ሀገር በመክበቡ ለዚች ሀገር ቀለበት እና ጌጥዋም ጭምር ነው የሚል ነው። ወርቅ የከበረ ድንጋይ ነው።አባይ ወርቁ ማለት የወንዙን ጠቃሚነት፣ክብርና ውድነት አመላካች ነው።በጠቃላይ ትርጉሙ ይህ በወርቅ የተመሰለው የአባይ ወንዝ እስከ ዛሬ ያልተጠቀምንበት ቢሆንም የኛ ስለሆነ ተመልሶ ለሀገሩ ጥቅም ሊውል ነው የሚል ነው።እናም በእነ ዚህ ሁለት መንቶዎች ውስጥ በተለያየ መልኩ የተገለጠው የአባይ ወንዝ እንዲገደብ ከማገኘው ገቢ አጠራቅሜ ቦንድ በመግዛት የግድቡን ግንባታ አግዛለሁ የሚል ሀሳብ በሶስተኛው መንቶ ውስጥ እናገኛለን።

በአንድ እና ሁለት መንቶዎች ውስጥ የአባይ ወንዝ በጀርባ አጥንት፣በቀለበት እና በወርቅ ሲመሰል ሲለወጥ እናያለን።ይህ ደግሞ የምስያ እና ለዋጭ ዘይቤ በውስጡ እናገኘለን ማለት ነው።ቃል ግጥሞቹ በሚከወኑበት እና በሚተረኩበት ጊዜ በዚህ ወንዝ ታኮ ስለ ማህበረሰ ሰቡ የኢኮኖሚ ዝቀተኛነት እና ከድህነት ጋር በተያያዘ ስለ ውጭ እርዳታ ያሳየናል።እነ ዚህ ቃል ግጥሞች ትኩረት ስለ አባይ ቢሆንም ዋናው ጉዳይ ግን ማህበረሰቡን ከድህነት አረንቋ የማላቀቅ ተግባር ይመስለኛል።ስለዚህ የማህበረሰቡን ማንነት፣የአኗኗር እሴት፣ ነገሮችን ለመግለጽ የሚጠቀሟቸውን ውክልናዎች፣ማህበረሰቡ ከነዚህ ውክልናዎች ጋር ያለውን ተዛምዶ፣ቦንዱን እንዲገዙ የመቀስቀስ እና የማዝናናት ፋይዳ አለው።

ቃል ግጥሙ የተከወነው በዳሞት ባህል ምሽት ቤት ውስጥ ሙዚቃዊ ቃናን ተላብሶ በማሲንቆና በከበሮ ታጅቦ ነው።እንዲሁም ልክ እንደ ፉከራው ታዳሚው በሌላ ዘፈን፣በመጠጥ… ሞቅ ሲል ነበር ተከወነው።በሚከወንበት ሰአትም ከላይ ካለው የፉከራ ቃል ግጥም አውድ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አውድ ነበረዉ።

## ሐ.የሙገሳ ቃል ግጥሞች

አዝማሪው ከዚህ በታች በቀረቡት ቃል ግጥሞች አማካኝነት ታዳሚዎችን ያሞግሳል፣ያሞካሻል።የመጀመሪያው ቃል ግጥም በፊትም በሌሎች አዝማሪያን ዘንድ ሲባል የነበረ በአሁን ሰአትም ይህ አዝማሪ ለአውዱ በሚስማማበት ጊዜ አስታውሶ የገጠመው ነው።ሁለተኛው ቃል ግጥም ግን ፈጥሮ የገጠመው ቃል ግጥም ነው።ሁለቱም ቃል ግጥሞች ደጋግመን በምናነባቸው ሰአት ትርጉማቸው የተለያየ ፍቺን የያዘ መሆኑን እንረዳለን።ከመተንተኔ በፊት ቃል ግጥሞቹን ላንሳ-

መንቶ 01 እዩአት የአንገቷን ስራስር
የበላይ ዘለቀ ልጅ የምትመስል፡፡

መንቶ 02 ከፈረንሳይ ሽቶ ከእንግሊዝ ወተት
በቃ ተከተተ ካንቺ ወዲያ ሴት፡፡

እነዚህ መንቶዎች የተገጠሙት ቆንጆ ሴትን ለሚመለከት ነው፡፡የመጀመሪያው መንቶ የአንገት እርዝማኔ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ምክንያቱም የበላይ ዘለቀ ልጅ አንገት ውበት የተመሰገነ ነው፡፡እናም ይህቺ ልጅ ከበላይ ዘለቀ ልጅ ጋር ትመሳሰላለች ማለት ነው።ስለዚህ አንገተ መልካም ነሽ ማለት ነው፡፡መቃ አንገት እንደሚባለው ማለት ነው።ሌላው ትርጉሙ ግን ቁንጅናን ለመግለፅ ነው።በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ የበላይ ዘለቀ ልጅ እና ልጅቷ የማመሳሰል ሁኔታ እናያለን።ይህም የምሰላ ዘይቤ ሲሆን በግጥሙ ውስጥ በጣም ቆንጆ መሆኗን ለማሳየት የገባ ነው።እንዲሁም ጥንትነትን የሚያሳይ ኀቡር ጠቃሽ ሀረግ በቃል ግጥሙ ውስጥ እናገኛለን።ይህም በላይ ዘለቀ የሚል ስም ነው።በላይ ዘለቀ በሀይለ ስላሴ ዘመን በጎጃም ክፍለ ሀገር የነበረ ጀግና ተዋጊ ሲሆን ታዋቂ ስም በመሆኑ ስሙ ሲነሳ ወደ ኋላ እንድናስብ ያደርገናል።

ሁለተኛውም መንቶ ልክ እንደ መጀመሪያው መንቶ ካንቺ ውጭ ቆንጆ ሴት የለም።ስለዚህ ሌላ ሴት አልፈልግም ማለት ነው።በዚህ በሁለተኛው መንቶ ውስጥ አነፃፃሪ እና ተምሳሌት ዘይቤን በመጠቀም የልጅቷን ውበት ቁንጅናን ለማሳየት ተወዳጅና ታዋቂ ከሆነው የፈረንሳይ ሽቶ እና ከእንግሊዝ ወተት ጋር ሲያወዳድራት እና ሲያመሳስላት ያሳየናል፡፡ቃል ግጥሞቹ ሲከወኑ ሲተረኩ ማህበረሰቡ ውበትን እና ቁንጅናን የሚመስልበትን ወይም የሚተካበት መንገድ ይታያል።

የዚህ ቃል ግጥም አውዳዊ ክዋኔ ከላይ የተነሱት ቃል ግጥሞች ውስጥ የተነሳው የሙዚቃ መሳሪያ፣ቁሱ…ወዘተ በተመሳሳይ ነበር።ነገር ግን የታዳሚው ሁኔታ የተለየ ነበር።ቃል ግጥሙ የተገጠመላት ልጅ እና አብረዋት የነበሩት ጓደኞቿ በቃል ግጥሙ ሙገሳ ደስታቸ ውን በመጮህ እና እጃቸውን በማውለብለብ ይገልፁ ነበር።

ቃል ግጥሞቹ መገጠማቸው እና አውዱ መፈጠሩ ታዳሚውን ለማሞገስ፣ለማድነቅ፣ለማዝና ናት ይጠቅማል።እንዲሁም ይህ ባህላዊ አውድ መከወኑና መቀረኑ የማህበረሰቡን ባህል ለማሳየትም ሆነ ለማሳደግ ትልቅ የሆነ የራሱ ድርሻ አለዉ።ከዚህ በተጨማሪም መልካም ምኞትን የተላበሰ በመሆኑ ከታዳሚው እና ከተገጠመላት ዘንድ ጭብጨባ ሳቅ እና ሽልማት አብሮ ይገባል፡፡

## ሠ.የፍቅር ቃል ግጥሞች

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ቃል ግጥሞች አዝማሪው ፍቅርን ለመግለፅ የሚጠቀምባቸው ሲሆን ሁለቱም ተደጋግመው ሲነበቡ የተለያየ ፍቺን የያዙ ቃል ግጥሞች ናቸው።ቃል ግጥሞቹን በማስታወስ የገጠማቸው ናቸው።እንዴት እንዳስታወሰው ከታች ቃል ግጥሙን ስተነትን የማመላከት ይሆናል።

ሶስቶ 01 ምነው ባደረገኝ የደጇን ገለባ
ምነው ባደረገኝ የደጇን ገለባ
ወደ ቤት ስትገባ ይዛኝ እንድትገባ

መንቶ 01 ከዚህ ተቀምጬ እስላም አንገቴን
ማተቤን ሸዋ ላይ ማን አስሮት ይሆን፡፡

የእነዚህ ቃል ግጥሞች የመገጠሚያ ምክንያት የፍቅር ጉዳይ ነው፡፡የመጀመሪያው ቃል ግጥም በኛ ሀገር ገለባ ለማገዶነት የሚያገለግል በመሆኑ ሴቷ ተመልክታው ትታው አትሄ ድም።ስለዚህ ከሷ ጋር ለመሆን ገለባ በሆንኩ የሚል እንድምታ ነው ያለው።ከዚህም በተጨ ማሪ የወደዳት ወዳጇ ከሷ ጋር አብሮ ለመሆን ለመጫወት የመፈለጉን ምኞት ነው የምናየው በሰውየው ምኞት ውስጥ መምሰልን፣መፈለግን እና መለወጥን እንመለከታለን።ስለዚህ በቃል ግጥሙ ውስጥ የምሰላ እና ተለዋጭ ዘይቤ አለ ማለት ነው፡፡ምክንያቱም ሰውየው እየደጋገመ ምነው ባደረገኝ የደጇን ገለባ ይላል።

እሱ ተለውጦ ሰው መሆኑ ቀርቶ ወደ ገለባነት መቀየር ሲፈልግ ይታያል፡፡እንዲሁም"ምነው ባደረገኝ የደጇን ገለባ" የሚለው ቃል ተደጋግሞ በመምጣቱ እንድም ገጣሚው የሚቀጥለውን

ስንኝ ለማስታወስ ወይም ለመፍጠር ይጠቀምበታል።ማለትም ገጣሚው ያንኑ ስንኝ እየደጋ ገመ በማለት ከዚህ ቀጥሎ የሚቀኘውን ተከታይ ስንኝ ያሰላስልበታል ያቀናጅበታል።እን ዲሁም የሰውየውን ፍላጎት አፅንኦት ለመስጠት እና መልእክቱን በሚገባ ለማስረፅ ይጠቅ ማል፡፡

ሁለተኛው መንቶውም ቢሆን እንደ መጀመሪያው ቃል ግጥም በፍቅር ላይ ተመስርቶ የተገ ጠመ ሲሆን ከታሪክ ጋር የተያያዘ ቃል ግጥም ነው፡፡ታሪኩ እንዲህ ነው።የደብረ ታቦር ንጉስ ወደ አዲስ አበባ ሄደው ይቆያሉ፡፡አዝማሪዋ ንጉሱ ለምን እንደቆዩ ስላወቀች ወደ ንጉሱ ሚስት ዘንድ ትሄዳለች፡፡ከዚያም ስትገጥም ይህንን ቃል ግጥም ተቀኘች፡፡የንጉስ ሚስትም ፅፋ ያቺን ወረቀት ለንጉሱ ትልካለች፡፡ከዚያ ያች ወረቀት አዲስ አበባ ንጉስ ዘንድ ትረድሳ ለች።ማህተሜን ሸዋ ላይ ማን አስሮት ይሆን የሚለው፡፡ታዲያ ያች ወረቀት ንጉሱ ስትደርሳ ቸው በቶሎ ወደ ደብረ ታቦር ይመለሳሉ፡፡ከዚያም ያችን አዝማሪ ካለችበት አምጡልኝ ብለው ቅኔው ገብቷቸው ስለ ነበር ፈረስ ከነኮርቻው ሸለሟት ይባላል፡፡ይህ ታሪክ የተተረከው ቃል ግጥሙ በፊት ሲገጠም የተገጠመበትን ምክንያት ለመንገር ሲሆን አሁንም ይህ ቃል ግጥም ከአውዱ ጋር ሲስማማ ታውሶ ይደገማል፡፡

በዚህም ገጣሚዎች እያስታወሱ ከአውዱ ጋር በማስማማት እንደሚጠቀሙበት ያመላክተናል ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል አማካኝነት እየተከወነ እየተደገመ ይተላለፋል።የቃል ግጥሙ ቀጥተኛ መልእክት አንገቴ ያለ ማህተብ ባዶ ሆነ ማህተቤን ማን ወሰደብኝ ማለት ነው።እዚህ ቃል ግጥም ውስጥ ህብር አለ ይፈከራል፡፡ማተህቤ የሚለው ቃል ትርጉም አለ ው፡፡ማህተብ ክርስትናን ለመግለፅ የገባ ትእምርታዊ ቃል ነው።ሀይሞኖትን ማሳያ መግለጫ ነው፡፡ስለሆነም ሙስሊሙ እና ክርስቲያኑን እንደ መለያነት ያገለግላል፡፡ይህን ልዩነት ለማሳየ የት በቃል ግጥሙ ውስጥ ክርስትናን ማሳያ የሆነው ማህተብ እና እስልምና የሚሉ በጥንድ ነት ተቃራኒ ነገሮች ገብተዋል፡፡ሌላው እኔ እዚህ ተቀምጬ ሙስሊሙ አረደኝ የሚል አንድ ምታም ያለው ይመስለኛል፡፡ዋናው ትርጉም ግን አንቺ እዚህ ተቀምጠሽ ባልሽ ባለበት ቦታ ሌላ ሴት ለምዶ ቀረ ማለቱ ነው፡፡ስለዚህ ለዋጭ ዘይቤን በመጠቀም ባልን በማህተብ መተ ካት ሁኔታ ይታያል።ሁለተኛው መንቶ የተገጠመው በቃል በንግግር መልክ ነው፡፡

አንደኛው ቃል ግጥም ግን የተገጠመው በዳሞት ባህል ምሽት ቤት ውስጥ ነበር።ይህ ቃል ግጥም ክዋኔ እና አውድ ለየት የሚያደርገው የታዳሚው ምላሽ ነው።ይኸውም ሳቅንና ሆሆታ ነበር፡፡በንድፈ ሀሳቡ ላይ እንደተነሳው ይህ ክዋኔ መከወኑ ታሪኩም መተረኩ አው ዱም መፈጠሩ ማንነትን፣ልዩነትን፣እምነትን፣በበፊት ነገስታት ዘንድ የነበረውን ከሚስት

ውጭ ቅምጥ የመያዝ ሁኔታ እንዲታይ እና እንዲጎላ አድርጎታል።ከዚህም በተጨማሪ ታዳሚን ለማዝናናት እና ሚስጥርን ለመንገር ያገለግላል።

## ሠ.ምክራዊ ቃል ግጥሞች

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው ቃል ግጥም ደግሞ አዝማሪው በማሻሻል ወይም ለአውዱ ሲመቸው በቀጥታ በመድገም የከወነው ነው።

መንቶ 01 ምን ያረግልሀል ሱፍ ለባሽ ቢበዛ
እንደምንም ብለህ ወታደርህን አብዛ።

ይህ ቃል ግጥምም አሁን እየተደገመ ቢገጠምም መደገሙ የራሱ የሆነ ታሪክ አለው።ታሪኩ ከቃል ግጥሙ ጋር መተንተኑ የቃል ግጥሙን መልእክት የበለጠ ስለሚያጎላው ታሪኩን ቀጥዬ ለመተረክ እሞክራለሁ።አጤ ሀይለ ስላሴ ግብር ሲያበሉ ሱፍ ለባሽ ቁጭ ብሎ ቁርጥ ይበላል ጠጁን ይጠጣል።ወታደር ግን ይጠብቃል።በዚህ ጊዜ ነው አዝማሪው ይህንን ቃል ግጥም የተቀኘው።ንጉሱ ትርጉሙ ገባቸው።አሁን ይህ ሱፍ ለባሽ እንዴት እንዲህ ይለናል ሲል ወታደር እስቲ በል ወንድ ትነካዋለህ ይላል።በዚህ ጊዜ ንጉሱ ሰላሳ ጠገራ ብር ሰጥተው ነገ ና ብለው ይሸኙታል።እሱም ሊገለኝ አይደል ይልና ቀረ ይባላል።

የቃል ግጥሙ ትርጉም የሱፍ ጨርቅ የለበሰ ሰው ምን ይሰራልሀል የሚል ሲሆን ሌላው ትርጉሙ ግን ባለሥልጣን የሆነ ሰው ዙሪያህን ቢከብህ ምን ያደርግልሀል።ይልቁስ ችግር ሲፈጠር ከአደጋ የሚታደግህን ወታደር ብታበዛ ብታበላው ይሻላል የሚል ነው።ይህ ቃል ግጥም እንዲገጠም መነሻው በምእራፍ ሁለት በንድፈ ሀሳቡ ውስጥ እንደተገለጸው አዝማ ሪው የህይወት ታሪኩን በሚተርክበት ወቅት እንደ አስፈላጊነቱ ቃል ግጥምን አቀናጅቶ ይጠ ቅማል።ስለዚህ አዝማሪው ስለ ቅኔ ሲያወሳኝ በምሳሌነት ከህይወት ታሪኩ ጋር አቀናጅቶ የገ ጠመው ቃል ግጥም ነው።አስከትሎም አብዛኛው ታዳሚ ቅኔው ስለማይገባው ስንሰድበው ይስቃል ብሎኛል።ይህንንም ያሰኘው የአዝማሪ ቃል ግጥም ቅኔን ማወቅ የሚጠይቅበት ጊዜ አለ ለማለት ነው።ቃል ግጥሙ ሁለት ነገሮችን ሲያነፃፅር ይታያል።

ወታደር እና ሱፍ ለባሽን።ሱፍ ለባሽ የሚለው ጥንታዊ ስያሜ በመሆኑ ንቡር ጠቃሽ ነው። ሱፍ ለባሽ ማለት በጥንት ጊዜ ባለስልጣን ማለት ነው።በአሁን ሰአት ይህንን ስያሜ አንጠቀ ምበትም።ስለዚህ ስያሜው ወደ ኋላ መልሰን እንድናስብ ያደርገናል።ይህ ቃል ግጥም የተከወ ነው በቃል በንግግር መልክ ያለ ምንም ሙዚቃ መሳሪያ ነው።የመከወኑም ሆነ የመተረኩ

ምክንያት ሁሉንም ከመሰብሰብ የሚጠቅም የሚረባ ትንሽ ነገር በቂ መሆኑን ለማስተማር ነው።እንዲሁም የቃል ግጥሙ መገጠሚያ የሆነው ታሪክ መከወኑ እና መተረኩ በበፊት ነገስታት ዘንድ የነበረውን አስተዳደራዊ ሁኔታ እና የስራ ክፍፍል ለማወቅ ያስችለናል።

## ፈ.ስለ ባህል የተገጠመ ቃል ግጥም

ከዚህ በታች የቀረበው ቃል ግጥም በመመራመር ወይም በማስተዋል የተለያየ ፍቺ እንደ ያዘ እንገነዘባለን።ቃል ግጥሙ ከአዝማሪው ማንነት ጋር እጅጉን የተያያዘ ነው።ይህንን መንደ ርደሪያ መሰረት በማድረግ ወደ ቃል ግጥሙ ላምራ-

መንቶ 01 አለው አለውና አለው አለውና
በማሲንቆ ፀና

የቃል ግጥሙ መነሻ ለባህል ከመቆርቆር ስሜት የመነጨ ነው።የዚህን ቃል ግጥም መልእ ክት ከነበረው አውድ ጋር አዛምደን ስንመለከት ብሎ ብሎ ነገሩ በማሲንቆ መሳሪያ ፀና የሚል ሲሆን ወይራው ትርጉም ግን ብሎ ብሎ ባህላችን ለውጥ አመጣ አደገ ፀና ማለት ነው።በአሁኑ ሰአት ማህበረሰቡ ዘመናዊውን መሳሪያ እየጠላ እየተወ ባህላዊውን የሙዚቃ መሳሪያ ማሲንቆን እንደገና እየፈለገ መጣ ለማለት ነው።ይህን ገጣሚው ያለበት ምክንያት የባህር ዳር ከተማ ማህብረሰብ ለዚህ ሙያ ከበሬታን በመስጠት በብዛት ወደ ባህል ምሽት ቤት እየመጣ ሲዝናና በመመልከቱ ነው።በተጨማሪም ማህበረሰቡ ዘመናዊው አልጥም ሲለው ተመልሶ የራሱን መገለጫ ባህል ፈለገ የሚል ድምፀት ያለው ይመስለኛል።ተደጋግ መው የሚገኙት አለው አለውና የሚሉ ቃላት የተጓዘበትን እረጅም ጉዞ ያሳያሉ።እንደ ገደል ማሚቶም እየደጋገሙ ያስተጋባሉ።በዚህም እነዚህ ቃላት በሚከወኑበት ሰአት በሚደጋገሙ ጊዜ ታዳሚው ትኩረት ሰጥቶ እንዲያዳምጥ ይጋብዛሉ።

በቃል ግጥሙ ውስጥ የምናገኘው ጥንታዊ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ የባህሉን ስረ አመጣጥ ጥንትነትን ያሳያል።እዚህ ጋር የባህል ነገር ሲነሳ ዝማሪዎቹም ሆኑ ታዳሚዎቹ ሞቅ ባለ ሁኔታ ነው የሚከውኑት።ምክንያቱም ማህበረሰቡም ሆነ አዝማሪዎቹ የዚህ ባህል በለቤት ናቸው።ቃል ግጥሙ ካልተከወነ ካልተተረከ በስተቀር የማህበረሰቡ ፍላጎት ጉልቶ ሊታይ አይችልም።እንዲሁም ቃል ግጥሙ መከወኑ ለማዝናናት፣ማንነትን ለመግለፅ፤ባህልን ለማስ ትዋወቅ፣ለማሳደግ፤ለማስተማር እና የማህበረሰቡ መገለጫ የሆነውን ባህላዊ የሙዚቃ መሳ ሪያ ለማስተዋወቅ ይጠቅማል።

## ሲ.ፖለቲካዊ የጀግና ቃል ግጥም

አዝማሪው ከዚህ በታች የምናገኘውን ቃል ግጥም ለመተቸት ለማንኳሰስ ይጠቀምበታል። ቃል ግጥሙን ደጋግሞ በማንበብ ትርጉሙን ለመረዳት ይቻላል።

መንቶ 01 ያልተገራ ፈረስ ጠቅል እያላችሁ
ከትግሬ እየሮጠ ለንደን ገባላችሁ

የቃል ግጥሙ መነሻ ፍርሀትን ለማሳየት ነው፡፡የመንቶው ሁለት ትርጉም አለው።አንደኛው ጠቅል ብላችሁ በማእረግ ስም የምትጠሩት ያልሰለጠነው ፈረስ ከትግሬ አገር የሮጠ እንግ ሊዝ ዋና ከተማ ደረሰላችሁ የሚል ሲሆን ሁለተኛው ትርጉም ደግሞ ንጉስ ሀይለ ስላሴ ከጣሊያን ጋር በነበረው ጦርነት ምክንያት ወደ እንግሊዝ መሄድ ታሪክ መሰረት ያደረገ ነው ያልተገራ ፈረስ ማለት ለግልቢያ ያልሰለጠነ እና የሚደነብር ማለት ነው።ያልተገራ ፈረስ ሊጫንበት ቢባል እሺ አይልም ልጓም አይዘውም አስቸጋሪ ነው።ደንባራውን ፈሪውን እያሞ ገሳችሁ ያውላችሁ ጥሎ ሸሸ የሚል ድምፀት ያለው ይመስለኛል።ሀገራቱ በቃል ግጥሙ ውስጥ የገቡበት ምክንያት እርቀቱን በማሳየት የንጉሱን ድንጋጤ እና ፈሪነት መጠን ለማ መላከት ነዉ።

በመንቶው ውስጥ ንጉሱ ያልተገራ ፈረስ ሲሆኑ እናያለን፡፡ስለዚህ ለዋጭ ዘይቤ አለ ማለት ነው።ቃል ግጥሙ ለምን ተከወነ ብለን ስናስብ ለመቃወም ይገለገሉበታል።እንዲሁም ለዘለ ለፋ እና ለትችት ያገለግላል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ በግጥሙ ዉስጥ ጠቅል የሚል ስም እናገኛ ለን።ይህ ስም የንጉስ ሀይለ ስላሴ ስም ነው፡፡ጥንታዊ ስያሜ በመሆኑ ምክንያት ንቡር ጠቃሽ ቃል ነው።ወደ ኋላ ተመልሰን እንድናስብ ያደርገናል።ፈረሱ እና ንጉሱ ለመሮጥ የተነሱበትንም ሆነ የደረሱበትን እርቀት ለማሳየት የተሞከረው የድንጋጤውን መጠን ለማመላከት ቢሆንም ሰው ሊያደርገው የሚችል ነገር ባለመሆኑ ግነት ያለበት ይመስለኛል። ሲላው ይህ መንቶ በመከወኑ ታሪካዊ ፋይዳ አለው።

ምክንያቱም ታሪክን ከቃል ግጥሙ ጋር አጣቅሰን እንድናውቅ ያደርገናል።እንዲሁም ይህ ቃል ግጥም እና ታሪኩ መተረኩ ኢትዮጵያኖች በጣሊያኖች ቅኝ ግዛት ላለመያዝ ያደረጉትን ተጋድሎአዊ ፍልሚያ፣የኢትዮጵያኖችን ጀግንነት እና ማህበረሰበረሰቡ ለፈሪ ያለውን አተያይ ያሳየናል።ቃል ግጥሙ የተከወነው በቃለ መጠየቅ ጊዜ ስለነበር በዜማ ሳይሆን በንግግር መልክ ነው፡፡

ከዚህ በታች የምናገኛቸው ቃል ግጥሞች ደግሞ አዝማሪው በጥምቀት እና ሀይማኖታዊ አመታዊ በአላት ወቅት የሚከውናቸው ሲሆኑ አንዳንዶቹን ደግሞ ስራውን ለመጀመር ይገለገልባቸዋል።

> የጥምቀት በአል በጣም ሳቢ እና ማራኪ ነው።ይህ በዓል የተለያዩ ጭፈራዎች ዘፈኖችን…ወዘተ አካቶ የያዘ ክብረ በዓል ነው።ጥምቀት የክርስቶስን መጠመቅ ምክንያት በማድረግ የሚከበር በዓል ሲሆን አመታዊ በዓላት ደግሞ በዓመት አንድ ጊዜ የሚከበሩ በአላት ናቸው።(ጌቴ ገላዬ፤2000፤51)

ይህ አመታዊ በአል እና የጊዮርጊስ ሰባሩ ጥምቀት ልክ እንደ ጥምቀት ታቦት ወጥቶ የሚገባበት፣ዘፈኑ፣ዝማሬው ሁሉም በተመሳሳይ መልኩ የሚከወንበት ነው።ይህንን ክብረ በአል የባህርዳር ማህበረሰብ ሰባሩ ጥምቀት እያለ ይጠራዋል።በዚህ የጥምቀት ክብረ በአል እለት አዝማሪያኑ ጠዋት እንደማናቸውም ሰው በመገኘት ፀበል ይጠመቃሉ።ከዚያም ቃለ እግዚአብሄርን ሰምተው በመመለስ ባህላዊ ልብስ ለብሰው ታቦቱ ከመስቀል አደባባይ ወደ ቤተክርስቲያን ሲሸኝ ከታቦቱ ፊት ፊት በመሄድ ድማፃቸውን ዝቅ አድርገው በማሲንቆ በመታጀብ ዘለሰኛ እና መዲና ዝማሬ እየዘመሩ ታቦቱን ይሸኛሉ።

አዝማሪያኑ አንዳንንዴ ዘለሰኛ እና መዲና የሆነውን ዜማ ትተው መዘምራኑ የሚዘምሩትን ዜማ አብረው በማሲንቆ እያጀቡ ያዜማሉ።በመቀጠልም በመሀል በመሀል ዘለሰኛ እና መዲናውን ዜማ በመስንቆ ብቻ ይጫወቱታል።በዚህ ሁኔታ ታቦቱ ቤተክርስያኑን ዞሮ እስከሚገባ ድረስ ይከውናሉ።ከታዳሚው በአብዛኛው ባህላዊ ልብስ ለብሶ በክበሮ በማሲንቆ እና በጥሩንባ ታጅቦ ከዘማሪያኑ ጋር እያጨበጨበ፤እየሰገደ፤እያሸበሸበ፤እልል እያለ ታቦቱን ያጅባል።አንዳንዱ ታዳሚ ደግሞ ለብቻው ቡድን ፈጥሮ ክብ ሰርቶ ይዘምራል።የተወሰኑ ወንድ ወጣቶች ከታቦቱ ፊት ቀድመው እየሮጡ ለታቦቱ ምንጣፍ ያነጥፋሉ።ሴቶቹ በዘንባባ መሬቱን ይጠርጋሉ ሳር ይጎዘጉዛሉ።መዘምራኑ የመዘምራን ልብሳቸውን ለብሰው የሰንበት ተማሪዎች ደግሞ ባህላዊ ልብስ ለብሰው በቀኝ እና በስተ በግራ በመሆን በክበሮ ይዘምራሉ።በዛ ያሉ ሽማግሌዎች ጠበንጃ ይዘው ከፊት ከፊት ይሄዳሉ።በዚያ ቅዱስ ታቦቱ፤መስቀሉ እና ሙያተ ቅዱሳት አልባሳቱ ይገኛል።በዚህ ክብረ በአል፤ፈረንጆች(ቱሪስቶች)፤ሴት፤ወንድ፤የተማረ፤ያልተማረ እና ከልጅ እስከ አዋቂ ድረስ ይሳተፋል።

ከዚህ በፊት በባህል ምሽት ቤት ውስጥ ክዋኔ ላይ እንዳነሳሁት ከላይ ያነሳሁት አውድ አጠቃላይ ድባቡ ነው።በየቃል ግጥሙ ውስጥ የሚፈጠረው አውድ የተለያየ በመሆኑ ከአጠቃላይ አውዱ የሚለይበት ነገር ሲኖር ቃል ግጥሞቹን ስተነትን የማሳይ ይሆናል።

## ሀ.ስለ ምህረት የተገጠመ ቃል ግጥም

ከዚህ በታች የቀረበው ቃል ግጥም ማር በሚለው ቃል የተንሳ የተለያየ ፍቺ እንዲኖረው ሆኗል።አዝማሪው ከላይ እንዳነሳሁት ይህን ቃል ግጥም ለስራው መጀመሪያነት እና ለሀ ይማኖታዊ ክብረ በአላት ማጀቢያነት ያውለዋል።ስለ ቃል ግጥሙ ይህን መንደርደሪያ ከሰጠሁ ወደ ቃል ግጥሙ ላምራ-

መንቶ 01 እግዚአብሄር ጠጅ አይጠጣም ለጌትነቱ
ማር ብሎ አይልክም ወይ በገዛ ፍጥረቱ

አዝማሪው ይህን ቃል ግጥም በሀይማኖታዊ ክብረ በአላት ላይ ለታቦት ማጀቢያነት፣በሰርግ እና በምሽት ቤት ውስጥ ስራውን ለመጀመሪያነት ይጠቀምበታል።መንቶው ሁለት ፍቺ እን ዲኖረው ያደረገው "ማር" የሚለው ቃል ነው፡፡አንደኛው እግዚአብሔር ከማር የሚሰራውን ጠጅ አይጠጣም እንጂ የፈጠረውን ፍጥረት አምጣልኝ ማለት አላቃተውም ማለት ሲሆን ሌላው ትርጉሙ ደግሞ የሰው ልጆችን ሀጢያት በደምህ ገዝተህ ይቅር በል አሰርይ ብሎ እየ ሱስ ክርስቶስን አላከውም ወይ የሚል ነው፡፡የቃል ግጥሙ የመከወኑ ምክንያት የእግዚአብሔ ርን ሙሉነት፣ምህረት፣የበላይነት እና ይቅር ባይነት ለማሳየት የተገጠመ ነው፡፡እንዲሁም ሲከወን የአዝማሪውንም ሆነ የእምነቱን ተከታዮች እምነት ያሳያል።እንዲሁም ይህ እምነት እና ክብረ በአሉ በተከታዩ ትውልድ እንዲቀጥል ያደርጋል።

ስለዚህ እነዚህ አዝማሪያን እዚህ ቦታ ላይ ከበረከቱ ለመካፈል ብለው መገኘታቸው በአሉን ለማድመቅ ያግዛሉ።በተጨማሪም የጥንቱን ከአባት ወደ ልጅ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ወጥ የሆነውን ባህል እየከወኑ ለትውልድ ለማስተላለፍ ይረዳሉ።በመሆኑም ይህ ክዋኔ መከ ወኑ እና መተረኩ እግዚአብሔርን ለማመስገን ይጠቅማል፣የበአሉን የመከበሪያ ምክንያት ለማስታወስ ይረዳል።

ከዚህም በተጨማሪ ይህ ሀይማኖታዊ አውድ መፈጠሩ የአዝማሪዎችንም ሆነ የእምነቱ ተከታዮችን እምነት፣ከከበራው የሚያገኙትን ስነልቦናዊ ደስታ፣ለአምላካቸው የሚሰጡትን ክብር፣በዚህም ክብረ በአል አማካኝነት የተፈጠረውን ማህበራዊ ተራክቦ ለማየት ያስች ላል።

ይህ ቃል ግጥም ስለ ይቅርታ እየነገረን በዋናነት ግን የእግዚአብሔርን ሙሉነት የሚያሳይ ይመስለኛል።መንቶው በምሽት ቤት ውስጥ በሚገጠም ሰአት ታዳሚው በዝምታ ሲያዳምጥ ነው ያየሁት፡፡በክብረ በአል ቦታ ደግሞ ከላይ ስለ ሀይማኖታዊ ክብረ በአላት አጠቃላይ

አውዳዊ ክዋኔ ባነሳሁት መሰረት ይከወናል።ታቦቱን የሚሸኘው ምእመን ምላሽም ተመሳ ሳይ ነው።

## ለ.የውዳሴ ቃል ግጥሞች

ከዚህ በታች የምናገኛቸው ሁለት ተከታታይ ቃል ግጥሞች ከሌላው ቃል ግጥም የሚለዩት በአዝማሪው አለመገጠማቸው ነው።ማለትም በክብረ በአሉ ስፍራ ዘማሪያኑ የሚዘምሩትን አብሮ በማዜም የሚያጅብበት መሆኑ ነው።ስለዚህ ይህን መሰረት በማድረግ ወደ ቃል ግጥሞቹ ላምራ-

አራቶ 01 ስርአተ ሙሴ
ተቀደሰ በስመ ስላሴ
ፅናፅል ፅናፅል ፅናፅል ፅናፅል
የአሮን ባህል

ከላይ ለማንሳት እንደሞከርኩት አዝማሪው አንዳንዴ ዘለሰኛ እና መዲና የሆነውን ዜማ ትቶ መዘምራኑ የሚዘምሩትን አብሮ በማጀብ ያዜማል።የቃል ግጥሙ መልእክት የጥንቱ የሙሴ ህግ ባህል በአብ በወለድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተቀደሰ የተባረከ ነው ማለት ነው።ሥላሴ ማለት አብ ወ ወለድ ወ መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው።ፅናፅል የአሮን ባህል የሚለው ስንኝ ግን በመፅሀፍ ቅዱስ ካለው የአሮን ታሪክ ጋር የተለያየ ይመስለኛል።ማለትም አሮን ካህን እንጂ ዘማሪ አይደለም።እንዲሁም ስለዚህ ቃል ግጥም ከዶ.ር ስርግው ገላው ጋር ስንነጋገር እንደተረዳሁት የፅናፅል የሙዚቃ መሳሪያ በኢትዮጵያ እና በግብፅ የሚገኝ ባህላዊ የሙ ዚቃ መሳሪያ ነው።ስለዚህ በአሮን ይህ ባህል አልተጀመረም።እንዲሁም በቃል ግጥሙ ውስጥ ንቡር ጠቃሽ ሆነው ወደ ኋላ ተመልሰን እንድናስብ የሚያደርጉን ጥንታዊ ስያሜዎ ችን እና ቁስ እናገኛለን።እነርሱም ፅናፅል፣ሙሴ እና አሮን ናቸው።ሙሴ እና አሮን እስራላ ውያንን ከግብፅ ያወጡ በእግዚአብሄር የተመረጡ የእግዚአብሄር አገልጋይ ናቸው።ፅናፅል የሚሉ ቃላቶቹ መደጋገማቸው ባህሉ የተጀመረበትን ጥንትነት ለማሳየት ነው።ይህ ይህም እግዚአብሄርን ከማመስገን ባለፈ የአሮን ባህል የሚለው ሀረግ የሀይማኖቱን ስረ አመ ጣጡ ከአሮን ጀምሮ መምጣቱን የማሳየት የመንገር አንድምታ ያለው ይመስለኛል።

አውዳዊ ክዋኔው ከላይ ካለው ቃል ግጥም ክዋኔ የሚለየው ቃል ግጥሙ የተገጠመው በሀይ ማኖት ክብረ በአላት ብቻ መሆኑ ነው።ይህ ክዋኔ መከወኑ እና መተረኩ ይህንን የጥምቀት

ሀይማኖታዊ ክብረ በአል እየደገሙ ለትውልድ ለማስተላለፍ እና እግዚአብሔርን ለማመስገን ይጠቅማል።በዚህም የማይታየውን ማህበረሰቡን እምነት ጉልቶ እንዲታይ ይሆናል።

ሶስቶ 01 እንደምናነበው በወንጌል ተፅፎ
መንፈስ ቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ
በእርግብ ምሳሌ ክንፉን አሰደፎ

አዝማሪው ልክ ከላይ እንዳለው ዝማሬ በተመሳሳይ ሁኔታ አንዳንዴ ዘለሰኛ እና መዲና የሆ ነውን ዜማ ትቶ መዘምራኑ የሚዘምሩትን አብሮ በማለት ያዜማል።የቃል ግጥሙ መልእክት ወልድን(ክርስቶስ) በመጥምቁ ዮሀንስ በተጠመቀ ጊዜ አብ የምወደው ልጂ ይሄ ነው እርሱን ስሙት ሲል ከሰማይ መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ ላይ በእርግብ አምሳል ወረደ ይህም በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ተፅፎ ይገኛል፡፡የቃል ግጥሙ መነሻ የእየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጥ ምቁ ዮሀንስ አማካኝነት ሲጠመቅ የተፈጠረውን ሁኔታ ላይ በመመስረት ነው፡፡ስለዚህ ይህንን ምሳሌ እንከተል የሚል ድምፀት ያለው ይመስለኛል።ስለዚህም ነው በዚህ ክብረ በአል አማ ካኝነት ሰዎች በመጠመቅ ይህን ክርስቶስ ምሳሌ መከተላቸውን የሚያሳዩት።እርግብ ተም ሳሌትነቷ የሰላም ምልክት ነች፡፡በዚህ አውድ ውስጥ ግን መንፈስ ቅዱስን ወክላ ነው የተገኘ ችው።ሌላው ታዳሚ በተመሳሳይ ሁኔታ ከማሲንቆው ጋር በክብሮ በጥሩንባ ታጅቦ ከዘማሪያኑ ጋር እያጨበጨበ፣እየሰገደ፣እያሸበሸበ፣እልል እያለ ይህን የመሰለ አውድ ይፈጥራል፡፡ክበራው እና በዝማሬው አማካኝነት የሚተላለፈው መልእክት መተረኩ የእምነቱን ቀጣይነት ያፀናል፣ እምነትን ያስተምራል፣የስላሴን ሚስጥር ይገልጣል(በመንፈስ አንድ በአካል ሶስትነታቸውን) የዚ ህን ክብረ በአል ሚስጥር ይፈታል፡፡እንዲሁም በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን"ያመነ የተጠመቀ ይድናል"የሚለውን ቃል ያፀናል።

ሐ.ስለ ማዳን የተገጠመ ቃል ግጥም

በመቀጠልም የምናገኛቸው ሶስት ቃል ግጥሞች አዝማሪው ታቦትን ለማጀብ የሚከውናቸው ናቸው።ቃል ግጥሞቹ ህብራዊነት ያላቸው በመሆናቸው ምክንያት ከአንድ በላይ ፍቺን ይዘ ዋል።

መንቶ 01 ገልብጣ ልትጥለኝ የሄዋን መኪና
ማሪያም አዳነችኝ ፍሬን ያዘችና

አዝማሪው ይህን ቃል ግጥም በጥምቀት እና በአመታዊ ክብረ በአላት ላይ ለታቦት ማጀቢያ ነት የሚገለገልበት ነው።ቃል ግጥሙ ሁለት ፍቺ እንዲኖረው ያደረገው "ፍሬን" የሚለው ቃል ነው፡፡ሊተላለፍ የተፈለገው የቃል ግጥሙ ዋና መልእክት ያለው ውስጣዊ ትርጉሙ ላይ

ነው።ማለትም ፊት ለፊት የምናገኘው ትርጉም ሄዋን የምትባል ሰው መኪና ልትገጨኝ ስትል ማሪያም የመኪናውን ፍሬን ይዛ አዳነችኝ የሚል ሲሆን ለዚህ እውድ የሚሆነው ትር ጓሜው ግን ሄዋን አትብሉ ከተባለው የህይወት ፍሬ ቀጥፋ በመብላቷ ሞትን ሞተን ነበር። ነገር ግን ማርያም ክርስቶስን በመፀነሷና በመውለዷ ምክንያት ከሞት ዳንን የሚል ትርጉም አለው።በቃል ግጥሙ ውስጥ ሁለት ነገር ሲነፃፀር ማየት እንችላለን።ሞትን ያመጣ እና ህይወትን ያስገኘ ነገር እንመለከታለን።

ቃል ግጥሙ ሲል የፈለገው ዋና ጉዳይ በሄዋን ከገነት ተባረርን በማርያም ተመልሰን ገባን የሚል ነው።እዚህ ጋር ቃል ግጥሙ ውስጥ የገባችው መኪና ሊባል የፈለገውን ሀሳብ ለማሳያነት እንጂ በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ከማሪያምም ሆነ ከሄዋን ጋር ግንኙነት የላትም በዚህ ክብረ በአል ቦታ ያለው አውዳዊ ክዋኔ ከላይ እንዳለው ቃል ግጥም በተመሳሳይ መልኩ የሚከወን ነው።ይህ ክዋኔ መከወኑ ከጥምቀቱ ክብረ በአል ጋር በተያያዘ ስለ ማሪያም አደኝ ነት ለማስተማር ያገለግላል።እንዲሁም በንድፈ ሀሳቡ ላይ እንደተጠቀሰው ቃል ግጥሙ ሲከወን እና ሲተረክ የማይታየው የሰዎች እምነት ይታያል።በተጨማሪም ይህን የጥም ቀት ክብረ በአል ማሪያም እየሱስ ክርስቶስን ባትወልድ ኖሮ ባልኖረ ነበር የሚል ሀሳብ ያነገበ ይመስለኛል።

መ.ስለ ፆም የተገጠመ ቃል ግጥም

መንቶ 01 አወይ ሰው ግብዙ ስጋ እየተመኘ
የነፍሱ ጎዳና ተሸሮ ተገኘ

የዚህ መንቶ መልእክት "ተሸሮ" በምትለው ቃል የተነሳ የተለያ ፍቺ እንዲኖረው ሆኗል፡፡የመ ጀመሪያው ትርጉም ለስጋው ብሎ ስጋ ብቻ ይበላል።ነገር ግን ነፍስ የምትደሰተው ሽሮ እየ በላ ሲፆም ነው የሚል ሀሳብ ያለው ሲሆን ውስጣዊ ትርጉሙ ደግሞ የሰው ልጅ የሚያስ በው የሚደክመው ስለ ሚቀረው ስጋው ብቻ ነው።ስለ ነፍሱ አያስብም ለስጋው ብቻ ሲኖር ከነፍስ ጎዳና ላይ ጠፋ የሚል ሀሳብ አለው።የቃል ግጥሙ መነሻ ለስጋችን ብቻ መኖራችን ያብቃ ስለ ነፍሳችንም እናስብ የሚል ነው፡፡

አውዳዊ ክዋኔው እንደ ሌሎቹ ሀይማኖታዊ ክብረ በአላት በተመሳሳይ መልኩ የሚከወን ነው።ይህ ክዋኔ መከወኑ እና መተረኩ የተጠመቀው ጌታ ወደ እዚህ አለም የመምጣቱን ሚስጥር እንዲታወስ ያደርጋል፣እረቂቅ የሆነውን የሰው ልጆች እምነት ያጎላል፣ዘላለማዊ አለ

መሆናችንን ያሳየናል፣ስለ መፃም ያስተምራል።ስለዚህ ከዋኔው፣አውዱ እና ፋይዳው ቃል ግጥሙን ስንተርከ የሚታይ ይሆናል።

ሠ.ራስን ዝቅ ስለማድረግ የተገጠመ ቃል ግጥም

አራቶ 01 በየቀኑ ጥፋታችን
ሳያርግ ቀረ ፀሎታችን
ከኛ ዘንድ ፍቅር ስላነሰ
ቀራጩ ፀድቆ ተመለሰ

ይህንን ቃል ግጥም አዝማሪው የሀይማኖታዊ ክብረ በአላትን ለማጀቢያ የሚከውነው ሲሆን የቃል ግጥሙ መልእክት በኛ ሀጢያት የተነሳ ግብር አስከፋዩ ሰው ፀድቆ ተመለሰ የሚል ነው።በሌላ መልኩ ደግሞ በኛ ሀጢያት እና ፍቅር ማነስ የተነሳ ሀጢያተኛው ይቅር ተባለ የሚል ነው።የበለጠ ሀሳቡን ግልፅ ለማድረግ በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው የዚህ ታሪክ ሀሳብ በአጭሩ ላንሳ።

ቃል ግጥሙ የቀራጩ እና የፈሪሳዊውን ፀሎት ነው የሚመለከተው።ይህን ታሪክ በመፅ ሀፍ ቅዱስ ውስጥ ስናይ ስለ ፍቅር ማነስ ሳይሆን ስለ ራስን ማዋረድ ስለ ዝቅታ ነው የሚያወሳው።ማለትም ፀሎቱ ሳይሰማ የቀረው ፍቅር ስላነሰው ሳይሆን ይቅር በለኝ ከማ ለት ይልቅ ራሱን ከፍ አድርጎ እንደዚህ ቀራጭ ስላላደረከኝ አመሰግንሀለሁ በማለቱ ነው።ምክንያቱም ራሱን ከፍ የሚያደርግ ዝቅ ይላልና ራሱን ዝቅ የሚያድርግ ደግሞ ከፍ ይላልና።ቀራጩ ግን አይኑን እንኳን ወደ ሰማይ ሳያነሳ ደረቱን እየደቃ ይቅርታን ስለለመነ ይቅርታን አግኝቷል።

ከዋኔያዊ አውዱ ከአጠቃላይ አውዱ ጋር በተመሳሳይ መልክ እና ሁኔታ የሚከወን ሲሆን ይህ ሀይማኖታዊ ክብረ በአል የመከወኑ እና ቃል ግጥሙ የመተረኩ ምክንያት ራስን ዝቅ ስለማድረግ ለማስተማር፤ በዚያ ክብረ በአል ወቅት የሚከበረውን እምላክ እንድናከብ ረው እና እንድንፈራው ለማስተማር ነው።አለበለዚያ ምስጋናችን ተቀባይነት እንደሌለው ያሳያል።

በአጠቃላይ የአዝማሪ ወርቁ ቃል ግጥሞች በሁለት አውድ ወገን ከፍለን ማየት እንችላለን። የባህል ምሽት ቤት ውስጥ የሚገጠሙ እና በሀይማኖታዊ ክብረ በአል ወቅት የሚከወኑ ናቸው።እነዚህ አውዶች ቀን፤ሰአት እና ቦታ ተቆርጦላቸው የሚከወኑ አውዶች ናቸው። በባህል ምሽት ቤት የተከወኑት ቆከራዊ፡ሙገሳዊ፡ፍቅር፤አባይ ግድብ...ወዘተ ላይ ያተኮረ

ይዘት ሲኖራቸው ሀይማኖታዊ ቃል ግጥሞቹ ደግሞ ስለራስን ማዋረድ፣ስለ ማዳን፣ስለ ፆም ተገቢነት…ወዘተ ላይ ያተኩሩ ቃል ግጥሞች ናቸው።የእነዚህ ቃል ግጥሞች ክዋኔ እና የህይወት ታሪኩ በግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ አማካኝነት ሲተረክ እና ሲከወን ረቂቅ የሆነውን የአዝማሪውን እና የማህበረሰቡን እምነት፣እስተሳሰብ፣ባህል፣ምንነት፣ከበረከቱ በመካፈሉ የሚያገኘውን ስነ ልቦናዊ እርካታ፣በእውዱ አማካኝነት የሚፈጠረውን ማህበ ራዊ መስተጋብር እና ቁርኝት አጠቃላይ ያለውን ፋይዳ እንዲታይ እና እንዲጎላ ይሆ ናል።በመቀጠልም ይህን መሰረት በማድረግ በዚሁ መንፈስ የአዝማሪ ምግብ ግድየለውን የህይወት ታሪክ እና ክዋኔ እተንትናለሁ።

## 3.3. የአዝማሪ ምግብ ግድየለው የህይወት ታሪክ -

አዝማሪ ምግብ ግድየለው ቡርቧክስ ውስጥ መወለዷ እና አባቷ አዝማሪ መሆናቸው ገና የአ ስር አመት ልጅ እያለች ወደ አዝማሪነት ህይወት እንድትቀላቀል አድርጓታል።ምክንያቱም ቡርቧክስ የአዝማሪ መፍለቂያ ሀገር እንደ መሆኗ አንዱ እንዱን እያየ በልጅነታቸው ወደ አዝማሪነት ሙያ ይገባሉ።በዚያ አከባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦች በአብዛኛው አዝማሪ እንደመሆናቸው በዘር በዚህ ሙያ ውስጥ የመቀጠል ሂደት እንዳለ ይነገራል።አዝማሪዋ ከአባቷ ጋር በመሆን በየጠጅ ቤቱ አብራ በመሄድ የእሳቸውን ሙያ በመከተል መለማመዷ ለዚህ ደረጃ እንዳበቃት ትናገራለች።ከዚያም ታዳሚው በሚሰጣት የሞራል ድጋፍ የተነሳ ራሷን ችላ በተለያዩ ጠጅ ቤቶች መዝፈን ጀመረች፡፡ታዳሚው ለእሷ እድገት ያበረከተውን አስ ተዋፅኦ ስትገልፅ"እንቅልፌ ሲመጣ ታዳሚው ውሀ አንስቶ ይረጨኝ ነበር።ይህ ደግሞ ለአ ሁኑ ስራዬ እረድቶኛል በማለት ከህይወት ታሪኳ ጋር በማያያዝ ገጠመኟን ትተርካ ለች"።(ቃለ፡4፡2004 ዓ.ም)

በአሁን ሰአት የሀምሳ ስድስት እድሜ ባለፀጋ የሆነችው አዝማሪ ምግብ ግድየለው በባህር ዳር ከተማ የአዝማሪነት ሙያን አንድ ብላ መጀመሯ እና በሙያው ውስጥ ለሰላሳ አመት መስራቷ በማህበረሰቡ ዘንድ እንድትወደድና እንድትከበር ያደረጋት ጉዳይ ነው።ከዚህ ጋር በተያያዘ የተገጠመላትን ቃል ግጥም እንደ ምሳሌ ላንሳ፦

> አይኖቼም ፈዘዙ እግሮቼም ደነዘዙ
> ምግብ እና ቢራ ከዚህ ቤት ካልጠፉ

ይህ ቃል ግጥም ለእውቅናዋ እንደ ማስረገጫነት ተጠቃሽ ነገር ነው።ምክንያቱም ቃል ግጥሙ እሷን ለማወደስ እና መወደዷን ለማሳየት የተገጠመ በመሆኑ ነው።በሌላ በኩል ደግሞ አዝማሪዋ ታዋቂ እና ተወዳጅ ያደረጋት ነገር አዝማሪን ውጤታማ ከዋኝ ከሚያስብ ሉት መካከል ሁለገብ የሆነ ቃል ግጥም መግጠም እንዱ ነው።ሌላው ቃል ግጥሙን እንደ አውዱ መጠቀም መለዋወጥ፣ማሳቅ፣ማሞገስ፣በአሽሙር መግጠም፣ቅኔያዊ ማድረግ እና በተ መረጡ ቃላት ቃል ግጥም መግጠም ናቸው፡፡ይህችም አዝማሪ ፈጥራ የመግጠም ችሎታ ያላት፣በምትፈጥረው ቃል ግጥም ታዳሚውን በማሳቅ በማስደመም ማዝናናት የምትችል ናት።ለምሳሌ ከነበረው ሁኔታ በመነሳት በፍጥነት ፈጥራ ከገጠመቻቸው ቃል ግጥሞች መካ ከል ለአብነት ያህል ልመልከት፦

ጫቴን ቅሜ ቅሜ ሲያመረቅነኝ
የበደሌ ሞተር የኔ መሰለኝ

የሚል ባለ ሁለት መንቶ ግጥም እናገኛለን።ይህ ቃል ግጥም የተገጠመበት ምክንያት በደሌ የተባለው ሰው ሞተር ሳይክል ይዞ ሰርጉን ለማጀብ ሲመጣ ተመልክተው ከታዳሚው ጋር ስለ እርሱ እድገት ሞተር መግዛት ሲያወሩ ቆዩ።ከዚያም ዘፈን በሚጀመርበት ሰአት ይህን ቃል ግጥም ፈጥራ ገጠመች።ይህ ደግሞ የአደራረጿን ችሎታ እና የመፍጠር ፍጥነቷን ያሳ ያል።ይበልጡኑ ደግሞ ከዚሁ ቃል ግጥም ጋር አያይዛ ፈጥራ የገጠመችው ሌላ ቃል ግጥም የበለጠ ለሚገጠመው ቃል ግጥም ውበትን ሰጥቶታል።

የኔ ውድ በደሌ እንደምን አለህ
በባህርዳር ከተማ ከዚህ ላይ ሁነህ
አንተን የመሰለ ሞተርም ገዝተህ
እንዲያው ተቀምጨ እኔ ላጫውትህ

ይህቺ አዝማሪ አብዛኛዎቹን ቃል ግጥሞች የምትደርሰው ሁኔታን ወይም አውዱን በመመል ከትና ከአውዱ ጋር በማስማማት፣የበፊቱን አስታውሳ በመድገም፣በማሻሻል እና አዲስ ቃል ግጥምን በመፍጠር ነው፡፡በብዛት ቃል ግጥም የሚታወሳት ወይም የሚፈጠርላት በአውዱ ላይ ስትገኝ ነው።እንዲሁም አዝማሪዋ በምትገጥማቸው ቃል ግጥሞች ውስጥ የሷን ማንነት የሚገልፁ እና ህብራዊ የሆኑ ቃል ግጥሞችን የመግጠም አቅም ያላት ናት።ለምሳሌነት ከታች ያለው ቃል ግጥም ብንመለከት ሁለት ፍቺን በውስጡ አምቆ የያዘ ነው፡፡

እንዴት ነሽ ኢትዮጵያ የታጠርሽው በአጋም
እሪ ይላል እንጂ ምስለኔ አይዋጋም

በተጨማሪም ተወዳጅ እና ታዋቂ አዝማሪ በመሆኗ ከአሜሪካ ድረስ መጥተው ሊወስዷት ቢሉ ከሀገሯ ለመውጣት ፈቃደኛ ባለመሆኗ ሳትሄድ ቀርታለች፡፡ስለዚህም ከዚህ ህይወቷ ጋር በተያያዘ መልኩ ቃል ግጥሞችን ስትገጥም ተመልክቻለሁ።

ከሰው ሀገር ሄጄ ጮማ ከምበላ
ይሻለኛል እኔስ አባይ እና ጣና

ቃል ግጥሙ የሚያወሳው ከሰው ሀገር ሄጄ ከሚመቸኝ ከሚያምርብኝ ቢደላኝም ባይደላኝም ሀገሬ ይሻለኛል የሚል አይነት ነው፡፡በሀገር ውስጥ የሚገኘው ይህን አይነት ፍቅር እና አውድ እዚያ የመኖሩ ሁኔታ አጠራጣሪ ነው።ስለዚህ ምንም ቢሆን ሀገሬ እና የሀገሬ ህዝብ

ይሻለኛል የሚል እንድምታ አለው።ይህንን እውቅናዋን በተመለከተ ቃለ መጠይቅ ያደረኩ ላቸው የማአዝማሪ ማህበር ሀላፊው አቶ ትእዛዙ፡ሌሎች አዝማሪያንና እንዲሁም ያነጋገር ኳቸው ሰዎች ስለ እርሷ እንዲህ ነበር ያሉኝ-

> ከሁሉም ደግሞ ምግብ ትልቅ ናት።ነገር ግን እስከ አሁን ወኔዋ አልጠፋም በጣም ከባድ ሴትዮ ናት፡፡ምግብ የምትባለዋ ሲጀመር ጀምሮ በጣም ታዋቂ ናት እጅግ እ ጅግ ነው የምልሽ በጣም ታዋቂ ናት፡፡አሜሪካ ድረስ ምግብ ምግብ እያሉ ይፈልጓ ታል።በጣም ጥሩ ባለ ሙያ ናት እናም ሁሉም ያውቃታል፡፡በሁሉም ጭንቅላት  ውስጥ አለች።አሁን ወጣ ብለን አንድ ሁለት ሰፈር ሄደን ምግብን ታውቋታላችሁ ብለሽ ብትጠይቂ እንጁ አዝማሪዋ እናውቃታለን ነው የሚሉሽ፡፡እንዲያውም በቅር ቡ ከአሜሪካ ድረስ መጥተው ሊወስዷት ቢጠይቋት እንቢ ብላ ነው የቀረችው። (ቃለ፣7፣2004)

በእንዲህ ችሎታዋ የምትታወቀው ይህቺ አዝማሪ ይህ ሙያ በአሁን ሰአት በባህል እና ቱሪ ዝም ታቅፎ እውቅና ከማግኘቱ በፊት አዝማሪ በመሆኗ ማህበረሰቡ ያሳደረባት ዝቅተኛ የሆነ አመለካከት እንደጎዳት ትናገራለች፡፡ማለትም ወጥታ ስትገባ መንደርተኛው፣ነዋሪው…ወዘተ አንቺ አዝማሪ እያሉ ያሾፉባት ነበር።ይህ ደግሞ ልጆቿ በሙያው እንዲያፍሩ እና እንዳይ ተኩ ያደረገ ነው።እንዲሁም የበለጠ በሙያው መስራት እና ማደግ እንዳትችል አድርጓታል። በተጨማሪም እዚህ የእውቅና ደረጃ ላይ ለመድረስ ብዙ የውጣ ውረድ ጎዳናን እንዳሳለ ፈች ያመላክታል።ይህንንም ሁኔታ በመቃወምና አዝማሪ በጥንት ጊዜ የተከበረ እንደነበር ለመግለፅ ይህን ቃል ግጥም በምትሰራበት ሁሉ ትላለች፡፡

> ምን አይነት ዘመን ነው የተገላቢጦ
> ብልሁ ተሰደበ ደንቆሮው ተቀምጦ

እኔ በሙያዬ ሰርቼ ለፍቼ በበላሁ እናቃለሁ።ነገር ግን ምንም ሳይሰራ ቁጭ ብሎ የሚበላው ተከበረ በማለት የውስጥ ብሶቷን የተነፈሰችበት ቃል ግጥም ነው።ያም ሆኖ አዝማሪዋ ምንም ሁኔታ ያልበገራት በሙያዋ የምትኮራ ጠንካራ፣ደፋር እና በራሷ የምትተማመን ሰው ናት፡፡ለሙያዋ ያላት ፍቅር ለእዚህ ክብር አብቅቷታል።

> ልጆቼን ያሳደግኩበት፣ቤቴን የሰራሁበት በዚሁ ሙያ ነው፡፡ስለዚህ የሚያሳፍር ሙያ አይደለም ስለማያውቁት ነው፣ገባ ብለው ስላላዩት ነው ገንዘብ ባገኝበትም ባላገኝበትም ለኔ ትልቅ ሙያዬ ስለሆነ ስለማላፍርበትና ስለምወደው እስከመጨረሻ በዚሁ ሙያ እቀጥላለሁ፡፡በማለት የህይወት ታሪኳን ትተርካለች።(ቃለ፡4፡2004)

ይህቺ አዝማሪ በአሁን ሰአት በባህል ምሽት ቤት ውስጥ ተቀጥራ በመስራት ላይ ትገኛለ ለች።እንዲሁም አዝማሪዋ ቃል ግጥሙን ከሌሎቹ አዝማሪያዎች በተሻለ ፈጥራ በመግጠም፤ ያለ ምንም የሙዚቃ መሳሪያ አጃቢነት መከወን በመቻል እና በእድሜ አንጋፋነት በባህር ዳር ከተማ ውስጥ ስመጥር አዝማሪ ናት።ከዚህም በተጨማሪ ከበባህር ዳር ከተማ ሙያ ውን በመጀመር እና እስከ አሁንም ድረስ በዚህ ሙያ በመቆየት፣ይህን ሙያ ለተተኪው ትውልድ በማስተላለፍ እና ሌሎች በዚህ ሙያ እንዲቀጥሉ አርአያ በመሆን አስተዋፅኦ እያበረከተች ትገኛለች።በዚህ አመትም ባህላዊ ካሴት ለማሳተም በዝግጅት ላይ የምትገኝ ትልቅ አዝማሪ ናት።

ይህቺ አዝማሪ የህይወት ታሪኳን በምትተርክበት ሰአት የምትጠቀመው ቋንቋ ጥሩ ሲሆን ህይወት ታሪኳን እና ገጠመኟን በሚገባ አቀናጅታ ትናገራለች።ቃል ግጥሞቿንም በተገቢው ጣልቃ በማስገባት ትከውናለች።በምእራፍ ሁለት ንድፈ ሀሳብ ላይ እንዳነሳሁት የግለ ተረክ ቲወሪ ከራስም ባለፈ ስለህብረተሰቡ መንገሪያ ስለሆነ አዝማሪዋ የህይወት ታሪኳን ስትተርክ በተያያዥነት ማህበረሰቡ ለእዚህ ሙያ ያለውን የበፊቱን እና የአሁኑን አመለ ካከት ትገልፃለች።እንዲሁም ይህ ዝቅተኛ የሆነ አመለካከት የሚያደርስባቸውን ስነ ልቦ ናዊ ተፅእኖ፣ማህበረሰቡ ለሌሎች ያለውን አተያይ፣የማህበረሰቡን ማንነት፣የእውቀት ደረጃ በተዘዋዋሪ መንገድ ትናገራለች።

በአጠቃላይ ይህች አዝማሪ ፈጥራም ይሁን ደግማ የምትገጥማቸው ቃል ግጥሞች አንዳን ዶቹ ከህይወቷ ተመክሮ ጋር የተቆራኙ፣ከሁኔታው እና ከአውዱ ጋር የተዋሀዱ አስቂኝ እና አስተማሪም ናቸው።ስለዚህ ከዚህ በታች ምእራፍ ሁለት ንድፈ ሀሳብ(ቲዮሪ) ላይ እንዳነሳ ሁት የዚችን አዝማሪ አጠቃላይ ሁለንተና በበለጠ ለመገንዘብ እና ይህን ሁኔታ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ የከወነቻቸውን ቃል ግጥሞች ከህይወት ታሪኳ ጋር በማቀናጀት ክዋኔውን፣ አውዱን እና ፋይዳዉን እመለከታለሁ።

ለዚህ ጥናት ከአጠቃላይ ግጥሞች በአዝማሪ ምግብ ግድየለው በአርቴፊሻል እና በተፈጥሮ መቼት140 ቃል ግጥሞች ተሰብስበዋል።ቃል ግጥሞቹ በሰርግ፣በባህል ምሽት ቤት እና በቃለ መጠይቅ ጊዜ የተሰበሰቡ ናቸው።ከ140ዎቹ ቃል ግጥሞች መካከል ለማሳያነት ሊሆኑ የሚ ችሉ የተወሰኑ ቃል ግጥሞችን በመምረጥ በይዘት በመከፋፈል ለመተንተን እሞክራለሁ።የአ ዝማሪ ወርቂን ቃል ግጥሞች ከመተንተኔ በፊት አጠቃላይ የባህል ምሽት ክዋኔ ምን እንደ ሚመስል አንስቻለሁ።ስለዚህ የባህል ምሽት ክዋኔውን በመመርኮዝ እና የቃል ግጥሞቹን

አውድ በተጨማሪነት በማሳየት የምተነትን ይሆናል።ነገር ግን ከዚህ በታች የምናገኛቸው ቃል ግጥሞች ከባህል ምሽት ቤት በተጨማሪ በሰርግ አውድ ላይ የተገጠሙም ጭምር በመሆናቸው ስለ ሰርግ አጠቃላይ አውዳዊ ክዋኔ ቃል ግጥሙን ከመተንተኔ በፊት እገልፃለሁ።

የአዝማሪያኑ የሰርግ አውዳዊ ክዋኔ የጀመረው ሙሽራው ከመውጣቱ ከስድስት ሰአት በፊት አዝማሪዎች በሰርጉ ቦታ ቀደም ብለው በመገኘት ነበር።ሙሽራው ቤት ደርሰው ትንሽ አረፍ ካሉ በኋላ ወንዱ እንደተለመደው የማሲንቆውን ቅኝት አስተካክሎ እግዚአብሄርን በማመስገን ይጀምራል።በመቀጠልም ሴቷ እየዘፈነች ወንዱ በማሲንቆ እያጀባት ቤቱን ታሞቃዋለች፡፡እኔ በብዛት ሀይሎጋዬ ሆ ሲያስጨፍር ያየሁት ወንድ ነበር እዚህ ግን ያየሁት ሴቷ ናት የምትከውነው፡፡ከዚያ ወንዱ እና ሴቷ እተጋገዙ ሙሽራውን ይዘን ወደ ሴቷ ቤት ጉዞ በመኪና ተጀመረ፡፡መኪናም ውስጥ ባለው ታዳሚ ልክ እንደ በፊቱ አዝማሪዎቹ እየተካኩ የዘፈን ክወናው ቀጠለ፡፡ዘፈኑ ሞቅ ሲል እሷ አብራ እስክስታ ትመታለች ደግሞ ወዲያው ሳይቀዘቅዝ ዘፈኗን ትቀጥላለች፡፡በዚህ ሁኔታ ተጉዘን ሙሽራዋ ቤት ስንደርስ።የሙሽራው መኪና እየተዞረ አዝማሪዎቹ ከፊት ከፊት እየቀደሙ እየዘፈኑ ይከውናሉ፡፡ክዋኔያቸውን በመቀጠልም የሙሽሪት ቤት እስክንገባ ድረስ አዝማሪዎቹ ከታዳሚው ጋር በመሆን ከሙሽራው በፊት እየዘፈኑ እስክስታ እየተመታ ገባን፡፡

ከዚያም ምሳ እየተበላ ታዳሚውን ሲቃኙ ከቆዩ በኋላ ወንዱ አዝማሪ ማሲንቆውን አስተካከለ።ሴቷ ቃል ግጥም በንግግር መልክ ስታቀብለው እሱ በዜማ መከወን ጀመረ፡፡ከዚያ የተቀመጠው ታዳሚ ጋር በመቅረብ ቃል ግጥሙን በዜማ ሲከውኑ፣አንዳንዴ ደግሞ በንግግር መልክ በታዳሚው ላይ በመግጠም ታዳሚውን ሲያዝናኑ ሲያስቁ ሲሸለሙ ቆዩ።በመቀጠልም ሙሽራዎቹ ወደ አሉበት ገብተን በዚሁ መልክ ለሙሽራውና ለሚዜው ቃል ግጥም ከስክስታና ከማሲንቆ በመታጀብ ሲዘፍኑ ሲገጥሙ ቆየን።የሙሽሮቹ መውጫ ሰአት ሲደርስ ሙሽራዋን ይዘን እስከ መኪና ድረስ እሱ እና እሷ እየተተካኩ የሰርግ ዘፈን እየዘፈኑ ተጓዝን፡፡

በመኪና እና መናፈሻ ውስጥ አዝማሪዎች ደክሞአቸው ዝም ሲሉ ታዳሚው እየገጠመ ይዘፍናል፡፡ይህ ጊዜ ለአዝማሪዎቹ የእረፍት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ግጥምም የመድረሻ እና የማሰቢያ ጊዜ ነው፡፡አዝማሪዎቹ ሲቀጥሉ አንዳንዴ ታዳሚው ቃል ግጥም ያቀብላል።አዝማሪዎቹን እየተቀበለ ይዘፍናል፣ያጨበጭባል፣እልል ይላል፣እስክስታ ይመታል፡፡በዚህ ጊዜ አዝማሪዋ

የአበሻ ቀሚስ ነበር የለበሰችው፡፡በአውዱ ውስጥ ጠላ እና ስጋ ወጥ አለ፡፡ከታዳሚው አበሻ ቀሚስ የለበሰ አላየሁም፡፡

እንግዲህ ይህንን የሰርግ አውዳዊ ክዋኔ እና ከወርቁ የቃል ግጥሞች ትንታኔ በፊት በተሰ ጠው የባህል ምሽት ቤት አጠቃላይ ክዋኔ ላይ በመመርኮዝ ቃል ግጥሞቹን እተነትናለሁ። ከዚህም በተጨማሪ እንደ አስፈላጊነቱ የቃል ግጥሞቹን የየራሳቸውን አውድ በተጨማሪነት በማሳየት የምተነትን ይሆናል።

## ሀ.ትችታዊ ቃል ግጥሞች

ከታች የምናገኛቸውን ቃል ግጥሞች አዝማሪዋ ስለ ስራ፣ስለ ባህሪ፣ስለ ጋብቻ እና ከህይወቷ ጋር በተያያዘ በትምህርት ዙሪያ ላይ አሻሽላ የገጠመቻቸው ናቸው።ገጣሚዋ እያንዳንዱን የማህበረሰብ ክፍሎች መጥፎ ስነ ምግባር በመመልከት ማህበረሰቡን በመተቸት ለማረቅ የገ ጠመቻቸው ቃል ግጥሞች ይመስላሉ።

መንቶ 01 ይወለድና እግረ ሰፋፊ
ዘሎ ይማታል በጫማ ጥፊ

መንቶ 02 ይወለድና ጉልበት ጉልበቱ
ጋን ይሸከማል ከነ ድፍድፉ

ቃል ግጥሞቹን የተገጠመችው ምክንያት የትውልዱን ሁኔታ ለማረቅ ብላ ይመስላል።ሁለ ቱም መንቶዎች በቀጥታ ፍቺ ተለያይተው በውስጣዊ ፍቻቸው ተመሳሳይ ናቸው።የመጀመ ሪያው መንቶ የሚያወሳው ጫማ ጥፊ ለመማታት አመቺ የሆነ ጠፍጣፋ ሰፊ እግር ያለው ቁመታም ቅልጥማም ሰው ይወለድና እየዘለለ በጫማ ጥፊ ይማታል ማለት ነው።ሁለተኛው መንቶ ደግሞ ጉልበታም የሆነ ሰው ይወለድና ሌላ ሰው ሊሸከም የማይችለውን ጋን እስከነ ድፍድፉ ድረስ ይሸከማል ማለት ነው፡፡የሁለቱም ውስጣዊው ትርጉም ግን ሀይለኛ፣ጡንቻም የሆነ ሰውን የማያከብር የማይፈራ ትውልድ ይወለድና ሰውን ያዋርዳል እንደ ማለት ነው። እነዚህን ቃል ግጥሞች ስንመለከት ወደ ፊት የሚመጣው ትውልድ ምን ያህል አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማሉ።

ይህንንም ለማመልከት አዝማሪዋ እግረ ሰፊ የሚለውን ጥምር ቃል በመፍጠር ተጠቅማለች በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ የፍርሀት ስሜት ይነበባል፡፡ማለትም ወደ ፊት ሊተካ ያለውን ትው ልድ በማሰብ ጥሩ የሆነ ስሜት አይታይም።ምክንያቱም ተረክዝን ማንሳት ትእቢተኝነትን

አመላካች ነው።ወደ ፊት ይፈጠራል ብላ የምታስበው ይህን አይነት ትውልድን ነው።እንዲሁም በሁለተኛው መንቶ ውስጥ ጋን የሚል ቃል እናገኛለን።አስር ጊዜ ጉልበታም ሰው ቢወለድ ጋኑን ብቻ መሸከም አይችልም እንኳን ድፍድፍ ተጨምሮበት።ስለዚህ ቃል ግጥሙን በቀጥታ ትርጉሙ ከተመለከትነው ግነት ይታይበታል።ይህ ቃል ግጥም የተገጠመው ሰርግ አውድ ላይ በመሆኑ ታዳሚው በዚህን ሰአት የቃል ግጥሙን መልእክት ትኩረት በመስጠት የሚሰማው አልመሰለኝም።ታዳሚው ግጥሙን ሲሰማ ምንም አይነት ምላሽ ሲሰጥ አልተመለከትኩም።እንዲያውም በደማቀ አቀባበል፣ጭብጨባ እና ጭፈራ(እስክስታ) አዝማሪዋን እየተቀበለ ይከውናል።ቃል ግጥሙ በዜማ መልክ ተላብሶ በማሲንቆ ታጅቦ ይከወናል።መከወኑም ሰርግ ያደምቃል።ከዚህም ባሻገር ማህበረሰቡ የሚወደውን የሚጠላውን የሚያሞግሰው የሚነቅፈው በዚህ አይነት መንገድ ስለሆነ ይነቅፍበታል፣ያስተምርበታል፣ ያሳስብበታል።

በንድፈ ሀሳቡ ላይ እንደተነሳው ቃል ግጥሞቹ በሚከወኑበት ወቀት ማህበረሰቡ በዉስጡ ሲል የፈለገዉን ጉዳይ ተጨባጭ በሆነ ሁኔታ ያንፀባርቅበታል።

መንቶ 01 ያገባም አገባ ያላገባም ታጨ
አንዳንዱ ቀረ እንጅ ፂሙን እየላጨ

ይህን መንቶ የገጠመችው በሰርግ ላይ በመሆኑ መልእክቱ ከተገጠመበት አውድ ጋር ተስማሚ ነው።በዚህ መንቶ ውስጥ የቃል ግጥሙ ፍቺ የሚገኘው ፂሙን እየላጨ የሚለው ቃል ላይ ነው።ምክንያቱም ፂም ሳይኖረው ቀርቶ ህፃን እየመሰለ ለቁም ነገር ሳይበቃ ቀረ የሚለውን ፍቺ ያሳየናል።በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ እድሜን አመላካች የሆነው ቃል "ፂም" የሚለው ነው።ይህ ቃል ከጉርምስና ጀምሮ በወንዶች ላይ የሚመጣ ተፈጥሮአዊ ነገር ነው። ወንዶች በልጅነት እድሜአቸው ፂም አያበቅሉም።ስለዚህ እድሜው ገና እየመሰለ ሳያገባ አረጀ ማለት ነው።የዚህ ቃል ግጥም መነሻ ያላገባውን ለመተቸት እና እንዲያገባ ለመገፋፋት ነው።ማለትም በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ ከተወሰነ እድሜ ልክ በላይ ሳያገባ ሲቀር "ቆሞ ቀር" እየተባለ ይተቻል።ይህ ቃል ግጥም ይህንን ሁኔታ ያመላክታል።

ታዳሚው አዝማሪዋ የቃል ግጥሙን የመጀመሪያ ስንኝ ስትል እሺ የሚል ምላሽ እየመለሰ እየሳቀ ይቀበላል።ይህ ደግሞ ታዳሚው ለመልእክቱ ትኩረት መስጠቱን ያሳያል።ቃል ግጥሙ ዜማዊ በሆነ መልክ በማሲንቆ ታጅቦ ይከወናል።ይህ አውድ መፈጠሩ፣መከወኑ፣ መተረኩ ሰርጉን ለማድመቅ፣ማህበረሰቡ ስለ ትዳር ያለውን ሁኔታ ለማመላከት ይጠቅማል። እንዲሁም በዚህ ቃል ግጥም አማካኝነት የማይወደውን ነገር ይተችበታል።

መንቶ 01 ኸረ ሚዜው ሚዜው ኸረ ሚዜው ፊዟል
ለሙሽራው ሚሆን እጣን መች ይዟል

ይህ መንቶ እጣን የሚለው ቃል ሁለት ፍቺ እንዲኖው አድርጎታል።ማለትም ህፃን ልጅ የሚል ሲሆን ሌላው ትርጉሙ ደግሞ የሚጤስ እጣን ወይም ሽቶ ማለት ነው።የቃል ግጥሙ መነሻ ሚዜውን ለመሳደብ ለመተቸት ነው።እንዲሁም የሙሽራው ሚስት ህፃን አይደለችም ማለት ነው።

ይህ ደግሞ ከላይ እንዳለው ቃል ግጥም በማህበረሰቡ ዘንድ ሴት ልጅ ብዙም ሳታድግ እንደ ምታገባና እድሜዋ ገፋ ሲል ትችት እንዳለባት ያሳየናል።ስለዚህ በአሁን ሰአትም ሴት ልጅ በልጅነቷ ማግባት አለባት የሚለው የቀረ አስተሳሰብ ገና ርዝራዥ አለመጥፋቱን የሚያ መላክት ነው።የቃል ግጥሙ ትኩረት በሚዜው ላይ ነው።ይህንንም ለማሳየት በተደጋጋሚ ኸረ ሚዜው የሚለው ቃል ተደጋግሞ እናገኛለን።ሚዜው ላይ ትኩረት መደረጉ ለሙሽራው ሚዜ የሚሆኑት ሰዎች ጓደኞቹ ወይም ቅርብ ዘመዶቹ ናቸው።ስለዚህ እንዴት ስለልጅቷ ምንም ሳይሉት ቀሩ ከሚል አንድምታ የመነጨ ይመስለኛል።በዚህ ሰአት አጃቢዎቹ የወንዱ ቤተ ዘመዶች ስለነበሩ እየሳቁ በደስታ ያጅቡ ነበር።ይህ ቃለ ግጥም መከወኑ እና መተረኩ ሰርግ ያደምቃል፣ያዝናናል፣የማህበረሰቡን አመለካከት ይገልፅበታል።

አራቶ 01 ሲነግዱ አትነግድና
ሲማሩ አትማርና
ሲሰሩ አትስራና
ሰው ውሎብኛል በል ከጥላው ሁንና

የቃል ግጥሙ አንዱ ትርጉም አንድ ስራ ሳትሰራ ተቀምጠህ ሰው እንዲህ አደረገኝ ስትል ዋል የሚል ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ በሌላ ሰው ላይ ተጠግተህ ስራ ሳትሰራ ሰው ስለ መተተብኝ እንዲህ ሆንኩ በል ማለት ነው።ምፀታዊ ንግግር ነው።በዋናነት ግን በቃል ግጥ ግጥሙ ሊተላለፍ የፈለገው ሀሳብ ሳይሰሩ በሰው ትከሻ ላይ ሁነው መኖርን ለመተቸት እና ሰርቶ ማደርን ለማስተማር፣ሰው ሳይሰራ እጁን አጣጥፎ ተቀምጦ እንዲህ ሆነብኝ ማለት ተገቢ አለ መሆኑን ለማመላከት ነው።እንዲሁም ማህበረሰቡ የስራ ባህሉን የበለጠ እንዲዳብር ለማድረግ ለማበረታታት ሲሆን አንዱ አንዱን እየተመለከተ ለስራ እንዲነሳሳ ለማድረግ ነው።ምክንያቱም የቃል ግጥሙ መነሻ በከወናው ወቅት በስራ ታታሪ የሆነ ሰው ስለነበር ልክ እንደ እርሱ ስራ ተማር ለማለት የተገጠመ ነው።ሌላው ደግሞ አዝማሪዋ ባለመማሯ

የሚፈጥርባት ስሜት እንድትገጥም ያደረጋት ይመስለኛል።ስለዚህ ሌላውም በዚህ ህይወት እንዳያልፍ ለመምከር ከሚል የሚመነጭ ነው። ይህ ደግሞ በንድፈ ሀሳቡ ላይ እንዳተነሳው ስለምናጠናው ሰው ምንነት በበለጠ ለመረዳት ከህይወት ተረኩ ጋር ስራዎቹን እያይዘን ማጥናት አንዱ ሁነኛ መንገድ ነው።

ስለዚህ በህይወት ተረኩ ያላገኘነውን ነገር በስራዎቹ ውስጥ ለማግኘት ያስችለናል።ምክ ንያቱም ግጥም የውስጥ ስሜትን ማንፀባረቂያ መሳሪያ ነው።እናም ህይወቷ ከግጥሞቿ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ያሳያል።ምክንያቱም በቃለ መጠይቅ ወቅት ስለ አለመማሯ እንጂ አለመማሯ የፈጠረባትን ስሜት አልነገረችኝም።ነገር ግን ይህን ስሜቷን ቃል ግጥሙ በተወሰነ ለማየት አስችሎኛል።እንዲሁም ከጥላው የሚለው ቃል ከላይ ካነሳሁት ትርጉም ባሻገር ከዝናብ ከፀሀይ የምጠለልበትን ቁስንም ይጨምራል።በአጭሩ የቃል ግጥሙ መልእክት እጅህን አጣምረህ አትቀመጥ ስራ ለማለት ነው።

ይህ ቃል ግጥም በሚከወንበት ወቅት የሰርጉ ምሳ ሰአት ስለነበር ታዳሚው በስርአት የሚባለ ውን ያዳምጥ ነበር።የቀረበው በማሲንቆ ታጅቦ በዜማ መልክ ነው።በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ በተደጋጋሚ የተነሱ ሲነግዱ አትነግድና ሲሰሩ አትስራና...ወዘተ የሚሉ ሀረጋትን እናገኛለን እነዚህ ሀረጋት የቃል ግጥሙ መልእክት የታዳሚውን ጆሮ እንዲያገኝ፣በሰሚው ውስጥ መል እክቱን ለማስረፅ እና ለመልእክቱ አፅንኦት ለመስጠት ተጠቅማባቸዋለች።በአጠቃላይ ይህ ቃል ግጥም ባይከወን እና ይህ ክወና ባይተረክ ለመታየት እና ጥቅሙን ለማወቅ አይቻልም ነበር።እንዲሁም የዚህ ቃል ግጥም መከወኑ ካነሳሁት ፋይዳ ባሻገር ስንፍናን ለመዋጋት ይጠቅማል።

## ለ.የሙገሳ ቃል ግጥሞች

ከዚህ በታች የምናገኛቸው ቃል ግጥሞች ደግሞ አዝማሪዋ ሰውን፣ቁንጅናን እና የተማረን ለማሞገስ ስትጠቀምባቸው የሰማኋቸው ናቸው።ስለ መማር ያነሳቻቸው ቃል ግጥሞች ከላይ እንዳለው ቃል ግጥም ከህይወቷ ጋር የተጣመሩ ናቸው።ምክንያቱም አለመማሯ በውስጧ የሚፈጥረው ስሜት እና ዘመኑ በራሱ ለትምህርት ያለው ከፍተኛ ቦታ የተማ ረን እንድታወድስ ያደርጋታል።

መንቶ 01 የኔማ እንትናዬ በጣም ታድለሻል
የተማረ ምሁር እንትናዬን አግኝተሻል

መንቶ 02 የኔማ እንትናዬ የጎበዝ ልጅ
የተማረ ምሁር ያስደስታል እንጂ

ቃል ግጥሞቹ የተገጠሙበት ዋነኛ ምክንያት ሙሽራውን ለማሞገስ ነው።ነገር ግን የአዝማሪ ዋን ውስጣዊ ስሜት ስናይ ግን ከላይ እንዳነሳሁት አለመማሯ ውስጧ የሚፈጥረው ስሜት ቃል ግጥሙን እንድትፈጥር እንዳነሳሳት እንረዳለን።የመጀመሪያው መንቶ የሚያወሳው ሙሽራዋን ያገኘሽው ሰው የተማረ ስለሆነ ደስ ይበልሽ የሚል ሲሆን ሁለተኛው መንቶ ደግሞ የተማረ ሰው መማሩ ደስታን እንደሚሰጥ የገለፀችበት ነው።እዚህ ቦታ ላይ ስለ ሙሽራዋ መማርም ሆነ አለመማር ያለችው ምንም ነገር የለም።አዝማሪዋ ትኩረት የሰጠ ችው በወንዱ ሙሽራ ላይ ነው።ሁለቱም መንቶዎች ማህበረሰቡ ለተማረ ሰው የሚሰጠውን ትልቅ ቦታ ያመላክታሉ "የተማረ የተመራመረ"ይባል የለ።

በተቃራኒው ደግሞ ቃል ግጥሞቹ ላልተማረው ማህበረሰብ የሚሰጠውን ቦታ ያሳያሉ።እኔ እንደሚመስለኝ ይህን የፈጠረው በአሁኑ ዘመን እየጨመረ የመጣውን ትምህርትን ፍላጎት ይመስለኛል።ከመማርም ባለፈ በአሁን ሰአት የውድድር ጊዜ ነው።በገጠሩም አካባቢ ከበፊቱ በበለጠ ማህበረሰቡ ልጁን ለማስተማር የፈለገበት ሰአት ነው።ስለዚህ ለትምህርት ትኩረት መስጠቱን እናያለን።ይህንን ሁኔታ የበለጠ ለማሳየት በዚህ ጊዜ የተቀለደን ቀልድ ላንሳ- አንድ ሰው ወደ ሆነ ቦታ ሄዶ ሊገባ ሲል በጥበቃዎች የሚጠየቀው መታወቂያ ከሌላው ደግሞ ዲፕሎማ ነው።ማለትም በአሁን ሰአት አብዛኛው ሰው ድግሪ እና ከዚያም በላይ የሆነ የትምህርት ደረጃ ባይኖረውም ቢያንስ ዲፕሎማ አለው በሚል ነው።ስለዚህ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን የትምህርት መውደድ እንቅስቃሴ ያመላክታል።

መንቶዎቹ ሙዚቃዊ ቃናን ተላብሰው በማሲንቆ፣በአጃቢው ጭብጨባ እና በአዝማሚዋ እስክ ስታ ታጅበው የተከወኑ ናቸው።መከወናቸውም ህዝቡን እና ታዳሚውን እያዝናኑ ለማስተ ማር ያልተማረውን እንዲማር ለማነሳሳት፣ስለ ትምህርት አስፈላጊነት ለማስተማር እና የተ ማረን ለማሞገስ ይጠቅማል።እንዲሁም በዚህን ሰአት የአብዛኛውን የማህበረሰብ የትምህርት ደረጃ፣ማህበረሰቡ ለትምህርት ያለውን ግንዛቤ ሲከወን ሲተረክ ይታያል።ከዚህም ባሻገር ስለ አዝማሪዋ ምንነት ከህይወት ታሪኳ ጋር በማያያዝ የበለጠ ለመረዳት ያስችላል።እንዴት ቢባል አዝማሪዋ የህይወት ታሪኳን ስትነግረኝ አለመማሯን ከመግለጽ በቀር ባለመማሯ ያደ ረባትን ውስጣዊ ስሜት አልገለፀችልኝም ነበር።ነገር ግን ቃል ግጥሙ እማካኘንነት የው ስጥ ስሜቷን በተወሰነ ለመረዳት አስችሎኛል።ስለዚህ ነው በምእራፍ ሁለት ውስጥ ያነሳ ሁት ንድፈ ሀሳብ በተግባር የሚታየው።

መንቶ 01 አንቺ ባህርዳር ጎድጓዳዋ መሬት
ታብቂያለሽ አሉ ሽጋ እንደ ሰንበሌጥ

ይህ መንቶ ደግሞ የሙሽራውን ውበት ለማመላከት እና ለማሞገስ የተገጠመ ነው፡፡በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ አነፃፃሪ ዘይቤ እናገኛለን፡፡የሙሽራው ውበት ከሰንበሌጥ ሳር ጋር ይወዳድራል።የባህር ዳር ከተማ የሰንበሌጥ ሳር እንደምታብቅል ሁሉ ቆንጆ ሰው ታፈራለች የሚል ትርጉም አለው፡፡ሌላው በቃል ግጥሙ ውስጥ የተመለከትኩት መልክ አምድራዊ የመሬት አቀማመጥ ገፅታን የሚገልፁ ነገሮችን ነው፡፡

ማለትም ጎድጓዳዋ መሬት የሚለው ባህር ዳር ረግረጋማ መሬት መሆኗን ነው የሚያሳየው። ምክንያቱም ሰንበሌጥ የሚበቅለው ረግረግ በሆነ ስፍራ ነው።ይህ ነገር በቃል ግጥሙ ውስጥ የመምጣቱ ጉዳይ ምንድን ነው ስንል ልክ እንደ እዚህ ሳር ይህቺ መሬት የቆንጆዎች መፍለቂያ መሆኗን ያመላክታል፡፡የቆንጆች ሀገር ናት ለማለት ነው።እንዲሁም በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ አዝማሪዋ ምስል ከሳች ዘዴን በመጠቀም ሀገሯን እንድናያት ታደርገናለች።ልክ እንደ ሰው ስታናግራት እናያለን።ስለዚህ ይህ ደግሞ ሰውኛ ዘይቤ በቃል ግጥሙ ውስጥ መኖሩን ያሳየናል፡፡ሀገሯ አንቺ የተባለችበት ምክንያት ሀገር በሴት ስለምትወከል ነው፡፡ስለዚህ ይህ ቃል ግጥም ሲከወን የአዝማሪዋን የአገጣጠም ክህሎት፣ማህበረሰቡ ስለ ራሱ የሚገልጽበትን መንገድ፣የሀገሩን ገጽታ ያሳይበታል።

ከዚህም በተጨማሪ ማህበረሰቡ ስለራሱ እና ስለ ሌሎች ያለውን አመለካከት ይንፀባርቅበታል።ቃል ግጥሙ በዜማ መልክ በማሲንቆ ታጅቦ እንደ የሁኔታው በቅብብል መልክ በመሆን ይከወናል።ታዳሚው በደመቀ አቀባበል እና በእስክስታ ይከውን ነበር።ቃል ግጥሙ መከወኑ ለማሞገስ ለማድነቅ ያገለግላል፡፡

መንቶ 01 እንትናዬ ጋር ስመጣ ማን ይሞታል ብዬ
ገንዘቤን ጨረስኩት ተስዬ ተስዬ

ይህ ቃል ግጥም በሰርጉ ምሳ ሰአት ላይ አዝማሪዋ አጃቢዎች መሀል በመግባት ለአንዱ የገጠመችው ነው፡፡ተስዬ የሚለው ቃል መንቶውን የተለያየ ፍች እንዲኖረው አድርጎታል።የመንቶው ፊት ለፊት የምናገኘው ትርጉም እሱን እንዳላጣው ለአምላኬ በሰላም አድርሰኝ ብዬ ስለት ተሳልኩ አስር ጊዜ ለአምላክ ስሳልም ገንዘቤን ጨረስኩት የሚል ነው።ሌላው ደግሞ እሱ ጋር ሄጄ አስር ጊዜ ስእል ለመሳል ስከፍል ብሬን ጨረስኩኝ ነው።ተስዬ የሚለው ቃል ሲከወን ማህበረሰቡ የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት አምላኩ እንደሚሰጠው በማመን ከአምላኩ

ጋር የሚያደርገውን የማይታየውን ግንኙነት እንዲታይ ያደርጋል።እንዲሁም ቃሉ በቃል ግጥሙ ውስጥ በመደጋገም ተነስቷል፡፡ይህም ድግግሞሽ ድርጊቱ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ተደጋግሞ መፈፀሙን ያሳያል፡፡እንዲሁም ሀረጉ በተደጋገመ መጠን ስለ ጉዳዩ አፅንኦት ለመ ስጠት በሰሚው ዘንድ ጆሮ ለማግኘት ይጠቅማል፡፡

በተጨማሪም ቤት እንዲመታ እና ዜማው እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡አጃቢው በሙገሳው እየተዝ ናና ይደሰታል፡፡አዝማሪዋ እስክስታ እየመታች በዜማ በማሲንቆ ታጅባ ነው ያቀረበችው።ቃል ግጥሙ መገጠሙ ለማድነቅ ለማሞገስ ያገለግላል፡፡

## ሐ.የእንጉርጉሮ ቃል ግጥሞች

እነዚህ ቃል ግጥሞች እንዳለ ደግማ የመቀኘቷ ሚስጥር ብሶትን፣ማጣትን፣መንከራተትን ለማመላከት ነው።በዚህ ርእስ ስር የምናገኛቸው ቃል ግጥሞች ከአንድ በላይ ትርጉም ያላቸው ቃል ግጥሞች ናቸው።

መንቶ 01 ላሚቱና ጥጃው አብረው እየዋሉ
አሁን የት ይገኛል ወተት ወተት ቢሉ

ቃል ግጥሙ ባለ ሁለት መንቶ ነው፡፡ወተት ወተት ቢሉ የሚለው ሀረግ ቃል ግጥሙን ህብረ ቃል ስለሆነ የተለያየ ፍቺ እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡የመጀመሪያው ላሚቷ ከጥጃዋ ጋር አብራ ከዋለች ወተቱን ስለምትጠባው አሁን ወተት ቢፈለግ አይገኝም ማለት ነው።ሌላው ደግሞ በአሁኑ ሰአት ቢወጡ ቢወርዱ ቢንከራተቱ ቢባዝኑ ምንም ነገር አይገኝም ማለት ነው።

እንደ እኔ አመለካከት በይው እና ተበይው በመገናኘታቸው የተፈጠረ ውጤት ይመስለ ኛል።ወተት የሚለው ቃል በቃል ግጥሙ ውስጥ በመደጋገም ተነስቷል፡፡ይህም ድግግሞሽ መንከራተቱን መውጣት መውረዱን ያሳያል፡፡እንዲሁም ሀረጉ በተደጋገመ መጠን ስለ ጉዳዩ አፅንኦት ለመስጠት ይጠቅማል፡፡እንዲሁም በአሁን ሰአት ያለውን የኢኮኖሚ ችግር፣የኑሮ ውድነትን ያሳያል።ስለዚህም በመተረኩ በመከወኑ የማህበረሰቡን ብሶት ያሳያል።አዝማ ሪዋ ቃል ግጥሙን ስትገጥም የነበራት የደበዘዘ ፊት ከሰርጉ እውድ ጋር የሚጣጣም አል ነበረም።

መንቶ 01 በሀምሌ በነሀሴ እንዴያ ስዋትት
እንዴት በመስከረም በተስፋ ልሙት

በዚህ መንቶ ውስጥ በተስፋ በሚለው ቃል ውስጥ ሁለት ትርጉም እናገኛለን።አንደኛው በሀምሌ እና በነሀሴ ወራት ስንከራተት ቆይቼ እንዴት በመስከረም ተስፋ በተባለው ሰው ፍቅር እሞታለሁ የሚል ነው፡፡በሌላ በኩል ደግሞ በሀምሌ እና በነሀሴ ስንከራተት ቆይቼ እንዴት በአዲሱ አመት በለምለሙ ጊዜ ቀን ሲወጣ ተስፋ አጥቼ ልሙት ነው።

የሀምሌ የነሀሴ ወራቶች ገና ምንም እህል የማይደርስባቸው በዝናብ የተሞሉ ጭፍግግ ያሉ ወራት ናቸው፡፡ስለዚህ እነዚህ ወራቶች የነገሩን ክብደት የችግሩን መክፋት እና የሰውየውን መባዘን ለመግለፅ በግጥሙ ውስጥ ተወክለው የገቡ ናቸው፡፡ስለዚህ ይህን ሁሉ ከባድ ጊዜ እና ሰአት ካለፍኩኝ በኋላ እንደገና የተስፋ ተምሳሌት በሆነው እና ብርሀን በሚፈነጥቅበት በመስከረም ወር ተስፋ ልጣ የሚል እድምታ ያለው ግጥም ነው።ስዋትት የሚለው ቃል መንከራተት መባዘን ያሳያል፡፡ቃል ግጥሙ ሲከወን ታዳሚውን ሳየው ምንም ነገር አልነበረም።ይህ ደግሞ እኔ እንደሚመስለኝ አንድም ታዳሚው እየተጫወተ ስለነበር ብዙም ጆሮ ያለመስጠት ጉዳይ ሲሆን ሌላው በቃል ግጥሙ ያለመሳብን ሊያሳይ ይችላል።

መንቶ 01 ማሲንቆ እና ክራር በእኛ ያምራል እጅ
አሰልጥኖ መስጠት ለመደብኝ እንጂ

ይህ መንቶ አንድም የባህላዊ ሙዚቃ ጥበብ መገለጫ የሆኑት ማሲንቆ እና ክራርን በልምዱ የቆዩ ሰዎች ሲጫወቱት ለዛ እና ልዩ ውበት አለው፡፡ነገር ግን የሁኔታዎች አለመመቸት እና የእድሜም ጉዳይ ገደበን እንጂ የሚል የሀዘን ድባብ የተላበሰ መልእክትን ያነገበ ነው፡፡ስለዚህ ለሌላው ይንን ሙያ እያስማመድኩኝ መስጠት ነው የሚል ነው፡፡ቃል ግጥሙ በአንድ በኩል ተስፋ የቆረጠ ስሜት ይነበብበታል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ እኔ ባልጫወትም ሌላውን በማሰልጠኔ ባህሉ ቀጣይ እንዲሆን አድርጌአለሁ የሚል የተስፋ ስሜት የሚታይ ይመስለኛል፡፡

ስለዚህ በቃል ግጥሙ ሁለት ተቃራኒ ስሜቶች ተዋህደው የገጣሚውን ስሜት ያንፀባርቃሉ። ምን ያደርጋል የሚል የተስፋ መቁረጥ ስሜት እና እንደገና በዚያ ስሜት ውስጥ ደግሞ ተስፋውን ህይወት የሚዘራ ነገር ይነበባል፡፡በቃል ግጥሙ ውስጥ የገቡት ማሲንቆ እና ክራር ጥንታዊ የሙዚቃ መሳሪያ እንደመሆናቸው ጥንታዊ የሆነውን የሙዚቃ ሁኔታ እንድናስብ

ያደርጉናል።ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ስለሆኑ ተጨዋቹ ባህላዊ መሆኑን አዝማሪነቱን ማሲንቆው ይጠቁመናል።ዚህም በተጨማሪ ይህ ጥንታዊ የሆነ የሙዚቃ ባህል ስናስብ በተዘዋዋሪ ይህ ባህል በምን ሁኔታ እንዳለ እንድናጤን ያደርገናል።

መንቶ 02 አዝማሪ ይሉኛል አዝማሪስ እሳቸው
የተበላሸውን ስላደስኩላቸው

ቃል ግጥሙን ስንመለከት አዝማሪ እያሉ ለምን ይሰድቡኛል የተበላሸ ነገራቸውን ባስተካከልኩላቸው የሚል ሲሆን ሌላው ትርጉሙ ደግሞ ለምን አዝማሪ እያሉ ይሰድቡኛል ባዝናናኋቸው ባስደሰትኳቸው የሚል ነው።እኔን እኔን ይጠላሉ እሬን እሬን ይወዳሉ እንዳለችው አይጥ ማህበረሰቡ ከአዝማሪዎች ሙገሳ እና ውዳሴአቸውን ይፈልጋል።በተቃራው ደግሞ ከእነርሱ ጋር መጋባትም መዋለድም አይፈልግም።ስለዚህ ይህ ሁኔታ የፈጠረው ጥሩ ያልሆነ ስሜት ነው ይህንን እንድትቀኝ አድርጓታል።

ይህንን ሁኔታ የተቀኘችውን ቃል ግጥም ከህይወት ታሪኳ ጋር አያይዘን ስንመለከት ይህ የማህበረሰቡ ዝቅተኛ አመለካከት ምን ያህል እኳንም ሆነ በዚህ ሙያው ውስጥ ተሰማርተው የሚገኙትን እንደጎዳቸው ያሳየናል።ይህ ሀሳብ በህይወት ታሪኩ እና በቃል ግጥሙም ውስጥ መንፀባረቁ የነገሩን ክብደት ያሳያል።መንቶው የተከወነው በባህል ምሽት ቤት ውስጥ ነው። ስለዚህ ስለ ባህል ምሽት ቤት አውዳዊ ክዋኔ በተነተንኩት አከዋወን መሰረት ይከወናል።ቃል ግጥሙ ንዴትን፣ቁጭትን፣መገረምን፣ማዘንን እና ብሶትን የተላበሰበ በመሆኑ ከታዳሚው ዘንድ ሀዘንና እና ሽልማት አብሮ ይገባል።ይህ ቃል ግጥም መከወኑ እና መተረኩ በቲወሪው እንደተነሳው ህዝቡን እና ታዳሚውን እያዝናኑ ለማስተማር፣ለዚህ ሙያ ያላቸውን ግንዛቤ ለመቀየር፣የውስጥ ስሜትን እና ብሶትን ለመተንፈስ፣የማህበረሰቡን አመለካከት እና ማህበራዊውን መስተጋብር ለማሳየት ይጠቅማል።ማለትም ማህበረሰቡ የሚያከብረውን እና የሚንቀውን ያሳያል።እንዲሁም በሚናቀው ማህበረሰብ ዘንድ የሚፈጠረውን ስነ ልቦናዊ ቀውስን ያሳያል።በተጨማሪም አንዱ አንዱን የሚያይበትን አተያይ በመመልከት የማህበረሰቡን ማንነት ለማየት ያስችላል።

## መ.ስለ ሀገር

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ቃል ግጥሞች ደግሞ ሀገርን እና ዘርን አወዳሽ ቃል ግጥሞች ናቸው።እነዚህም ቃል ግጥሞች ከላይ እንዳለው ቃል ግጥም ከአዝማሪዋ የህይወት ታሪክ እና ከማንነቷ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው።

ሰውነቱ አንድ ነው

ጨርቂም ምናምን ነው

ሀሞቴም ኩሩ ነው

ሰባራው ይቅርብኝ ዘሬ ጎንደሬ ነው

የመንቶው መነሻ ሀገሯን ለማስተዋወቅ ነው፣ማንነትን ለማሳየት ነው።የቃል ግጥሙ መልእክት ደግሞ የኔ ዘር ጥሩ ኩሩ ነው ዝም ብሎ የማይጠቅመው አልፈልግም ማለት ነው።በሌላ በኩል ደግሞ የሆነ አካሉ(የሰውነት ክፍሉ) የተጎዳው ይቅርብኝ ነው።ይህ ዘር የሚለው ጉዳይ በጥንት ጊዜ የባላባት ዘር ያለው፣የተከበረ አጥንት ያለው ከሚለው የመጣ ነው።በቃል ግጥሙ ውስጥ ንፅፅራዊ ዘይቤን እናገኛለን።የጎንደሬ ዘርን ከሌላው ጋር የማነፃፀር ሁኔታ ይታያል።ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ ሶስተኛው ስንኝ ድረስ ተመሳሳይ የሆነን ሀሳብ የሚገልፁ ሀረጋትን እናያለን።እኔ እንዲህ ነኝ የሚል ሀሳብን የያዘ ነው።

በህይወት ታሪኳ ውስጥ ጎንደሬ መሆኗን ተናግራለች።ነገር ግን በተወለደችበት ሀገር እና ዘር መኩራቷን ያሳየው በቃል ግጥሞቿ ውስጥ በተደጋጋሚ የምታነሳቸው ሀሳቦች እና ስትከውን የምታሳየው ሁኔታ ነው።ስለዚህ በንድፈ ሀሳቡ ላይ እንደተመለከተው የህይወት ታሪክን እና ስራዋን መመልከት የበለጠ ስለ አዝማሪዋ ማወቅ እንዲቻል ይረዳናል።ቃል ግጥሙ በዜማ መልክ በማሲንቆ ታጅቦ በቅብብል ይከወናል።ቃል ግጥሙ መከወኑ ሰርግ ያደምቃል፣ያዝናናል፣ማንነትን ያንፀባርቃል።አንዱ ስለ ሌላው ያለውን አመለካከት ያሳያል።

ውጭ ሀገር ብሄድ ጭብጥ ጤፍ አይገኝ

ሀገሬ ኢትዮጵያ ካንቺ ውጭ አያድርገኝ

የቃል ግጥሙ መነሻ አዝማሪዋ ወደ ውጭ ሀገር እንውሰድሽ መባሏ ነው።የቃል ግጥሙ መልእክት ደግሞ ከኢትዮጵያ ሀገር ውጭ መሄድ አልፈልግም ማለት ነው።ምክንያቱም እንደ ኢትዮጵያ ያለ አወድ(ባህላዊ አውድ)ህዝብ አላገኝም ከሚል ስሜት የመነጨ ነው።ጤፍ የሚለው ቃል ለምግብነት የሚያገለግል የሰብል አይነት ሲሆን በዚህ አውድ የኢትዮጵያን ባህላዊ አውድን ወክሎ ለማንፀባረቅ የገባ ቃል ነው።የህይወት ታሪኳን ስትርክ ወደ አሜሪካ የመሄድ አጋጣሚ አግኝታ እንደነበር ሌሎች አዝማሪዎች፡ህላፊው እና ሌሎች ሰዎች ነግረውኝ ያካተትኩትን ሀሳብ እውነታውን ያረጋገጥኩበት ቃል ግጥም ነው።ማለትም ከላይ እንዳለው ቃል ግጥም አዝማሪዋ ታሪኳን ስትናገር ያልገለፀችውን ጉዳይ በስራዎቿ ለማወቅ አስችሎኛል።ስለዚህ በንድፈ ሀሳቡ ላይ እንደተባለው ስለ ባለሙያው ለማጥናት ሁለቱንም በማያያዝ መመልከት ስለ ነገሩ ያለን እውቀት እንዲሰፋ ያደርጋል።



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ ሀገርን የመውደድ እና የማድነቅ ስሜት ይንበባል።እውዳዊ ከዋ ኔው በባህል ምሽት ቤት አከዋወን እንደገለፅኩት በተመሳሳይ መልኩ ይከወናል።መከወ ኑም ሀገርን መውድድን ለመግለፅ፣ማንነትን ለማንፀባረቅ፣ሀገርን ለማወደስ ይጠቅማል።

## ሠ.የፍቅር ቃል ግጥሞች

በዚህ ርእስ ስር የሚገኙት ቃል ግጥሞች ሙሽሪትን ለማወደስ የገቡ የሰርግ ዘፈኖች ናቸው

ሶስቶ 01 አይኗ በላይ በላይ
ጥርሷ በላይ በላይ
ኬላ ላይ ያለሽው አስካልዬ በላይ

መንቶ 02 ስጠይቅ ሳስጠይቅ ኬላ ላይ ሁነሽ
የኔ ውድ አስካሌ አንጀቴን በላሽ

ሶስቶ 03 ኸረግ እናናዬ ኸረግ እናናዬ
እንዲያው እመጣለሁ ኸረግ እናናዬ
አስካልዬን ብዬ

የእነዚህ ቃል ግጥሞች መነሻ ናፍቆት ነው፡፡ቃል ግጥሞቹ ተከታትለው የተከወኑ ናቸው። ሁሉም ቃል ግጥሞች አስካለን ፍለጋ ላይ ያተኩሩ ናቸው፡፡የመጀመሪያው ቃል ግጥም አስካለ አይንሽ ጥርስሽ ሁለመናሽ ሁሉም ቆንጆ ነው ማለት ሲሆን የሶስተኛው መንቶ ደግሞ እንዲ ያው ያለምንም ተግባር አስካለን ለማየት ብዬ እመጣለሁ የሚል ሀሳብ አለው።የሁለተኛው መንቶ ውስጣዊ ትርጉም ግን አሳዘንሽኝ ናፈቅሽኝ ማለት ነው።ኬላ የሚለው ተፈላጊዋ ሰው ያለችበት ቦታ እሩቅ መሆኑን ያመላክታል፡፡

በመጀመሪያው ቃል ግጥም ውስጥ ንፅፅር አለ፡፡የሷ ውበት ከሌላው ጋር እያወዳደረ መብለ ጡን ያሳያል፡፡በላይ በላይ የሚል ሀረግ ተደጋግሞ ይገኛል፡፡ይህ ድግግሞሽ የበለጠ ውበቷን ይገልፃል፡፡ዜማውን ለመምታትም ያገለግላል፡፡ከዋኜው ላይ ታዳሚው ቃል ግጥሙን የሚቀ በልበት ሁኔታ ደማቅ ነበር።

## ረ.የጀግንነት ቃል ግጥም

ቀጥሎ የቀረበው ቃል ግጥም ታዳሚውን በመቀስቀስ እንዲጨፍር የምታደርግበት ነው።የሰ ውን ወኔ እያነሳሳች ከዚህ ወደ እዚያ እየሄደች ታዳሚውም እየተከተለ የምትዘፍንበት የሰ

ርግ አውድ ነው።ችሎታዋን በመጠቀም በቃል ግጥሙ ውስጥ የሚያነሳሳ ቃላትን እየጨመረች እየተንቀሳቀሰች የተለያየ ብልሀት እየተጠቀመች ታስጨፍራለች።

ስድስቶ 01 ሀይሎጋ ሀይሎጋዬ ሆ ሀይሎጋ ሀይሎጋ ሆ
ሀይሎጋ ተዋጋ ብዬ ሀይሎጋ ሀይሎጋዬ ሆ
ሀይሎጋ ብሰጠው ጋሻ ሀይሎጋ ሀይሎጋዬ ሆ
ሀይሎጋ ለእናቱ ሰጣት ሀይሎጋ ሀይሎጋዬ ሆ
ኸረ ጎበዝ እህምለው ኸረ ወንዱ እህምለው
በለው በለው እህምለው

የእዚህ ቃል ግጥም መነሻ ወንድ አይደለህ በማለት ለጭፈራ መቀስቀስ ነው።በቃል ግጥሙ ውስጥ ኸረ ወንዱ ምን ነካህ የሚል አንድምታ አለው።ወንድ አይደለህ ምታው እንጂ እያለ የሚያደፋፍር የሚያነሳሳ ወደ ድርጊት የሚገፋ ቃል ግጥም ነው።አዝማሪዋ በምትከውንበት ሰአት አውቃ ወንዶቹን ሴቶቹ ወደ ሚጨፍሩበት ይዛቸው ትሄዳለች።በዚህ ወቅት ሴቱ ወንዱን ለመብለጥ አድምቆ ሲጨፍር ኸረ ወንዱ ትለዋለች።በዚህ ጊዜ ወንዱ በሴት መሸነፍ ስለማይፈልግ ላቡ ጠብ እስኪል አቧራው እስኪቦን ድረስ እየዘለለ ይጨፍራል።ስለዚህ ወንድ እና ሴት የሚሉ ተቃርኖዎች በቃል ግጥሙ ውስጥ መምጣታቸው አንድም የቃል ግጥሙን መልእክት ለማጉላት ሲጠቅም አንድም ለንፅፅር ጠቅሟል።እንዲሁም ጋሻ የሚባለው ጥንታዊ ቁስ ከጦርነት ጋር አብሮ የሚነሳ ነው።ስለዚህ የቃል ግጥሙን መልእክት ለማጉላት እንደ ንብርር ጠቃሽ ሆኖ የገባ ነው።

በቃል ግጥሙ ውስጥ ታዳሚው የሚቀበለው ሀይሎጋዬ ሆ የሚለው ቃል ተደጋግሞ ይገኛል።ይህም ለመቀባበል እና ለዜማ ምት ይጠቅማል።ቃል ግጥሙ በዜማ መልክ በማሲንቆ ታጅቦ አዝማሪዋን በመቀበል ይዘፈናል።የመከወኑም ፋይዳ መከወኑ ሰርግ ያደምቃል፣ያዝናናል፣ለመጨፈር ያነሳሳል፣ይሞገስበታል።

## ሰ.የሰርግ ቃል ግጥሞች

እነዚህ ቃል ግጥሞች ሙሽራዋን፣ሙሽሪትን እና የሙሽሮችን ቤተሰብ የሚያወደስ የሰርግ ዘፈን ነው።

ሶስቶ 01 አለምሽ ዛሬ ነው ዛሬ
አለምሽ ዛሬ ነው ዛሬ
አሆሆ እቴ ሙሽሬ

ሶስቶ 02 ለአባትሽ ደስ ይበላቸው
ለእናትሽ ደስ ይበላቸው
ኦሆሆ እቴ ልጃቸው

እነዚህ ቃል ግጥሞች በሰርግ ላይ ሙሽራ ለማጀብ የሚዘፈኑ ናቸው።ቃል ግጥሙ ሙሽራ ዋን ሙሽራውን እና የሙሽሮችን ቤተሰቦች ለማወደስ ይጠቅማሉ።የመጀመሪያው ቃል ግጥም ሙሽሪትን ሰርግ ተመልሶ አይመጣም።ስለዚህ ደስታሽ ወግ ማረግሽ ዛሬ ነው የሚል ይመስላል።ሁለተኛው ቃል ግጥም ደግሞ ባንቺ ለወግ ማእረግ መድረስ አባትና እናትሽ ደስ ይላቸዋል የሚል አንድምታ አለው።በሁለቱም ቃል ግጥሞች ውስጥ ሀረጋት በመደጋገም ለመልእክቱ አፅንኦት ለመስጠት፣ዜማ ለመምታት እና ሀሳቡን ለማጉላት ጠቅመዋል።በዚህ ጊዜ በሁሉም ዘንድ የነበረው የደስታ ስሜት ላቅ ያለ ነበር።

እንዲሁም ይህ ቃል ግጥም መተረኩ በዚህ ሰርግ አማካኝነት የተፈጠረውን ማህበራዊ አውድ ለማየት ያስችላል።

በአጠቃላይ የምግብ ግድየለውን ቃል ግጥሞች በባህል ምሽት ቤት ውስጥ የሚገጠሙ እና በሰርግ አውድ የሚከወኑ በማለት በሁለት አውድ ወገን ከፍለን ማየት እንችላለን።እነዚህ አውዶች ቀን፣ሰአት እና ቦታ ተቆርጦላቸው የሚከወኑ አውዶች ናቸው።በባህል ምሽት ቤት የተከወኑት ፍቅር፣ሀገር፣ጀግንነት፣ሀዘን፣ሙገሳ…ወዘተ ላይ ያተኮሩ ቃል ግጥሞች ናቸው።የእነዚህ ቃል ግጥሞች ክዋኔ እና የህይወት ታሪኩ በግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ አማካኝ ነት ሲተረክ እና ሲከወን ረቂቅ የሆነውን የአዝማሪዋን እና የማህበረሰቡን እም ነት፣አስተሳሰብ፣ባህል፣ምንነት፣የአዝማሪዋን ችሎታ የቃል ግጥም አደራረስ ችሎታ፣በአ ውዱ አማካኝነት የሚፈጠረውን ማህበራዊ መስተጋብር እና ቁርኝት አጠቃላይ ያለውን ፋይዳ እንዲታይ እንዲጎላ ይሆናል።

ከዚህ በታች ደግሞ ይህን መሰረት በማድረግ የአዝማሪ ማሾ ፋንታዬን የህይወት ታሪክ እና ስራዎቿን እተርካለሁ።

## 3.4. የአዝማሪ ማሾ የህይወት ታሪክ

አዝማሪ ማሾ ፋንታዬ በቡርቧክስ መወለዷ እና የአዝማሪ ምግብ ግድ የለው ዝናና ከበሬታ ወደ አዝማሪነት ህይወት ገና በአስራ አምስት አመቷ እንድትቀላቀል አድርጓታል።ነገር ግን ትዳር ከያዘች በኋላ ለተወሰነ ጊዜ ትታው ቆይታ ነበር።ሆኖም ግን ለምን ጥሩ ድምፅ እያ ለሽ አትዘፍኝም እያሉ በሚገፋፏት ሰዎች ምክንያት ተመልሳ በሙያዋ ተሰማራች።ሙያ ውን ከባለቤቷ ጋር በመለማመድ ከዚያም ራሷን ችላ በመስራት አሁን ወደ አለችበት የታዋ ቂነት ህይወት ተሸጋገረች።ይኼው የህይወት ታሪኳ ከእርሷ እንደበት በዚህ መልኩ ቀር ቧል።

> "በመጀመሪያ ከባለቤቴ ጋር አብረን እየዞርን ስንሰራ ቆይተን ከዚያ በኋላ የባህል ምሽት ቤት ውስጥ መስራት ጀመርን።በመቀጠልም ስራዬን እያዳበርኩ እየታወኩ ስሄድ አሁን አንደኛ በሆነው የባላገሩ የምሽት ቤት በመስራት ላይ እገኛለሁ ከቦታ ወደ ቦታ በምትሄድበት ወቅት ታክሲ ውስጥ ሰው አውቆኝ ይከፍልልኛል በዚህም ደስተኛ ነኝ።ስለዚህም ሙያውን ልጆቼን ለማስተማር ወስኛለሁ"።(ቃለ፣3፣2004)

ከላይ እንደተመለከትነው ባለቤቷም በዚሁ ስራ ተሰማርቶ እንደሚገኝ እንረዳለን።ሰርግ ላይ እንዲዘፍኑ በሚጋበዙበት ወቅት አብረው በመሄድ ነው የሚከውኑት።ይህቺ አዝማሪ ፈጥሮ የመግጠም ችሎታ ያላት፣ታዳሚውን በግጥሟ ማሳቅ ማዝናናት የምትችል እና እንደ ተፈጠ ረው አውድ መሆን የምትችል ሁለገብ አዝማሪ ናት።ይህን በተመለከተ የባህል እና ቱሪዝም ባለሙያ የሆነው አቶ አበባው እና የማህበሩ ሀላፊ አቶ ትእዛዙ ሲያስረዱ"ማሾ ያላት የስራ አክብሮት ሰውን የማዝናናት ችሎታዋን እና በየትኛውም ጨዋታ ላይ ገብታ መጫወት መቻ ሏን ይናገራሉ።"(ቃለ፣7፣2004) አዝማሪዋ ፈጥራ ከገጠመቻቸው መካከል ለምሳሌነት በባ ህል ምሽት ቤት ውስጥ ሴቶች ብቻ በርከት ብለው ተቀምጠው ሲዝናኑ ወደ እነሱ ጋር በመ ሄድ የገጠመችውን ማንሳት ይቻላል።

> እዚህ አከባቢ በጣም ታምራላችሁ<br>
> ታዲያ ምን ያደርጋል ቦይ ፍሬንድ የላችሁ።

አዝማሪዋ ቃል ግጥምን ፈጥራ ከመግጠምም ባሻገር ጊዜያዊ እና አንገብጋቢ ሁነት ላይ ተመርኩዛ በፍጥነት መግጠም የምትችል ናት።ትኩስ የሆነውን የማህበረሰብን እንቅስቃሴ የማንፀባረቅ ችሎታም አላት።እንዲሁም አውዱን ተመልክታ ወዲያው እንደ አውዱ የመሆን የመለዋወጥ ጥበብም አላት።በቦታው ምን መገጠም እንዳለበት የምታስተውል ነች።ለምሳሌ ስለ አባይ ፈጥራ ከገጠመቻቸው ቃል ግጥሞች መካከል ስንመለከት-

አባይ ጠመዝማዛ ሁሌ መንገደኛ
ያለፈው ይበቃል ተመለስ ወደ እኛ።

ይህ ቃል ግጥም በአሁን ሰአት የሰውን ትኩረት በሳበው የአባይ ወንዝ ላይ የተመሰረተ ነው ስለዚህ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ማተኮሯ ከጊዜው ጋር አብራ መጓዟን ያሳያል።በአሁን ሰአት ይህቺ አዝማሪ የአርባ ዘጠኝ እድሜ ባለ ፀጋ ስትሆን በእድሜ እንጋፋነት፣በሙያው ቀደምት ነት፣ደፍሮ በመጫወት እና ከላይ እንዳነሳሁት ታዳሚውን በማሳቅ የማዝናናት ልዩ ክህሎት ያላት አዝማሪ ናት።ለምሳሌ ሳቅ ከፈጠረችባቸው ቃላዊ ግጥሞቿ መካከል-

ሰው ሁላ ሞኝ ነው ለቁመት ይሳሳል
ወንድሜ እረጅም ነው ካሰበው ይደርሳል

ይህ ቃል ግጥም ባህል ምሽት ቤት ውስጥ ከሁሉም ጎላ ብሎ የሚታይ ሰውን እሷ ብቻ አስ ተውላ ባለችበት ቆማ ገጠመችበት።ታዳሚው ሁሉ እረጅም መፈለግ ጀመረ ልክ ሲመለከተው እሱን እየተመለከተ ይስቅ ነበር።ይህቺም አዝማሪ ልክ እንደ አዝማሪ ምግብ ግድ የለው ሁሉ በፊት የነበረው የማህበረሰቡ ዝቅተኛ አመለካከት ለስራዋ እንቅፋት ስለ ነበር መሰላቸት ነበረ ባት።አሁን ግን ይህ ሁኔታ በመለወጡ ካሴት እስከመስራት ድረስ እራዬዋን ሰንቃለች።"እኔ እቤት ውስጥ የሆነ ድግስ ኖሮኝ ልቀር ስል እንኳን ጎረቤቱ ሂጅ ወደ ስራሽ እኛ እንሰራዋለን ይሉኛል"በማለት የማህበረሰቡን ለውጥ ከታሪኳ ጋር አያይዛ ትናገራለች።(ቃለ፡፡3፡2004)ይህን በፊት የነበረውን አሳንሶ የማየት ሁኔታ መለወጡን በቃል ግጥሟም አንፀባርቃዋለች።

ከእንግዲህ ወዲህ አንገት መድፋት ቀርቷል
በኢህአዴግ እኩልነት መጥቷል

ከላይ የቀረበው ቃል ግጥም የገጠመችው በፊት በምሰራበት ወቅት እቆነጠጥ ነበር።አንቺ አዝማሪ እየተባልኩ እሰደብ እገለል ነበር።አሁን ግን ኢህአዴግ ከመጣ በኋላ እኩልነት ስላለ ሁኔታው እየተለወጠ ማህበረሰቡም ለሙያው ያለው ግንዛቤ እያደገ መጣ በማለት ትናገራ ለች።ከዚህ በመነሳት ይህንን ቃል ግጥም ገጥማለች።በአሁን ሰአት ለሙያዋ እንደ ትልቅ ችግር የምታነሳው ነገር ቢኖር ያለመማሯ ጉዳይ ነው።"አንድ የሚቆጨኝ ነገር ቢኖር ግጥሞ ቼን ባለመማሬ ምክንያት የሆነ ነገር ተመልክቼ እገጥምና መፃፍ ስለማልችል እረሳዋለሁ። ይህ ደግሞ ለስራዬ እንቅፋት ሆኖብኛል በማለት ሁኔታውን ትተርካለች።(ቃለ፣3፣2004)

ከዚህም ባሻገር አዝማሪዋ ያለምንም ቅብብል ብቻዋን መቆም ትችላለች።በአብዛኛው ግጥምን የምትደርሰው ከአዝማሪ ምግብ ግድ የለው ጋር በተመሳሳይ መልክ እና ሁኔታ ነው።በአዝ

ማሪነት ሙያ ውስጥም ለበርካታ አመታት በማሳለፏም ለሌሎች አርአያ በመሆን ተመክሮ ዋን ታካፍላለች።በዚህም ለባህላዊው ሙዚቃ ቀጣይነት የራሷ የሆነን አንድ አሻራን አሳርፋ ለች።ሌሎች የእርሷን አከዋወን እና አደራረስ በመመልከት እንዲቀጥሉ በማድረግ ምሳሌ በመሆን ድርሻዋን በመወጣት ላይ ትገኛለች።"ሌሎች አዝማሪዎች የኔን የአገጣጠም ስልት ተከትለው ይገጥማሉ።የኔን ቃል ግጥም ይገጥማሉ።በዚህም ለሙያው ቀጣይነት አስተዋፅኦ አበርክቻለሁ"በማለት ትናገራለች።(ቃለ፤3፤2004)

ስለ እውቅናዋ ስለሺ የተሰኘ አዝማሪ ሲናገር"ማሽም በአሁን ሰአት እውቅናዋ እንዳለ ሆኖ አብራን እየሰራች ትገኛለች"በማለት ስለ እርሷ ማንነት ይናገራል።(ቃለ፤7፤2004) በአጠቃላይ አዝማሪዋ በተለይ በአሁን ሰአት በሙያዋ እጅግ ስለምትኮራና የማህበረሰቡ ድጋፍ ስላልተለ ያት እና በዚህ ሙያ በበለጠ ለመታወቅ በርትታ እስከ መጨረሻ ለመስራት ቆርጣ ተነስታ ለች"ከዚህ በኋላም በቃሽ እስከምባል ድረስ ስራዬን አለቅም አልተውም"።በማለት ትናገራለች። ይህን እንድትል ያደረጋት ከተስፋ መቁረጥ ያላቀቃት እና ያበረታት በለውጥ ሂደት ላይ ያለው የማህበረሰቡ የግንዛቤ ነው።

ይህቺም አዝማሪ የህይወት ታሪኳን በምትተርክበት ሰአት የምትጠቀመው ቋንቋ መካከለኛ ሲሆን የህይወት ታሪኳን እና ገጠመኟን በሚገባ አቀናጅታ ትናገራለች።ቃል ግጥሞቿንም በተገቢው ጣልቃ በማስገባት ትከውናለች።በምእራፍ ሁለት ንድፈ ሀሳብ ላይ እንዳነሳሁት የተረክ ቲወሪ ከራስም ባለፈ ስለህብረተሰቡ መንገሪያ በመሆኑ አዝማሪዋ የህይወት ታሪኳን ስትተርክ ከዚህ ቀደም እንዳነሳኋቸው አዝማሪዎች በተያያዥነት ማህበረሰቡ ለእ ዚህ ሙያ ያለውን የበፊቱን እና የአሁኑን አመለካከት፡ይህም ዝቅተኛ የሆነ አመለካከት የሚያደርስባቸውን ስነ ልቦናዊ ተፅእኖ፣ማህበረሰቡ ለሌሎች ያለውን አተያይ፣የማህበረሰቡ ንም ሆነ የራሷ ማንነት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ትገልፃለች።

በአጠቃላይ ይህች አዝማሪ ፈጥራም ይሁን ደግማ የምትገጥማቸው ቃል ግጥሞች አንዳን ዶቹ ከህይወት ተመክሮዋ ጋር የተቆራኙ፤ከሁኔታዎች እና ከአውዱ ጋር የተዋሀዱ ናቸው። እንዲሁም የተለያየ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ናቸው።ስለዚህ ከዚህ በታች በምእራፍ ሁለት ንድፈ ሀሳብ (ቲወሪ) ላይ እንዳነሳሁት የዚችን አዝማሪ አጠቃላይ ሁለንተና በበለጠ ለመገንዘብ እና ይህን ሁኔታ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ የከወነቻቸውን ቃል ግጥሞች ከህይወት ታሪኳ ጋር በማቀናጀት ክዋኔዉን፡አዉዱን እና ፋይዳዉን እመለከታለሁ።

ከአዝማሪ ማሾ ፋንታዬ ሰአት በተፈጥሮአዊ እና በአርቴፊሻል መቼት በባህል ምሽት ቤት ስትከውን እና ቃለ መጠይቅ በማደርግ ቃል ግጥሞችን ሰብስቤአለሁ።አብዛኛዎቹ ቃል ግጥ ሞች አባይ፣ሙገሳ፣ትችት፣አሽሙር፣ሴቶች፣ሀገር…ወዘተ ላይ ያተኮሩ ናቸው።ከነዚህ ቃል ግጥሞች መካከል ለማሳያነት የሚሆኑትን በመምረጥ ከዚህ በታች እተነትናለሁ።የአዝማሪ ወርቁ እና የምግብን ቃል ግጥሞች ከመተንተኔ በፊት አጠቃላይ የባህል ምሽት ቤት እና የሰርግ አውዳዊ ክዋኔ ምን እንደሚመስል አንስቻለሁ።በመሆኑም በዚህ አጠቃላይ አውዳዊ ክዋኔ ላይ በመመርኮዝ እና እንደ አስፈላጊነቱ የየራሳቸውን አውድ በተጨማሪነት በማሳየት እና በምእራፍ ሁለት የተገለፀውን ንድፈ ሀሳብ ላይ በመመስረት የምተነትንን ይሆናል።

## ሀ.ስለ አባይ የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

ከዚህ በታች የቀረበው ቃል ግጥም በአባይ ወንዝ ላይ ፈጥራ የገጠመችው ቃል ግጥም ነው ይህ ቃል ግጥም የአባይን መከታነት አመላካች ነው።

አራቶ 01. ውጭ መሄድ እንግዲህ ለምናችን
ዱባይም መሄድ እንግዲህ ለምናችን
ሱዳንም መሄድ እንግዲህ ለምናችን
አባይን ገድበን እናለማለን።

ቃል ግጥሙ የተገጠመው ከህዳሴው ግድብ ጋር በተያያዘ ህዝቡን ለመቀስቀስ ነው።የቃል ግጥሙ መልእክትም ከዚህ ወዲህ በስው ሀገር መንከራተት አበቃልን።አባይን ገድበን በምናገ ኘው ገንዘብ ሀገራችንን እናያለማን ሀገራችን ስታድግ እኛም እናድጋለን የሚል ሀሳብን የያዘ ነው።በቃል ግጥሙ ውስጥ ተስፋን እናነባለን።እንዲሁም ለግድቡ ስራ መቀስቀስን እንመለከ ታለን።

ለምን እነዚህ ሀገራት በቃል ግጥሙ ውስጥ መጡ ስንል ስራ ፍለጋ ሰው የሚሄደው ወደ አረብ ሀገራት ነው።ይህን ያመጣብን ደግሞ ድህነታችን ነው።ስለዚህ አባይ ሲገደብ ከድህነት እንላቀቃለን ነው።እንዲሁም በዚሁ ቃል ግጥም ውስጥ የሚደጋገሙ ሀረጋትን እናገኛለን። ሀረጋቱ ቃል ግጥሙ ውስጥ መደጋገማቸው ከዚህ በኋላ የአባይ ግድብ ስላለልን የውጭ እር ዳታን አንፈልግም የሚለውን ሀሳብ ለማጉላት አፅንኦት ለመስጠት ነው።በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ የአባይ ግድብ እንዳለ ሆኖ በውስጠ ታዋቂነት ግን ከስለማህበረሰቡ ኢኮኖሚ እንድናይ ያደርገናል።ማለትም የማህበረሰቡን የኢኮኖሚ ዝቅተኛነት አመላካች ነው።

ምክንያቱም የአባይ ወንዝ ግድብ እንደ ችግር መሳቀቂያ መፍትሄነት ስለ ተቀመጠ።ሌላው አዝማሪዋ ይህን ቃል ግጥም እንድትገጥም ያደረጋት የልጇ ወደ አረብ ሀገር መሄድ በራሱ አንድ አስተዋፅኦ አለው።ስለዚህ የአዝማሪዋ ኑሮ እና ቃል ግጥሙ ተያያዥነት ያላቸው ነገሮች ናቸው።ይህ ቃል ግጥሙ መተረኩ ታዳሚውን ስለዚህ ጉዳይ እያዝናኑ ለማስተማር እና ለማነሳሳት ይጠቅማል፡፡ቃል ግጥሙ ሲከወን የታዳሚው አቀባበል ላቅ ያለ ነበር።ምክን ያቱም ሀገራዊ ስሜት ስለሚያድርበት ነው።

## ለ.የሙገሳ ቃል ግጥሞች

በዚህ ርእስ ስር የቀረቡ ቃል ግጥሞች ማንነትን፣ቁመናን በማሞገስ በማወደስ ላይ የተመሰ ረቱ ናቸው።

መንቶ 01 አንደበተ መልካም የተደላደለ
አጥተነው ቢሆን ይቆጨን ነበረ፡፡

ሶስቶ 02 የውጩ ካምፓኒ እኛ ለምናችን
የውጩ ድርጅት እኛ ለምናችን
የኔማ እንትናዬ የጀርባ አጥንታችን፡፡

ሁለቱም ቃል ግጥሞች ለማሞገስ ተብለው የተገጠሙ ናቸው፡፡የመጀመሪያው መንቶ ሀሳብ አንደበተ ርቱእ የሆነ፣ተደማጭነት ያለው የተረጋጋ ሰው ማለት ነው፡፡ይህን የመሰለ ሰው የኛ ባይሆን ኖሮ ተናደን አይወጣልንም ነበር የሚል አንድምታም ያለው ይመስላል።ሁለተ ኛው ቃል ግጥም ደግሞ የጀርባ አጥንታችን በሚለው ሀረግ አማካኝነት ሁለት ትርጉም የያዘ ነው።ቀጥታ ትርጉሙ ሰውየው ለእኛ የጀርባ አጥንት ነው የሚል ሲሆን በውስጥ ታዋ ቂነት ግን ደጋፊያችን መመኪያችን አለኝታችን ነው ማለት ነው፡፡ስለዚህ እሱ ስላለን ለልመና እጃችንን ወደ ሌላ ሀገር አንዘረጋም የሚል ይመስላል፡፡እንዲሁም የራሳችን ሀገር ተወላጅ ለኛው መከታ ይሆነናል የሚል ድምፀት ያለውም ይመስለኛል።ስለዚህ እራሳችን ሀገራችንን ባለን ነገር እናልማ እንደግፍ የሚል ይመስለኛል።

የመረዳዳትን ባህልን እናዳብር እናሳድግ የሚል ነው።የማነሳሳት የመገፋፋት ሁኔታ ይታ ያል።ከላይኛው ቃል ግጥም በተመሳሳይ መልኩ የሀረጋት ድግግሞሹ መልእክቱን ለማጉላት ይጠቅማል።ቃል ግጥሙ ውስጥ የአገር እድገት ልማት ይነበባል፡፡ቃል ግጥሙ ሙገሳዊ ስለ ሆነ ታዳሚው እና የተገጠመለት ሰው ደስታውን በጭብጨባ እና በሽልማት ደስታውን ይገ

ልፃል።ይህም ሲሆን በተሞገሰችው ውስጥ የተፈጠረውን ስሜት ከሁኔታዋ ለመረዳት እስ ችሏል።

መንቶ 02 ዝቅ ብል ምድር ነው ቀና ብል ሰማይ
ከወንድሜ ወዲያ ሰው ይገኛል ወይ።

ቃል ግጥሙ የተገጠመው በምሽት ቤት ውስጥ ነው።የቃል ግጥሙ መነሾ ከታዳሚው ውስጥ ከሁሉም እረጅም የሆነ ሰው በማየቷ ነው።የቃል ግጥሙ ትርጉም በቁመናው እሱን የሚያክል አለ ወይ ማለት ሲሆን ሌላው ትርጉሙ ወንድሜን የመሰለ ሰው የትም ብሄድ አላገኝም ማለት ነው።በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ ተፈጥሮአዊ ነገሮችን እናገኛለን።ሰማይ እና ምድር በቃል ግጥሙ ውስጥ መምጣታቸው የሰውዬውን ቁመና እርዝመት በዚህ መስሎ ለማሳየት ነው።ለምሳሌ ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ማለት እረጅም ፎቅ ማለት ነው።ስለዚህ ከሰማይ እስከ ምድር ያለውን እርቀት በማሳየት የልጁን እርዝማኔ ማሳየት ነው የተፈለገው።በዚህም የሱ ቁመና ከምድር እስከ ሰማይ ባለው ርዝመት ሲመሰል ሲነፃፀር ይታያል።ነገር ግን ይህ ንፅፅር ግነት ያለበት ይመስለኛል።

ቃል ግጥሙ ሲከወን ታዳሚው የተገጠመበትን ሰውን በመመልከት ይስቃል።ቃል ግጥሙ መከወኑ መተረኩ ለመዝናናት እና ለማሞገስ ይጠቅማል።ምክንያቱም ቃል ግጥሙ ሲገጠም ሰው እሱን እያየ ይስቅ ነበር።

## ሐ.የአሽሙር ቃል ግጥሞች

እነዚህ ቃል ግጥሞች አዝማሪዋ ከሷ ጋር ለሚከውነው አዝማሪ ለመመለስ እሱ የሚለውን ሰምታ ወዲያው በፍጥነት ፈጥራ የምትገጥማቸው ናቸው።በዚህ የፈጠራ ፍጥነቷን ማየት ይቻላል።

አራቶ 01 አቤት ወግ መልክና ቁመና(ወንዱ)
አሟልቶ ካልሰጠሽ ምን ዋጋ አለውና
የሚቻል ከሆነ ለሀኪም ንገሪና
ካስተካክሉልሽ በቀዶ ጥገና

አራቶ 02 እኔ የምወድህ በቁመትህ ነው(ሴቷ)
እኔ የምወድህ በቁመናህ ነው
እኔ የምወድህ በማሲንቆ እያያዝህ ነው
ከወገብህ በታች ሁለመናህ የሞተ ነው።

ሶስቶ 03     እንቺ ምትወጅው የነገንጉርን ነው(ወንዱ)

እንቺ የምትወጅው የነታከለን ነው

እኔ ላንቺ ስልስ አህያ ልሆን ነው።

ሶስቶ 04   የዚህን ልጅ ነገር እኔ ነኝ የማውቀው

የዚህን ልጅ ታሪክ እኔ ነኝ የማውቀው

እንኳንስ ያህያ የሰውም የለው።

እነዚህ ቃል ግጥሞች ሴቷ አዝማሪ እና ወንዱ አዝማሪ በአንድነት ሁነው በቅብብል እየተመ ላለሱ በአሸሙር የሚሰዳደቡት ነው።የመጀመሪያው ቃል ግጥም መልክ እና ቁመት ስለሌለሽ ከተቻለ በቀዶ ጥገና አስተካክይው የሚል ሲሆን ሁለተኛው ቃል ግጥም ደግሞ አንተን እኔ እንድወድህ ያደረገኝ ቁመናህ፣ማሲንቆ አያያዝህ እንጂ ሌላውን ሁኔታህን አልወደውም ማለት ነው።ሶስተኛው ቃል ግጥም ደግሞ መልእክቱ አንቺ መተኛት የምትፈልጊው ከነታከለ ጋር ነው።እኔን አትወጅኝም(ሴሰኛ) ነሽ ማለት ነው።አራተኛው ቃል ግጥምም ከላይ ካለው ሀሳብ ጋር በተያያዘ መልኩ እሱ እንደ እንደሚለው ሳይሆን ምንም የለውም የሚል ነው።

ይህ ቃል ግጥም አዝማሪዎቹ ሊከወን የቻለበት ጉዳይ ማህበረሰቡ ግልፅ አድርጎ የማይናገ ረው ነገር ግን ለጋብቻ መፍረስ የሚሆን ትልቅ ችግር በመሆኑ ነው።በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል የሚፈጠር ያለ መጣጣምን ሁኔታ አመላካች ነው።ስለዚህ ይህ ቃለ ግጥም በሚከ ወንበት ወቅት ሰው በመዝናናት ስለዚህ ጉዳይ ይፋ አውጥቶ በመንገር ለስተማር ነው። ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር የተያያዘ ነው።በቃል ግጥሙ ውስጥ ለዋጭ ዘይቤ አለ።ሰው የነበ ረው ወደ አህያነት የመለወጥ ሂደት አለ።እንዲሁም በአህያው እና በሰውየው መካከል ንፅፅር አለ።እንዲሁም ከቃለ ግጥም ሁለት እስከ ቃል ግጥም አራት ድረስ የሀረጋት ድግግሞሽ እናገኛለን።ለምን አስፈለገ ስንል ንፅፅር ለመፍጠር የገባ ነው።ለምሳሌ የሁለተኛውን መንቶ ስንመለከት የምትወድለትን በመደጋገም በመንገር በደንብ ካስረገጠች በኋላ የምትጠላውን ነገር ስታነሳና ስታወዳድር በግልፅ ሁኔታውን ማሳየት ይቻላል።ማለትም ጨለማን በደንብ ለማወቅ ብርሀንን ማየት አስፈላጊ ነገር ነው።ይህ ደግሞ በተደበቀው አለም ውስጥ የሚሆነውን ጉዳይ ታዳሚውን እያሳቁ፣እያዝናኑ እና እያዋዙ ለመጫን ለማረቅ የሚያደርጉት ነገር ነው።

ይህ የቃል ግጥም የተከወነው በባህል ምሽት ቤት ሲሆን ከዋኔ አውዱ በተመሳሳይ ሁኔታ ይከወናል።ቃል ግጥሙ መከወኑ እና መተረኩ በምእራፍ ሁለት በንድፈ ሃሳቡ ላይ እንደተን

ሳው ድብቅ የሆነውን የሰው ልጆችን ችግር በማጉላት የትኛውንም ችግር በግልፅ መነጋገር ተገቢ መሆኑን ለማስተማር ይረዳል።

## ሠ.የጀግንነት ቃል ግጥም

ይህ ቃል ግጥም ደግሞ ማሞገስ እና ማሳቅ ላይ የተመሰረተ ነው።ካለው የታዳሚው ፍላጎት አኳያ አላማውን ግብ እንዲመታ ተደርጎ የተገጠመ ነው።

ሶስቶ 01 ሁለት ደና ተኳሽ የሚሆነውን
ሁለት ደና ጀግና የሚሆነውን
አንድ አድርገው ፈጠሩት ወንድሜ ሆዬን።

ይህ ቃል ግጥም የተገጠመበት ምክንያት ጀግናን ለማወደስ ነው።የቃል ግጥሙ መልእክት ደግሞ ይህን መሳይ ጎበዝ ጀግና አንድ ብቻ ሆኖ ተፈጠረ መንታ ቢሆን ኖሮ የሚል አንድ ምታ አለው።የሱ ጀግንነት ከአንድ ሰው ይበልጣል አንድ ሰው አያክለውም ማለት ነው። በቃል ግጥሙ ውስጥ ንፅፅራዊ ዘይቤን እናገኛለን።እሱ ከሁለት ሰው ጋር ይወዳደራል።እንዲሁም ቃል ግጥሙ የጀግና ግጥም እንደሆነ የሚጠቁሙ ተኳሽ ጀግና የሚሉ ቃላቶችን እናገኛለን።ቃል ግጥሙ መከወኑ ለማዝናናት፣ለማሞገስ እና ለሽልማት ያበቃል።ምክንያቱም ይህ ቃል ግጥም የተገጠመለት ሰው ይሸልማል።እንዲሁም ቃል ግጥሙ መተረኩ ማህበረሰቡ ለጀግና ሰዎች ያለውን አተያይ ለማወቅ ያስችላል።ቃል ግጥሙ የተገጠመው በባህል ምሽት ቤት ውስጥ ዜማዊ በሆነ ቅኝት ነው።

### ረ.ስለ ሴቶች የተገጠሙ ቃል ግጥም

ከዚህ በታች የቀረቡት ቃል ግጥሞች ደግሞ በሴቶች ተሳትፎ ላይ ያተኮሩ ናቸዉ።

መንቶ 01 የአምስት አመት እቅድ አልቀረም ተለፍቶ
መጣ እየጨመረ የሴቶች ተሳትፎ።

መንቶ 02 ይሄ ተሳትፎአችን ይቀጥል ካላችሁ
ሂሳቡንም ሼር ሼር እያደረጋችሁ።

የሁለቱም መንቶዎች መገጠም በባህል ምሽት`ቤት ውስጥ ሴቶችን መመልከቷ ነው።እነዚህ መንቶዎች ተከታትለው የሚከወኑ ናቸው።የመጀመሪያው መንቶ እንድም በዚህ በአምስቱ

አመት እቅድ መሰረት ሴቶች በየትኛውም ነገር ላይ ተሳታፊ እንደሆኑ ያመላክታል።እናም ይህ የአምስት አመት እቅድ ተግባራዊ እንዲሆን በመደረጉ ውጤታማ እየሆነ መጣ የሚል ይመስለኛል።ዋናው ምክንያት ግን ቀደም ሲል ወደ ባህል ምሽት ቤት የሚመጡ ጥቂት ሴቶች ብቻ ነበሩ።አሁን ግን ቁጥራቸው ተበራክተ ለማለት ነው።ሁለተኛው መንቶ በመጀመ ሪያው ላይ በመመስረት ይህ ተሳትፎ እንዲቀጥል ከፈለጋችሁ፣መዝናናት ከፈለጋችሁ የሽል ማቱንም ነገር እያሰባችሁበት የሚል ነው።

በእነዚህ መንቶዎች ውስጥ ሴት ልጅ ቀደም ሲል በፖለቲካው፣በትምህርቱ…የነበራት ተሳ ትፎ አነሳ እንደነበር ያሳያል።ይህም የሆነበት የሀገራችን ባህል ስለማይፈቅድ ነበር።አሁን ግን ይህ ሁኔታ መቀየሩን ያመላክታል።ስለዚህ ቃል ግጥሙ መከወኑ እና መተረኩ ማህበረ ሰቡ ራሱ አምኖበት የሚቀይረውን ወይም የሚያሻሽለውን ባህል ለማየት ያስችላል ማለት ነው።ሌላው ደግሞ በዚሁ መንቶ ውስጥ ሼር የሚል የእንግሊዘኛ ቃል እናገኛለን። ቀጥታ ትርጉሙ ድርሻ ማለት ሲሆን ቃሉን በአውዱ ስንፈታው ግን ገንዘቡን በማዋጣት ለመስጠት ለመሸለም በዛው እያሰባችሁበት ማለት ነው።ታዳሚው ቃሉን በመደጋገም እንዲ ሰማው ተደርጓል።

በዚህ ወቅት ወንድ እና ሴት ታዳሚዎች በተመሳሳይ መልኩ በመሳቅ ምላሽ ሲሰጡ ነበር።ቃል ግጥሙ መተረኩ በሴት ልጅ ተሳትፎ ላይ ያለውን የማህበረሰቡን የለውጥ ሁኔታ ለመመልከት ያስቻለ ነው።

## ሠ.ስለ ሀገር የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

እነዚህን ቃል ግጥሞች ደግሞ አዝማሪዋ ስለ ሀገር እድገት ፈጥራ የገጠመቻቸው ቃል ግጥሞች ናቸው።

መንቶ 01 አገራችን ትደግ እንበርታ በእውነቱ
የሰው ምን ያደርጋል ከኛ እያለ ሀብቱ

የቃል ግጥሙ መነሻ ስራ እንስራ ለማለት ነው።የስራ ወኔን ለመቀስቀስ የተገጠመ ነው።የግ ጥሙ መልእክት ኢትዮጵያ ሀገራችን ከዚህ የበለጠ እንድታድግ በመበርታት ለለውጥ ታጥ ቀን እንስራ የሚል ነው።የሰው ብንመኝ የሰው ነገር ሁልጊዜም የሰው ነው።የሰው ወርቅ አያደምቅ እንደሚባለው የራሳችን ይሻለናል የሚል ነው።ሀገራችን ምንም አልነፈገችንም በርትተን ከሰራን የማንለወጥበት ምንም ምክንያት የለም ነው።

ከዚህም በተጨማሪም ወደ ሌላ ሀገር ከምንሄድ በሀገራችን ላይ ሰርተን እንደግ የሚል ሀሳብ ያለው ይመስለኛል።ቃል ግጥሙ የተከወነው በንግግር ሲሆን ሰው ባለው ነገር ኮርቶ እና በርትቶ በመስራት ህይወቱን እንዲቀይር ለስራ ለማነሳሳት ይጠቅማል።

መንቶ 01 አገሬ ኢትዮጵያ የተባረከች
አሁን ሰው አግኝታ በጣም አድጋለች

ይህም ቃል ግጥም እንደ ላይኛው ቃል ግጥም መነሻ ሀገርን ለማሞገስ ነው።የቃል ግጥሙ መልእክት ኢትዮጵያ ጠንካራ ሰራተኛ ለሀገሩ ተቆርቋሪ ሰው በማግኘቷ አድጋለች ማለት ነው።የቀረበው በንግግር መልክ ነው።ማህበረሰቡ አሁን ያለበትን እና እየተጋ ባለው ሀገርን የማልማት ትግል የበለጠ በርትቶ እንዲቀጥልበት ለማበረታታት የተገጠመ ነው።በተቃራኒ ደግሞ አሁን ሰው አግኝታ በሚለው ሀረግ በፊት በነበሩት መንግስታት የነበረውን የልማት እንቅስቃሴ መቃወሙን እንመለከታለን።

እንዲሁም እስከ ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያ ያላደገችው ከሌላው ያነሰ ተፈጥሮአዊ ሀብት ኖሯት ሳይሆን በርትቶ የሚሰራ ሰው ባለማግኘቷ ነው።አሁን ግን ጠንካራ ሰራተኛ ስላገኘች ተለው ጣለች የሚል አንድምታ ያለው ይመስለኛል።በዚህ የቃል ግጥም ትረካም አማካኝነት ማህበ ረሰቡ ስለ ሀገር እድገት ያለውን አመለካከት ለማየት ያስችላል።

## ሬ.የፍቅር ቃል ግጥም

ይህ ቃል ግጥም ደግሞ ቀጥተኛ የሆነ ፍቺ ብቻ ያለው ነው።ለማሳቅ፣ለማዝናናት ተብሎ የተገጠመ ቃል ግጥም ነው።

አራቶ 01 እንኳን ያንተ ፍቅር አንቺን ማመኔ
ተጨምሮበት አንቺን ማመኔ
እንዴውም ይሞቃል አንቺን ማመኔ
ሰኔ እና ግንቦት አንቺን ማመኔ

የዚህ ቃል ግጥም መነሾ ያንተ ፍቅር ይቅርብኝ ማለት ነው።የቃል ግጥሙን መልእክት በቀ ጥታ ስንመለከተው የግንቦት ወር ሙቀት አስቸግሮኛል እንኳን ያንተ ፍቅር ተጨምሮበት ለማለት ነው።በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ የፍቅርን ሙቀት ከሞቃታማ ወራቶች ጋር ሲያመ ሳስል ሲያወዳድር ያሳያል።ስለዚህ ወራቶቹ የቃል ግጥሙን ሀሳብ ይበልጥ ለማጉላት ይጠቅ ማሉ።

አንቺን ማመኔ የሚባለው የሀረግ ድግግሞሽ በአቧ አባባል በመናደድ ድሮስ የሚል የትዝ ብት አይነት ንግግር ነው።በዚህም የሱን ቅየማ ክብደት ሀይለኛ መሆኑን ያመላክታል። የቀረበው በዜማ በማስንቆ እና በታዳሚው ጭብጨባ ታጅቦ ነው፡፡ታዳሚው አዝማሪዋን እየ ተቀበለ አንቺን ማመኔ እያለ ያጅባል፡፡

## ሰ.የሰርግ ግጥም

ይህ የቃል ግጥም አዝማሪዋ አስታውሳ በመድገም ሲሆን የሚከወነውም በሰርግ አውድ ውስጥ ነው።

አራቶ 01 የወይን አበባዬ የወይን
የወይን አበባዬ የወይን
የወይን አበባዬ የወይን
እኛ ካላንተ ማን አለን

ይህ ቃል ግጥም ሙሽራውን ለማሞገስ ይጠቅማል፡፡ቃል ግጥሙ ቁንጅናውን ለማሳየት የተ ገጠመ ነው፡፡በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ ተለዋጭ ዘይቤ እናገኛለን።ሙሽራውን በወይን አበባ መተካት አለ።ቃል ግጥሞች ውስጥ ሀረጋት እየተደጋገሙ ለመልእክቱ አፅእኦት ለመስጠት፣ ዜማ ለመምታት እና ሀሳቡን ለማጉላት ገብተዋል።በዚህ ጊዜ በታዳሚው ዘንድ ያለው የደ ስታ ስሜት ላቅ ያለ እንደ ነበር በአውዱ ላይ ተገኝቼ ለመመልከት ችያለሁ፡፡

ታዳሚውም እየጨፈረ እስክስታ እየመታ እየሳቀ እያጨበጨበ በደስታ ነው ሲከወን ነበር። ቃል ግጥሙ በዜማ መልክ በማሲንቆ ታጅቦ በቅብብል መልክ እና በአንድ ላይ በመሆን ይዘ ፈናል።ቃለ ግጥሙ መከወኑ ሰርግ ያደምቃል፣ያዝናናል ይሞገስበታል፡፡እንዲሁም በዚህ ሰርግ ክዋኔ አማካኝነት ማህበራዊ አውድን ለመፍጠር ያስችላል።ስነ ልቦናዊ እርካታን ለማ ምጣት ያስችላል።

እንግዲህ ከዚች አዝማሪ የቃል ግጥሞቹን የተሰበሰቡት በባህል ምሽት ቤት ስትከውን እና ቃለ መጠይቅ በማድረግ ነው።እነዚህ ቃል ግጥሞች ስለ ሀገር፣ስለ ሴቶች፣ስለ ፍቅር፣ስለ ጀግንነት፣ስለ አባይ ወንዝ ግድብ...ያተኮሩ ሲሆኑ ቃል ግጥሞቹ መከወናቸውም ያላቸውን ማህበራዊ፣ስነልቦናዊ፣ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ለመመልከት ያስቻለ ነው።

በተከታታይ የተነሱት እነዚህ ሶስት አዝማሪዎች ይህንን የአዝማሪነት ሙያ የተለማመዱበት መንገድ በህይወት ታሪካቸው እንዳየነው የተለያየ ነው።ነገር ግን የሁሉም ለመዳ እንዱ ሌላ ላውን በመመልከት ላይ የተመሰረተ ነው።ይህም ማለት ለምሳሌ አንዱ አዝማሪ የሚለውን ቃል ግጥም በመስማት እና በመያዝ ያንን ደግሞ ደጋግሞ በመለማመድ ሌላ ጊዜ ለቦታው ምቹ ሆኖ ሲያገኝ በመቀኘት ነው።ይህንን የሚያደርጉት በመጀመሪያ ከነባር አዝማሪያን ጋር አብረው በመሆን በየጠጅ ቤቱ፣በየሰርግ ቤት ውስጥ በመሄድ ሲሆን በመቀጠል ደግሞ እየተለ ማመዱ ሄደው መታወቅ ሲጀምሩ በባህል ምሽት ቤት ውስጥ እየተከፈላቸው ተቀጥረው ይከ ውናሉ።

እንዲሁም በእነዚህ አዝማሪያን በኩል ከተሰበሰቡት ቃል ግጥሞች ውስጥ አንዳንዶቹ ከህይ ወት ታሪካቸው ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ስራዎቻቸውን እና የህይወት ታሪካቸውን እያ ይገፄ በበለጠ ስለ እነርሱም ሆነ ስለ ማህበረሰቡ ለማየት አስችለውኛል።አዝማሪዎቹ የሚገ ጥሙትን ቃል ግጥም ሌላው ሰው የሚለውን ሰምተው በመያዝ በመሸምደድ እና ለቦታው እና ለአውዱ ተገቢ እና ተስማሚ ሆኖ ሲያገኙት አስታውሰው በመድገም ይጫወቱታል። ወይም በሌላ በኩል ደግሞ ያንን ቃል ግጥም አሻሽለው፣ቀንሰው ወይም ጨምረው ይቀኙ ታል።ከዚህ በተጨማሪም የዚያን ቃል ግጥም ሀሳብ በመያዝ የራሳቸውን ሌላ አዲስ ቃል ግጥም ይፈጥራሉ።እንዲሁም የአውዱን ሁኔታ በማየት ይፈጥራሉ።

በዚህ መሰረት ይህን የማህበረሰብ መገለጫ የሆነውን ቃል ግጥም ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል እየከወኑ ያስተላልፋሉ።በዚህ መልኩ የሚደረሱት እነዚህ ቃል ግጥሞች መከወናቸው መተረካቸው ረቂቅ የሆኑ የማህበረሰቡ እምነቶች፣አመለካከቶች፣ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች፣ ማህበራዊ መስተጋብሮች፣ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊ ሁነቶች፣ባህሎች እና አጠቃላይ የማህበ ረሰቡ መገለጫዎች ጎልተው ሊታዩ ችለዋል።

ስለዚህ በምእራፍ ሁለት ውስጥ እንደተነሳው ንደፈ ሀሳብ የህይወት ታሪክን ከቃል ግጥ ሞቹ ጋር በማያያዝ ማጥናት የበለጠ ስለነገሩ ያለን ግንዛቤ እንደሚሰፋ ያደርገናል።እን ዲሁም ቃል ግጥሞቹም ሆኑ የህይወት ታሪኩ መተረኩ ከላይ እንዳነሳሁት ረቂቅ የሆኑት የሰው ልጅ አመለካከት፡ፍቅር፡እምነት…ጎልተው የሚታዩ እንዲሆኑ ያደርጋል።ስለዚህ በመከወናቸው እንዲታዩ ሆኗል።እንዲሁም በመከወናቸው በሚፈጠረው አውድ አማካኝነ ነት ማህበራዊ ግንኙነትን ለመመስረት፡ስነ ልቦናዊ ደስታን ለማግኘት፡ትምህርት ለመቅ ሰም፡ለማበረታታት… ወዘተ አስችሏል።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

እንዲሁም ለዚህ ጥናት ግብአትነት የተሰበሰቡት አብዛኛዎቹ ቃል ግጥሞቹ የተሻገሩ እና አዲስ ፈጠራ የታከለባቸው በመሆናቸው በሌሎች ጥናቶች ከተካተቱት የተለዩ ናቸው።

ነገር ግን ይህ የአዝማሪው ዋና ነገር የሆነው ቃላዊ ግጥም በሁለት መልኩ ካለው ስነ ውበታዊ ቀለም ሲቀንስ ተመልክቻለሁ።አንድም በቃል ግጥሞቹ ውስጥ የቋንቋ መዳቀል (ልሳነ ክልኤነት)እንመለከታለን።ይህ የቋንቋ ክልኤነት በተለያየ መንገድ ሊፈጠር ይችላል።አንደኛ ሁለት የተለያየ ቋንቋን የሚናገሩ ማህበረሰቦች አብረው በመኖራቸው የሚፈጠር ሲሆን ሌላው ደግሞ የራስን ቋንቋ አሳንሶ በመመልከት ምክንያት የሚፈጠር ነው። በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ ግን ይህ ሁኔታ የተፈጠረው ታዳሚን ለመያዝ ካለ ፍላጎት የመነጨ ነው።ማለትም ባህል ምሽት ቤት ውስጥ የተማሩ ታዳሚዎችም ስለሚመጡ የእንግሊዘኛ ቋንቋን በመቀላቀል ብጠቀም ታዳሚውን የበለጠ ለመሳብ እችላለሁ ከሚል ስሜት የመነጨ ይመስለኛል።በተጨማሪም ታዳሚውን ለማሳቅ ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች መካከል አንዱ ነዉ።የአዝማሪ ሙያ ደግሞ ባህላዊ እንደመሆኑ የራስን ባህል የበለጠ አጉልቶ የሚያሳይ እንጂ ታዳሚውን በመያዝ ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ ተገቢ አይደለም።የሌላውን ባህል ማንፀባረቂያ መሆን የለበትም።

የአዝማሪ ቃል ግጥም እምቅ የሆነ ሚስጥራዊ ገፅታን የተላበሰ ነው።እንዲሁም የአዝማሪ መለያ ከሚባሉት መካከል አንዱ ቃላትን መርጦ መጠቀም አንዱ መስፈርት ነው።ይህን ሁኔታ ግን በባህር ዳር ከተማ ታዋቂ አዝማሪዎች ዘንድ ከሰበሰብኳቸው አብዛኛዎቹ ቃል ግጥሞች ላይ አልመለከትኩም።ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የእውዱን ሁኔታ በመከተል የታዳሚን ፍላጎት ለማርካት በሚደረግ ጥረት ነው።እንዴት ቢባል ታዳሚው ከሌለ ባህሉን ማሳየት አይቻልም።እንዲሁም መተዳደሪያ የሚሆናቸውን የገቢ ምንጭ እናገኝም ከሚል ስሜት የመነጨ ይመስለኛል።

በተጨማሪም የሚመጣው ታዳሚ በአብዛኛው ወጣት በመሆኑ ቅኔ አይፈልግም ወይም አይገባውም በሚል እሳቤ ሊሆን ይችላል።በመሆኑም ይህን ታዳሚ ላለማጣት ሲባል በማሳቅና እና በማዝናናት ላይ በመመስረቱ ነው።ይህ ደግሞ የቃል ግጥሙን ስነ ውበት፣ዘይቤያዊነት፣እምቅነት እና የቅኔያዊነት ባህሪ እንዲያጣ አድርጎታል።ይህም ማህበሩ ከተመሰረተበት ባህልን የማስተዋወቅ ዋና አላማ ይልቅ ወደ ንግድ ያደላ አስመስሎታል።በመሆኑም ለቃል ግጥሞቹ ብዙ ትንታኔ ለመስጠት አስቸጋሪ እንዲሆን አድርጓል።

በተለይ አንዳንድ ግጥሞች ነጠላ ትርጉም ከመስጠት በስተቀር ሊተነተን የሚችል ምንም የተለየ ትእምርታዊ ቃል እንኳን አላገኘሁባቸውም።ቃል ግጥም ሲገጠም የሚኖረውን ባህሪ ያሟሉ አይደሉም።ይህም የቃል ግጥም ስነ ውበት እየወረደ መምጣቱን አመላካች ነው።

ሌላው ነገር ከዚህ የቃል ግጥም ክዋኔ ጋር እጅጉን ተያያዥነት ያለው እውድ በተመሳ ሳይ መልኩ ሲበረዝ ነው የተመለከትኩት።ማለትም አዝማሪው ለመከወን የግድ የሚከው ንበት እውድ ያስፈልገዋል።ይህ አውድ ደግሞ ታዳሚውን፣ቁሱን፣መቼቱን፣ጊዜውንና እያ ንዳንዱን ክዋኔ የያዘ ነው።ስለዚህ አዝማሪው ያለ አውድ ስለማይከውን ቁሱ እና ሙያው ሊነጣጠሉ የማይችሉ ነገሮች ናቸው።ነገር ግን የአዝማሪው መከወኛ በሆኑት የባህል ምሽት ቤቶች ውስጥ ለመጠጥነት ሲቀርቡ የተመለከትኳቸው የመጠጥ አይነቶች ባህላዊ ሳይሆኑ ዘመናዊ መጠጦች ናቸው።ማለትም ቢራ፣ውስኪ..ወዘተ ናቸው።በዚህ ቦታ ደግሞ ከሀገረኛው ታዳሚ በተጨማሪ የተለያዩ ቱሪስቶችም ይገኛሉ።ስለዚህ ባህልን ማሳየት እና ማስተዋወቅ የሚለውን አላማ የሚያደናቅፍ ይመስለኛል።ይህ ሁኔታ በዚህ ቀጥሎ የባህል ብርዘቱ ከተስፋፋ ባህላዊውን ነገር ናፍቆ የሚመጣውን ታዳሚ ጭምር ሊያሳጣ የሚችል ነው።

ከዚህ በተጨማሪም በገና አከባቢ በባህል ምሽት ቤት ውስጥ የምናገኘውም የገና ዛፍ ለባህሉ ብርዘት ሌላው ማሳያ ነገር ነው።ምክንያቱም ይህ ዛፍ ደግሞ የኛ ባህል መገለጫ አይደለም።ባህል ምሽት ቤቶቹ ባህላዊ እና የአዝማሪዎቹ መከወኛ እስከሆኑ ድረስ የሀገራ ችንን ባህል የሚያሳይ ነገር ብቻ በቤታቸው ቢያካትቱ ተገቢ ይመስለኛል።

በመጨረሻ የማነሳው ጉዳይ ከአዝማሪያኑ ጋር ቃለ መጠይቅ በማደርግበት ጊዜ እንደነገሩኝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመንግስታት ወደ በሀር ዳር ሲመጡ እንግዶች አበሻ ልብስ ለብሰውና ባህላዊ ጫማ ተጫምተው ያቀባበል ስነ ስርአት ያደርጋሉ።በክዋኔው ወቅት በአንድ መስመር ተሰልፈው ወንዶቹ በማሲንቆ እየተጫወቱ ሴቶቹ ደግሞ በማጨብጨብ እና እልል እያሉ እንደሚቀበሉ ነግረውኛል።ይህን ክዋኔ በቅርብ እንደመጀመሩ እና ሁልጊዜ የሚካሄድ ባለመ ሆኑ ሲከውኑ እድሉ አጋጥሞኝ ለመመልከትና ለመቅረፅ አልቻልኩም።በመሆኑም ከሌሎቹ አውዶች በተለየ መልኩ በክወና ብቻ የሚያከናውኑት ስለሆነ በቃል ግጥም ትንታኔ ውስጥ ላከትተው አልቻልኩም።

## ምእራፍ አራት

### ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በባህር ዳር ከተማ በሚገኙ ታዋቂ አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥ ሞች ላይ ያተኮረ ነዉ።ጥናቱ በአራት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን በእነዚህ ምእራፎች ውስጥ የባህር ዳር ከተማ አዝማሪዎች ባህላዊ ሙዚቃ ክዋኔ ምን እንደሚመስል ለዚህ ጥናት በተመረጡ ሶስት አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ፣በቃል ግጥሞቹ አውዳዊ ክዋኔ፣በዳ ራው.... ወዘተ ተረካ አማካኝነት ለማሳየት ተሞክሯል።

እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ ባህላዊ ዘፋኝ የሆነው አዝማሪ በሚከውንበት ወቅት በአ ውዱ ውስጥ ባህላዊ ቁሱን፣ባህላዊ ሙዚቃውን፣ታዳሚውን...ወዘተ አቅፎ ስለያዘ እንዲ ሁም በባህል ምሽት ቤት፣በሰርግ፣በሀይማኖት ክብረ በአላት እና በመንግስታት አቀባበል ስነ ስርአት አውዶች ላይ በመከወኑ በሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት የፎክሎር ዘውግ ውስጥ እንዲመደብ አድርጎታል።እነዚህ አውዳዊ ክዋኔዎች በጥናቱ ትረካ ውስጥ የሚታዩ ናቸው። ስለዚህ በጥናቱ ውስጥ የተነሱትን ጥያቄዎችን ይህ ጥናት ለመመለስ ሞክሯል።

በመሆኑም ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ባላቸው የፅሁፍ ሰነዶች፣በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ መረጃው ተሰብስቧል፡፡መረጃው በጽሁፍ ማስታወሻ በቪዲዮ ካሜራ፣በፎቶ ግራፍ፣በቴፕ እና በመቅረፀ ድምፅ አማካኝነት ተቀርጿል።የተሰበ ሰቡት መረጃዎችም የተለያዩ ማጣቀሻ መፅሀፎችን መሰረት በማድረግ ትንተና ተሰጥቶባቸ ዋል፡፡

ይህም የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያመላክተው በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት ሶስት ታዋቂ አዝ ማሪያን ቃል ግጥም የሚገጥሙት አንዳንድ ጊዜ ከሌላ ሰው በመስማት፣በመሸምደድ እና ለቦ ታው እና ለአውዱ ተገቢ እና ተስማሚ ሆኖ ሲያገኙት አስታውሰው በመድገም ነው፡፡በሌላ በኩል ደግሞ ያንን ቃል ግጥም አሻሽለው፣ቀንሰው ወይም ጨምረው ሊገጥሙ ይችላሉ።ከዚ ህም በተጨማሪም የአውዱን ሁኔታ በማየት የራሳቸውን ሌላ አዲስ ቃል ግጥም ይፈጥራሉ በዚህ መሰረት ይህን ማህበረሰብ መገለጫ የሆነውን ቃል ግጥም ከተውልድ ወደ ትውልድ በቃል እየከወኑ ያስተላልፋሉ፡፡

ይህ ጥናት በባህር ዳር ከተማ የሚገኙ አዝማሪዎች በማህበረሰቡም ዘንድ ሆነ በሌሎች ተቋ ማት ዘንድ እየታወቁ እና ተቀባይነታቸው እያደር እየጨመረ መምጣቱን ያሳየናል።አዝማሪ

ዎቹ ቀደም ሲል ሳይጋበዙ በየመጠጥ ቤቱ እና በየሰርጉ እየተዘዋወሩ ይከውኑ ነበር። አሁን ግን ዝፈንልኝ ተብለው እና በርከት ያለ ክፍያ ተከፍሎአቸው እንደሚከውኑ ተመ ልክቷቸዋል።(ምሽት ቤት እስከ 800 ብር ሲከፈላቸው በሰርግ ላይ ደግሞ እስከ 3 000 ብር ድረስ ይከፈላቸዋል)።ሌላው አዝማሪዎቹ በህብረተሰቡ ዘንድ እንዳላቸው የተቀቂነት ደረጃ በተለያየ ቦታ እንደሚከውኑ ያሳያል።ማለትም ጀማሪዎቹ በጠጅ ቤት ውስጥ ሲከ ውኑ የታወቁት ደግሞ በባህል ምሽት ቤት ውስጥ ተቀጥረው ይከውናሉ።

ሌላው ደግሞ እነዚህ አዝማሪዎች ያለምንም ክፍያ በራሳቸው ፈቃድ ለነፍሳቸው ብለው በጥምቀት፣በሰባሩ ጥምቀት(ሰባሩ ጊዮርጊስ) እና በአመታዊ የሀይማኖት ክበራዎች ላይ ታቦትን በማጀብ ይከውናሉ።ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመንግስታት እንግዶችን በመቀበል ስነ ስርአት ላይ በመገኘት መከወን ጀምረዋል።ነገር ግን በአዝማሪዎች የሚሰሩ ቃል ግጥሞች የታዳሚውን ፍላጎት ለማርካት፣ለማዝናናት በሚል እና በቋንቋ መረጣቸው አናሳነት የተነሳ የቃል ግጥሞቹ የእምቅነት ደረጃ፣ዘይቤያዊነት እና ቅኔያዊነት እየቀነሰ መምጣቱን እንመለከ ታለን።እንዲሁም ታዳሚውን ለማዝናናት እና ለማሳቅ በሚል ሰበብ በቃል ግጥሞቹ ውስጥ ባእድ ቃላትን በመጨመር ቃል ግጥሞቹን ጉራማይሌ የማድረግ ሁኔታ ይታ ያል።ይህም ሙያው ከንግድ ጋር መያያዙን ያመለክታል።

ምክንያቱም ቅድሚያ የሰጡት ለሙያው ሳይሆን በሙያው ለሚጠቀመው ነገር ነው።ከዚ ህም ጋር በተያያዘ ከአዝማሪው ክወና ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው የባህል ምሽት ቤቶች የባህል መገለጫ እንደመሆናቸው ባህላዊ ነገርን ብቻ ማሳየት ቢችሉ የሚል እመለካከት አለኝ።ምክንያቱም አዝማሪው እና እነዚህ ቤቶች ሊለያዩ የሚችሉ ነገሮች ባለመሆናቸው ባህላዊነታቸው እስካልተጠበቀ ባህላዊውን ነገር ናፍቆ የሚመጡትን ቱሪስቶችም ሆነ የታ ዳሚውን እግር የሚያሳጥር ነገር ነው።ይህ ደግሞ በአዝማሪዎቹም ሆነ በሀገራዊ ኢኮ ኖሚ ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ ቀላል የሚባል አይደለም።

የእነዚህ አዝማሪዎች ቃል ግጥሞች በፍቅር፣በፉከራ፣በምክር፣በሙገሳ፣በእንጉርጉሮ፣አገራዊ እና ሀይማኖታዊ በሆኑ መልእክቶች ...ወዘተ ላይ ያተኮሩ ናቸው።በአጠቃላይ በጥናቱ ውስጥ እንደምንመለከተው በባህር ዳር ከተማ የሚገኘው የአዝማሪው ባህላዊ ሙዚቃ በክወና ስራቸው ከእለት እለት ከፍ ያለ ደረጃን እያገኘ የሄደ ሲሆን በሌላ ጎኑ ደግሞ በቃል ግጥሙ እና በቁስ አካሉ ላይ የታዳሚን ፍላጎት ለማሟላት፣ለማሳቅ እና ታዳሚን ላለማጣት እየተባለ ጉራማይሌ ማደረግ፣ቃል ግጥሙን ስነ ውበት ደረጃ ከነበረበት መቀነስ እና ባህሉን መበረዝ

ይታያል።ስለዚህ ይህ ጉዳይ ሊሻሻል ይገባል ባይ ነኝ።እንዲሁም በባህል ምኽት ቤቶች ላይ የተጠና ጥናት ስለሌለ ይህ ጉዳይ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊጠና ይችላል።

## ግኝት እና ይሁንታ

### ግኝት

ከምእራፍ አንድ እስከ አመስት ድረስ በተደረገው ጥናታዊ ሂደት አማካኝነት የተገኘው ውጤት ሁለት ገፅታን የያዘ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።እሱም በአንድ በኩል ጥሩ ጎን ሲኖረው በሌላ በኩል ደግሞ ጥሩ እና ጠንካራ ያልሆነ እና ሊቀረፍ የሚገባ ገፅታን የያዘ ነው። ይህንንም ግኝት ከዚህ በታች በመተንተን ለማሳየት እሞክራለሁ።

- በባህር ዳር ከተማ የሚገኙ አዝማሪዎች በህበረሰቡም ሆነ በሌሎች ተቋማት ዘንድ ከቀን ወደ ቀን እየታወቁ እና ተቀባይነታቸው እየጨመረ መምጣት።ይህም ማህበረ ሰቡ ለአዝማሪነት ሙያ ያለው አመለካከት በተወሰነ መልኩ እየተቀየረ መምጣ ቱን ይጠቁማል።
- አዝማሪዎቹ በፊት ሳይጋበዙ ይሰሩ ነበር።አሁን ግን ዝፈንልኝ ተብለው እና በርከት ያለ ክፍያ ተከፍሎአቸው መከወናቸው።(ምሽት ቤት እስከ 800 ብር ሲከ ፈላቸው በሰርግ ላይ ደግሞ እስከ 3000 ብር ድረስ ይከፈላቸዋል)
- አዝማሪዎቹ ታዋቂ ሲሆኑ እና ሳይታወቁ(ጀማሪ ወይም ተለማማጅ) ሲሆኑ በተለ ያየ ቦታ መከወናቸው።ማለትም ተለማማጆቹ በጠጅ ቤት ውስጥ ሲከውኑ የታወ ቁት ደግሞ በባህል ምሽት ቤት ውስጥ ተቀጥረው ይከውናሉ።
- እነዚህ አዝማሪዎች ያለምንም ክፍያ በራስፈቃድ ለነፍሳቸው ብለው በጥምቀት፣ በሰባሩ ጥምቀት(ሰባሩ ጊዮርጊስ) እና በአመታዊ የህይማኖት ክበራዎች ላይ ታቦ ትን በማጀብ መከወናቸው።
- በአሁን ሰአት ደግሞ የመንግስት እንግዳዎች የአቀባበል ስነስርአት ላይ እንዲከ ውኑ መጋበዛቸው።
- ለዚህ ጥናት ግብአትነት የተሰበሰቡ አብዛኛዎቹ ቃል ግጥሞች በሌሎች ጥናቶች ላይ ካየኋቸው ቃል ግጥሞች አዲስ ፈጠራ የታከለባቸው መሆናቸው።
- ለዚህ ጥናት ግብአትነት ከተለያየ አውድ የተሰበሰቡ አብዛኛዎቹ ቃል ግጥሞች በቋንቋ መረጣ ዝቅተኛ መሆኑ የተነሳ የቃል ግጥሙ እምቅነት፣ዘይቤያዊነት፣ስነ ውበት እና ቅኔያዊነታቸው እየጠፋ መምጣቱ።

➢ የአዝማሪ ሙያ ባህላዊ እስከሆነ ድረስ የሚያሳየው ነገር በሙሉ ባህላዊ መሆን አለበት።ስለዚህ በቃል ግጥም ውስጥ የሚቀላቅሏቸው አንዳንድ የባእድ ቃላት ቃል ግጥሙ ጉራማይሌ እንዲሆን አድርገውታል።ስለዚህ በራሳቸው ቋንቋ ብቻ በመጠቀም ባህላቸውን እና ቋንቋቸውን ለቱሪስቶችም ሆነ ለታዳሚው አለማሳየታቸው።

➢ ከአዝማሪነት ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው የባህል ምሽት ቤት አላማው ባህልን ማስተዋወቅ እስከሆነ ድረስ ባህላዊ ያልሆኑ መጠጦች እና ቁስ በውስጡ ማካተቱ።

ይሁንታ

➢ በባህር ዳር ከተማ የሚገኙ አዝማሪያን ለታዳሚ፣ለንግድ…ወዘተ የሚለውን ምክን ያትን ትተው ቅድሚያ ለቃል ግጥሙ ስነ ውበት ቢሰጡ።ምክንያቱም በዚህ አያ ያዝ ቃል ግጥሙ ለዛው ከጠፋ ታዳሚውንም ለማግኘት ያስቸግራል።

➢ የባህል ምሽት ቤቶች የባህል መገለጫ እንደመሆናቸው ባህላዊ ነገርን ብቻ ማሳየት ቢችሉ።ምክንያቱም በዚህ ቦታ ባህላዊውን የሙዚቃ ክዋኔ እና አጠቃላይ አውዱን ለማየት የሚመጣው ታዳሚ እና ቱሪስት የሀገራችንን ባህል ብቻ መመልከት ያለበት መስለኛል።

ዋቢ መፅሀፍት

መንገሻ አማረ።"የወገል ጤና አዝማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ቃላዊ ግጥሞች"።ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ(ዲማፅ)፣1992።

ብርሀኑ ገበየሁ።የአማረኛ ሥነ ግጥም።አዲስ አበባ፣አልፋ አሳታሚዎች፣1999።

ኑር ሁሴን መሀመድ- "በፎገራ አከባቢ የሚሰሙ የአዝማሪ ግጥሞች ይዘታዊ ትንተና"።ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ(ዲማፅ)፣1986።

አልማዝ አበበ- "አዝማሪ እና ግጥሞቹ በየጁ አውራጃ"።ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ(ዲማፅ)፣1974።

አበበ ማለደ።"በጎንደር ዙሪያ ወረዳ በቡርባክስ ቀበሌ የአዝማሪነት ሙያና የዘፈን ግጥሞች"።

ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ(ዲማፅ)፣2002።

አንለይ ሙሉ -"የአዝማሪ ታደለ የህይወት ታሪክና ቃላዊ ግጥሞች"።ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ(ዲማፅ)፣1995።

ዳዊት ጌታቸው -"አዝማሪዎች"።ለዲፕሎማ ሳናት ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ(ዲማፅ) 1993።

ፈቃደ አዘዘ።የስነቃል መምሪያ።አዲስ አበባ፤ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች፣1991።

..................ሰሚ ያጡ ድምጾች።አዲስ አበባ፣ብራና ማተሚያ ቤት፣1996።

Abraham,Alemu,."Jimma Oromo Oral Prose Narratives:A Preliminary Descriptive Analysis." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 2000.

Ashenafi,Kbede."The Music Of Ethiopia.Its Development And Cultural Setting". Phd Disseration,Wesleyan University,1971.

........................Zemenawi Musika Modern Trends In Traditional Secular Music Of EthiOpia,Vo.4,No.3,1970.

Bascom,R.William."Four Functions of Folklore".The Journal of American foklore V. 67, No.226,1954.

Bauman,Richard.Foklore,Cultural Performance,and Popular Entertainments. New YOrk oxford university press,1992.

..............................."Genre,Intertextuality and Social Power".Journal of Linguistic Antropology,American Anthropology Association,1992.

Bolay,Anne."The Azmari,Voices of Ethiopia Memory".Proceedings Of The xlv Intrernational Conference Of Ethiopian Studies,vo.1,2000.

Braid,Donald.*Personal Narrtive and Exprincial Meaning.The Journal of Amerian Folklore,Vol.109,No.431,1996.*

Catherine Kohler Riessman.*ANALYSIS OF PERSONAL NARRATIVES.* Boston University, Riessman@bu.edu, 2000.

Dan be,Amose,contxt in context, *Western Folklore*, Vol. 52, No. 2/4, 1993.

Duisit,Lionel and Roland.An.Introduction to the Structural Analysis of Narrative. the jons Hopkins University Press,v.6,no.2,1975.

E.Polk,Donald.Validity Issues in Narrative Research.Universty of South Californ ia,losanjalse,2007.

Finnegan, Ruth. *Oral Literature in Africa.* Nairobi: Oxford University Press1970

...............................*Oral Poetry its Nature,Siginificance and Social Context.Cont ext.Cambridge,*University Press,1977.

................................."Oral Traditions and the Verbal Arts".*Routledge Is An Internatio nal Thoms On Publishing Company,1992.*

Getie,Gelaye.Pesants And The Ethiopian Agricultural Producers,Cooperative And Their Reflections In Amharic Oral Poetry-A Case Study In yetnona, East Gojam.1975-1991 v.7,Humburg Litverlag Munster 2000.

Goldstein, Kenneth S. A Guide For Field Workers In Folklore. Detroite: Gale Research Company, 1974.

Helina,Fekadu- "Survey Of Ethiopian Female Azimaris In Addis Ababa"Frist Degree Studies,1998(2006).

Jikes,Pat and Gale,Ken.Narratve Approaches To Resarech.Universty Of Ply Mouth,2006.

Hufford, Mary.*The Journal of American Folklore*, Vol. 108, No. 430,1995.

Kfeyalew,Azeze.- "Minstrels in Addis Ababa in the Social Life of Gonderian Inzata".masters thesis,Adis Ababa Universty school of graduate studies,1998.

Moen,Torill,Reflection On the Narrative Resarech Approach.Intrenational Journ al of Qualitative Metedology,2006.

Oring, Elliot.*Folk Groups And Folklore Genres: An Introduction*. Logan, Utah: Utah University Press,1986.

......................"Three Functions Of Folklore: Traditional Functionalism As Expla nation In Folkloristics",The Journal Of American Folklore,Universtiy Of Illinois Press On Behalf Of American Folklore Society,Vol. 89, No. 351, 1976.

.................... Traditional Functionalism: Once More with Feeling Author(s): Source: The jou rnal Of American Folklore, Vol. 90, No. 355, 1977,

Solmon,Mulegeta,- "The Azmaries".Deploma Studies,1985(1993)

Sims.C.Martha,*Living folklore*.Utah State University Press / Logan, Utah,2005.

The Concise Oxford Dictionary Literary Of Terms, Oxford University Press,200 1.

To appear in special issue of *The Journal of Narrative and Life History*,1997.

Victor,Jupp.The Sage Dictionary Of Social Research Method. Great Britain By Athenaeum Press,2006.

W.Mariyame,konejete-"Major Themes In The Play Azmari"Frist Degree Studie s,1990(1998).

Zebebe,Bekele.-music in the horn.A preliminary analytical approach to the study of Ethiopia music,stockndm Sweden published,1987.

# አባሪ አንድ

## በአዝማሪ ወርቁ የተከወኑ ቃል ግጥሞች

### ስለ አባይ ግድብ የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. የውጩ ናንጋኒ እንግዲህ ለምናችን
   አባይ ተገድቧል የጀርባ አጥንታችን

2. ኸረ አባይ ወርቁ ኸረ አባይ ወርቁ አለም ዞሮ እንደገና
   አባይ ወንዛችን የኛማ የኢትዮጵያ ቀለበት ነውና።

3. ኸረ እንደምን አለህ ከማገኘው ገንዘብ አምስት አስር ብዬ
   ቦንዱን እገዛለሁ ለግድቡ ብዬ።

### የሙገሳ ቃል ግጥሞች

1. አይኗ ጉልላት ጥርሷ የመሰለ ወተት
   ጣቷ የመሰለ የሞርተር ጥይት
   ምነ ለእህታችን ባልተሰራ ሞት።

2. እዩአት አንገቷን ስራስር
   የበላይ ዘለቀ ልጅ የምትመስል።

3. አዩኗን እዩብኝ አፍንጫዋን እዩብኝ
   ጥርሷን እዩብኝ ከንፈሯን እዩብኝ
   ሽንጧንም እዩብኝ ዳሌዋን እዩብኝ
   ባቷ እዩብኝ ሁሉንም እዩብኝ
   ወይም ፍረዱባት ወይም ፍረዱብኝ።

4. ከፈረንሳይ ሽቶ ከእንግሊዝ ወተት
   በቃ ተከተተ ካንቺ ወዲያ ሴት።

5. እኔ ምን ቸገረኝ አዝማሪ ቢሉኝ
   የሰው ልጅነቴን ከአገር ሊገኝ

### የፍቅር ቃል ግጥሞች

1. ምነው ባደረገኝ የደጇን ገለባ
   ምነው ባደረገኝ የደጇን ገለባ

ወደ ቤት ስትገባ ይዛኝ እንድትገባ

2. ከዚህ ተቀምጬ እስላም አንገቴን
   ማተቤን ሸዋ ላይ ማን አስሮት ይሆን።

3. ሽሙንሙን ሽሙንሙን በይልኝ
   የያዘኝ አባዜ ገለል እንዲልልኝ

4. እሳቱ እየጠፋ ባነደው ከሰለ
   አሁን የት ይገኛል እሷን የመሰለ

5. ሆድዬ ኮተት በይ በጓሮ
   እንደ ኪዳው ዶሮ

የምክር ቃል ግጥሞች

1. ምን ያረግልሀል ሱፍ ለባሽ ቢበዛ
   እንደምንም ብለህ ወታደርህን አብዛ።

ስለ ሀገር የተገጠመ ቃል ግጥም

1. ድስቅ ድስቅ አድርገሽ ምችው ባንገትሽ
   ድስቅ ድስቅ አድርገሽ ምችው ባንገትሽ
   ጎንደሬ ነሽ እና መቼም አይጠፋሽ

የፉከራ ቃል ግጥሞች

1. ዘራፍ አካኪ ዘራፍ
   ዘራፍ አካኪ ዘራፍ
   እሯ በል አንተ

2. ዘራፍ በል እንጂ
   የመጣህበትን አገሩን እንጃ
   ወንዝ አሻጋሪ በሰው ጠበንጃ

3. በሰው ብረት ኸረ እንዴት አድርጎ
   አወቀበት አተኳኮሱን አገዳደሉን
   ከአፋፍ ላይ ሆኖ ነፈስ ይዞ መግደል

4. አባቱ ነበር የጎበዝ አድላ
   ልጅዬው ደርሷል አቤት ከለላ

ከቀረው ሜዳ አጭዶ ከለላ

5. ኸረ አብዬ ኸረ አብዬ

አትበለኝ ችላ ያንተ ደም መላሽ እኔ ነኝና

6. የታዴ ወንድም የሀይልዬ ወንድም

ያውም ከነሱ በቆላ ሽመል

አንገት ጠባሹ እንበለው እና

የመጣው ይምጣ አርሶ ጀግና ነው ሽምቶም ጀግና

7. ኸረ ዳኘዬ የሰደድ እንጨት

እባብ ልብ እንጂ የለውም አንጀት

8. በዚያ ቁልቁለት በዚያ ማታ

አሮጌ ብረት እያንገላታ

እያራወጠ ያስፈጅ ጫጫታ

9. የእናተ ወንድም የእናንተ ውላ

እበ ጎራዴ መቃብር ብላ

10.የግሽ አባይ ልጅ የእረኛው ምሳ

ያርበደብዳል ገና ሲነሳ

11.ኸረ አይንዬ የሰደድ እንጨት

እባብ ልብ እንጂ የለውም አንጀት

ኸረ ተው በለው ኸረ ተው በለው

እንቢ ካለማ ነፍጠኛ ጎጂ

በቴስታ በለው

12.አንዱን ከወዲያ አንዱን ከወዲህ

አንዱን በጥይት አንዱን በጥፊ

ነፍጠኛው ጎጂ ኸረ እንደው ጎጂ

13.አካልበውና ኸረ ተው በለው ኸረ ተው በለው

እንቢ ካለማ ያገሬ ጀግና አናቱን በለው፡፡

14.ኸረ አጅሬ ኸረ አጅሬ እንኮኮ ብዬ

እንደ ዝንጀሮ በልጅነቱ በረሀ ለምዶ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አሳዶ በል

15.እንበለውና የመጣው ይምጣ

አርሶ እንቢ ካለ ሸምቶም ይብላ

እንበለውና ጉልበት ጉልበቱን

እያንኳተተ ይውጣው ዳገቱን

16.የስሌ ወንድም እንቆቆ ፍሬ

ልቡ ድፍን ነው እንደ ጥጥ ፈሬ

17.ኸረ እናንተዬ እንደው ምን ይሻል

ሳይገሉ ገዳይ ስም ያበላሻል

18.ተልባ ሲቆላ ይላል ጢ ጢ

የዳኜ ወንድም የኔ ወንድም

አመለ ክፉ ቂጥ ቂጡን

19.የወና ፍሬ እንደ በረዶ በረሀ ለምዶ

አሳዶ በለው ከወዲያ ማዶ

ስለ ባህል የተገጠመ ቃል ግጥም

1. አለው አለውና አለው አለውና

በማሲንቆ ፀና

ስለ ፖለቲካ የተገጠመ ቃል ግጥም

1. ያልተገራ ፈረስ ጠቅል እያላችሁ

ከትግሬ እየሮጠ ለንደን ገባላችሁ

ስለ ምስጋና የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. እህህ እእህ እህህ

ክበር ተመስጌን ጌታችን

በዋጋ ገዛኸን

2. ውለታው ብዙ የእግዚአብሄር

አመስጋኝ ሰው ቢኖር

3. ክበር ተመስገን ጌታችን

ለዚች ሰአት ያደረስከን

4. ክበር ተመስገን ያንተ ዋጋ
   የጨለመውን ስታነጋ

5. እግዚአብሄር ይመስገን አንቺን የሰጠን
   ሳንጠራሽ አንውልም
   የልባችን ነሽና ድንግል

6. ክበር ተመስገን ተመስገን
   የኀበጡ እና የታወሩ
   ከደዌ ብዛት ታሰሩ
   በእምነት ቀርበው ቢለምኑ
   ሲዳስሳቸው ደህና ሆኑ

7. ኸኸ ኸሀ ኸሀሀ
   ክበር ተመስገን ጌታችን
   መልአከ ሚካኤል
   ሰውነቱ የነፃ ከበደል

8. ተመስጌን ሰላምን ላከረምኝ
   ለወር ማብቂያው ላደረስከኝ

9. ቅዱስ ሚካኤል መእላክቱን
   አንግሼ መጣሁ ታቦቱን
   ለሰራው ገድል ተአምር
   እኔም ቆምኩለት ዝክር

10. አቤት ፈጣሪ ቸርነትህ
   ተነግሮ አያልቅም ውለታህ
   እንዲያው ተመስገን ልበልህ

ስለ ውልደቱ የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. ከሰማይ ሰማት ወርደህ
   ከድንግል ማሪያም ተወልደህ
   አንተንም አሙህ እንደ ሰው
   ምናምን ነው

2. እመቤቴ ወልዳ ተወልዶ ጌታዬ
ምን ይገፔ አየዋለሁ አቤት መከራዬ

3. አምላክ ወርዶ ከምድር
አዳምን ዋና ሊያስተምር
አክ እንትፍ ቢያሳያቸው
ምራቁ አሳዘናቸው

4. አየነው እግዚያበሄር በግርግም ተወልዶ
ለኛ ሀጢያት ሲል ክብሩን ጥሎ መጥቶ

5. በንስሀ በንስሀ ወ በሰላም
በንስሀ በንስሀ ወ በሰላም
ወረደ ወለድ ወረደ ወለድ
ወረደ ወለድ ወረደ ወልድ

ስለ ማዳኑ የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. የየሩሳሌም ነጋዴ
አለም ያወቀው ወንበዴ
ለገንዘቡማ አላዘነም
ወዮ ያዳነን

2. በእርሱ ቁስል እንዲድኑ
እርሱ ሰጣቸው በስልጣኑ

3. ኸሀ ደስ ይበለን ደስ ይበለን
እልል በሉ እልል በሉ
አዳነን ከሀጢያታችን

4. እሀሀ ኸሀ ኸሀሀ
ከቤቴልሄም ጎልጎታ
እስከ ቀራኒዮ ከፍታ
እየተከተልክ ፈለግኸኝ
ከሀጢያት ቁስሌ ፈወሰወከኝ

5. እህህ ኸሀ ኸሀሀ

   አሁን የለብኝ ወቀሳ

   ከፍለህልኛል ለኔ ካሳ

   መልሰኸኛል ወደ ቤቴ

   አክብረኸኛል ደግ ቤቴ

6. ኸሀሀ ኸሀሀ እሀሀ

   እንዳምላክነቱ መክብር ሳያንሰው

   ሊያገለግል መጣ የጌታ ልጅ ለሰው

7. ትልቅ ነጭ በግ አርደን

   ሁሉ ዳነ አሉ የታመሙ

   በስጋው እና በደሙ

ስለ ምህረት የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. እግዚአብሄር ጠጅ አይጠጣም ለጌትነቱ

   ማር ብሎ አይልክም ወይ በገዛ ፍጥረቱ

2. ሁሉንም ተው ስለጌታ

   አንድ እንኳን ሳይቀር

   ኸሀሀ ሀሀ ኸሀሀሀ

   ክበር ተመስገን ጌታችን

3. ሀጥኡ ተምሯል ብዙ ነፍስ አጥፍቶ

   በድንግል ማሪያም ስም ጥርኝ ውሀ ሰጥቶ

ስለ ክብር የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. አንቱ የምለውን ሰውዬ አንተ አልለው

   አባይም ይጎላል እንኳን ሰው ጊዜ ሲያዋርደው

2. እውነትን ይመስክር የክብርሽን ዝና

   ቅዱስ ገብርኤል

   እግዛቢሄር ነውና ከአንቺ ጋር

3. የክብር ሚስጥሩ በቃሉ ሲፈታ

   ቁሳር ለቁሳር የጌታም ለጌታ

4. መልካም አገር ነው አብይ ጎንደር
   ቤተስኪያን ስሞ ለመኖር
   አይቀርም እና መዳኘት
   ሰው ከተማስ መግባት

5. በመቤትነቷ አላት ልዩ ክብር
   አንድ እሷ ናትና የየሱስ መንበር

ስለ ክርስቶስ ንፅህና የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. እህህ እ እህ እህህ
   እውነት ሲከሰስ በሀሰት
   እውነት ሲከሰስ በሀሰት

2. አቤት ትግስት ቸርነት
   በስራው ሳይኖረው ስህተት

3. ነፅቶ ሳለ ከበረዶ
   ምን አለ ጌታ ሲከሰስ
   ንፅሁ ጌታ ለሞት በቃ
   ዳግመኛ ይመጣል
   የወጉት ሁሉ ያዩታል

4. እህህ ኸህ ኸህህ
   ተብለህልኝ ወንጀለኛ
   ቆመህልኛል ከሀሰት ዳኛ
   እስከ ሞት ተሰቅለህ
   ክብርን ጠገብኩኝ ከእጅህ

ስለ ክርስቶስ ጥምቀት የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. በወንጌሉ ያመናችሁ በወንጌሉ ያመናችሁ
   እንኳን ለብርሀነ ጥምቀቱ አደረሳችሁ
   እንኳን ለብርሀነ ጥምቀቱ አደረሳችሁ

2. ተጠመቀ ተጠመቀ ተጠመቀ
   ተጠመቀ በዩሀንስ እጅ
   ተጠመቀ በዩሀንስ

3. እንደምናነበው በወንጌል ተፅፎ
መንፈስ ቅዱስ ታዬ በራሱ ላይ አርፎ
በእርግብ ምሳሌ ክንፉን አሰይፎ

4. የአለምን በደል
የሰውን ግፍ አይቶ
ዘጠና ዘጠኙን መንጋውን ትቶ
ፍርድን ለመፈፀም በደልን አንፅቶ
የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለኛ

5. አሆሆ እውነት በእውነት እውነት በእውነት
እንዲህ ነው የጌታ ጥምቀት
እንዲህ ነው የጌታ ጥምቀት
ኸሀ እንዲህ ነው የጌታ ጥምቀት

6. ሀሌ ሀሌሉያ ሀሌ ሀሌሉያ ሀሌ ሀሌሉያ
አለም በሰማያዊት በደም በቤዛዊት
አለም በሰማዊት በደም በቤዛዊት

7. ሀሌ ሀሌሉያ ሀሌ ሀሌሉያ ሀሌ ሀሌሉያ
አምላክ ወገኖችህ ዳኑ በጥምቀትህ
አምላክ ወገኖችህ ዳኑ በጥምቀትህ

8. አማን በአማን አማን በአማን
እንዲህ ነው ብርሀነ ጥምቀቱ
እንዲህ ነው ብርሀነ ጥምቀቱ
ኸሀ እንዲህ ነው ብርሀነ ጥምቀቱ

9. አማን በአማን አማን በአማን
እንዲህ ነው ስርአተ ጥምቀቱ
እንዲህ ነው ስርአተ ጥምቀቱ
ኸሀ እንዲህ ነው ስርአተ ጥምቀቱ

10. ወ ለአምን በአብ ወ ለአምን በወልድ በወለድ
ወ ለአምን በአብ ወ ለአምን በወልድ በወልድ

ወ ለአምን ወ ለአምን ወ ለአምን ወ ለአምን
ወ ለአምን በመንፈስ ቅዱስ

11.አሆሆ ዩሀንስን ሀሎ ያጠመቀ ሀሎ ዩሀንስ ያጠመቀ
በሄሆል በእየሩሳሌም በሄሎን በእየሩሳሌም
በሄሎል በእየሩሳሌም በሄሎን በእየሩሳሌም

12.እኛን ከነሀጢያታችን ወደን
የአለም መድሀኒት ተጠመቀልን

13.ኦሆሆ በቃና በገሊላ በቃና ዘገሊላ
በገሊላ በገሊላ ድንቅ አረጉልን
በገሊላ ድንቅ አደረጉልን

ስለ ማሪያም አዳኝነት የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. የተዋህዶ ሚስጥር ወልደሽው ነው ጌታን
የአለም መድሀኒት እናት ሆነሽናል

2. ኸሀሀ ኸሀ ኸሀ ሀሀሀ
ገና ጥንስስ ሳለች ተሸክማት ሀና
ድውይ ፈውሳለች በማህፀን ሆና

3. ኸሀሀ ኸሀ ኸ ሀሀ
ሁሉን በቃልህ ማድረግህ
ሳይፈሩ ጌትነትህ
እንዴት አየኸው አማኝህን
አላውቃትም ሲል እናትህን

4. ተዋህዶ ሀይማኖት እመቤቱ ናት
ተዋህዶ ሀይማኖት እመቤቱ ናት
እንከተላት እንከተላት የአምላክ እናት

5. ተዋህዶ ሀይማኖት እመቤቱ ናት
እንከተላት እንከተላት እስከሞት እስከሞት
በእውነት የአለም ብርሀን

6. ነይ ነይ እምዬ ማሪያም
ነይ ነይ እናቴ ማሪያም

7. የት አገኘሁ ብዬ ግንብም አልገነባ
ከድንግል አርፈለሁ ከፀናቸው አንባ

8. እመብርሀን ቅድስት
የፈጣሪያችን እናት
. ከሴቶች ሁሉ ንፅእት
ጭንቅ አማላጅ ናት በእውነት

9. ኸኸኸ ኸሀ ኸሀሀ
ሆኖ የማያውቅ ታየ ገድል
ጌታ ተገኘ ከድንግል

10. ጥፋት በደሌ በዝቶብኝ
ሳልሰማህ ጠይቄህ
ተሟልቶልኛል ስጦታህ
ከእናትህ

ስለ ምክክር የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. እሀሀ እሀእሀሀ ሀሀ
እርስበርሳችን እንማከር
እርስበርሳችን እንማከር አሀ
ልጆች ነንና ለእግዚአብሄር

2. እሀሀ እሀሀ ኸሀሀ
እርስበራሳችን እንማከር
ከአንድ መንፈስ ተወልደን
ከአንዱ አብራክ ተፈጥረን
ከወጼት መጣ መለያየት
ተፈጥረን ሳለ ከአንድ አባት

ስለ ፍቅር የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. ከሁሉም በላይ ፍቅር ይፀናል
ጌታችን በቃሉ ይህን ብሏል

2. የሚያየው እንደ ጠላት ወንድሙን

እርሱ አያውቀውም አምላኩን

3. ፍቅር ነውና ህግ መጨረሻ

መንግስተ ሰማያትን መውረሻ

4. ያቆብ ከኤሳው የታገለ

የርብቃን ማህፀን ልብ ወሰደ

የጥላቻን ግንብ ስንገነባ

መናወጥ መጣ በመርከቡ

5. በየቀኑ ጥፋታችን

ሳያርግ ቀረ ፀሎታችን

ከኛ ዘንድ ፍቅር ስላነሰ

ቀራጩ ፀድቆ ተመለሰ

6. መንጋውን ተኩላ ሳይገባበት

ከሳሽ ጠላትን ጥሎልን

እግዚያብሄር ፍቅርን ያልብሰን

ኸሀሀ ኸሀ ሀሀሀ

7. ኸሀሀ ኸሀሀ ሀሀሀ

የወደዳቸው ናቸው

የጠራቸው መረጣቸው

የመረጣቸውን አፀናቸው

8. እሀሀ ኸሀ ኸሀሀ

እንደምትወደኝ አውቃለሁ

ሁሌ ስጠራህ አውቃለሁ

የቅጠል ልብስ ብለብስም

ሞቴን አትፈልግም

ስለ ፅናት የተገጠመ ቃል ግጥሞች

1. የተስፋውን ቃል የጠበቁ

በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቁ

የታቦት ነውና አምላካቸው

ትንሳኤ በእሁድ ሊያሳየቸው
ሶስት ጊዜ ራሱ ተገለጠ
ኸሀሀ ኸሀሀ ሀሀ

2. ስርአተ ሙሴ
ተቀደሰ በስመ ስላሴ
ፅናፅል ፅናፅል ፅናፅል ፅናፅል
የአሮን ባህል

3. ኸሀ ኸ ኸሀሀ ሀሀሀ
ሰው ቃሉን ጠብቆ ለእምነቱ ከበቃ
ማለዳ ያያታል በለሲቱ ደርቃል

ስለ ስግደት የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. ተዋህዶ ሀይማኖት እመቤቴ ናት
ተዋህዶ ሀይማኖት እመቤቴ ናት
እንስገድላት እንስገድላት እንስገድ እንስገድ
በእውነት ለአምላክ እናት

ስለ እምነት የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. እናምናለን በአብ እናምናለን በወልድ በወለድ
እናምናለን በአብ እናምናለን በወልድ በወለድ
እናምናለን እናምናለን እናምናለን እናምናለን
እናምናለን በመንፈስ ቅዱስ

ስለ ፀሎት የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. ስርአተ ፀሎት ማዬ በፀሎት
ስርአተ ፀሎት ማዬ በፀሎት
ደመና መንኮራኩሩ ለመድሀኒያለም
ደመና መንኮራኩሩ ለመድሀኒያለም

2. እህሀ ኸሀ ኸሀሀ
እረሳሁ ጌታ ህግህን
ቀጥፌ በላሁ በለሱን
ከገነት ቤቴ ተሰደድኩኝ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ከፍቅርህ እጅ ተለየሁኝ

3. ኸሀ ኸሀ ኸ ሀሀ

 ለኔም ከነቢያት አንዱ ደረሰኝ

 እንባ አቁምም ብለው አይኔ እንቢ አለኝ

4. ኸኸኸ ኸሀሀ ሀሀሀ

 ድንጋዩን ጨብጠው አይሁድ ሲወግሩህ

 ትፀልይ ነበር ለእነርሱ ተጨንቀህ

 በእየሱስ ክርስቶስ አለምን ሊያድን

ስለ መክሊት የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. ላለው ይጨመራል ይላል የጌታ ቃል

 ሰምቶ ማይሰማ የእጁን ይነጠቃል

ስለ ፆም የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. ኸሀ ኸ ኸሀሀ

 አወይ ሰው ግብዙ ስጋ እየተመኘ

 የነፍሱ ጎዳና ተሸሮ ተገኘ

ስለ ሚካኤል የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. እልል እልል ደስ ይበለን

 እልል ደስ ይበለን

 እልል ብላችሁ ተቀበሉን

 ይዘን መጥተናል ሚካኤልን

2. እረሀብ እና ቸነፈር

 በቀትር ሀሩር በሌት ቁር

 ላጋጠማቸው ብዙ ጉዳት

 ቅዱስ ሚካኤል ነው እረዳት

3. እሰይ ስለቴ ሰመረ

 እሰይ ስለቴ ሰመረ

 ለሚካኤል ነግሬው ነበረ

## ስለ ሞት የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. ለኔ እየመሰለኝ ቤቴን የሰራሁ
   ባላውቀው ነው እንጂ ለካ እፈርሳለሁ

2. ኸሀ ሀሀ ኸሀ ኸሀሀ
   ትልቅ አትመኙ ፎቁን አያያችሁ
   መሄዳችሁ ላይቀር ካፈሩ ቤታችሁ

3. ኸሀ ኸሀ ኸ እሀ
   አሞራ አንኳን አዝኖ በወንድሜ ሞት
   ዋ ብሎ በረረ አንጀቱን በልቶት

4. በውጭ የሚያምር ውበታችሁ
   ሀጢያት የሞላ በውስጣችሁ
   ልባችሁ ቢመኝ ትልቅ ቦታ
   ወየው ለእናንተ ከጌታ

5. አንዱ መነኩሴ አንዱ ቄስ
   ሶስተኛ በአባሰል
   ይንገሩኝ እና ልረዳው
   ይሄ ሰሞን የማን ነው

6. ኸሀሀ ኸሀ ኸሀ
   ክበር ተመስገን ጌታችን
   ውዱን ሲልከው
   በራሱ እንዳለው

## ስለ መከራ የተገጠሙ ቃልግጥሞች

1. ስለቃሉ የተጠሉ የተጨነቁ
   እነርሱ መንግስቱን ይወርሳሉ

2. በጠባቧ በር ያለፉት
   ገቡ ወደ እግዚአብሄር መንግስት
   ኸሀሀ ኸሀ ሀሀሀ

3. ኸሀ ኸ ኸሀ ኸሀሀ

በስጋ ዛለች ተንከራታ

እያለላት ልጇ የአለም ሁሉ ጌታ

ስለ ተአምራት የተገጠመ ቃል ግጥም

1. ኸሀ ኸ ኸሀሀ

ጌታ ያደረገው መቼም አለ አይባል

አምስት ለአምስት ሺ. መግቦ ያጠግባል

ስለ ትንሳኤ የተገጠመ ቃል ግጥም

1. የዕድቅን ጎዳና ለአለም አስተምሮ

ሄደ ወደአባቱ መቃብሩን ሰብሮ

ስለ መማር የተገጠመ ቃል ግጥም

1. መች ያቅተን ነበር ፊደልን መቁጠር

እጣችን ሆኖ እንጂ ቀርተን ሳንማር

2. ዳዊት የማይደግም ፊደል ያልቆጠረ

መውደቂያው የት ይሆን ቀድሞ ያልተማረ

ስለ ነፍስ መኖር የተገጠመ ቃል ግጥም

1. ኸሀ ኸሀ ኸሀሀ ሀሀ

እስኪ. ሀቁን እወቅ አለው ጠይቀህ

ካፊር የሚገባው ስጋ ነው ነፍስህ

2. ሰው ሁሉ ሲሰራ ሲያሳምር ቤቱን

የእኔይቱ ጎጆማ ቀረች በማእዘን

## በአዝማሪ ምግብ የተከወኑ ቃል ግጥሞች

### የእንጉርጉሮ ቃል ግጥሞች

1. ምን አይነት ዘመን ነው የተገላቢጦ
   ብልሁ ተሰደበ ደንቆሮ ተቀምጦ።

2. ባቲ እና አንቺ ሆዬ ትዝታን ቃኝተን
   ኖሮአችን ባህር ዳር እዝራ ነው ስማችን።

3. የማይጨው ወረዳ እናኳን አወቀሽ
   አንቺ ማሲንቋችን እንደምን አለሽ
   ይህ ሁላ ሰው ታጫውቻለሽ

4. አዝማሪ ይሉኛል አዝማሪስ እሳቸው
   የተበላሸውን ስላደስኩላቸው

5. ማሲንቆ እና ክራር በእኛ ያምራል እጅ
   አስልጥኖ መስጠት ለመደብኝ እንጂ

### የፍቅር ቃል ግጥሞች

1. እንትና እንትና ብዬ እንትናን አላገኝም
   እኔ ሞቴን እንጂ ሌላ አልመኝ

2. ወደ አንተ ስመጣ ሶስት ጊዜ ወደቅሁ
   ለነፍሴ ቢሆንም ኸረ እንዴት በፀደቅሁ

3. አበደች ይሉኛል የት አለ ማበዴ
   ከድፍን ሀገር እኔ አንተን መውደዴ

4. ጎጃም በግራ ነው ቢቸና በቀኝ
   ምን አግኝቶት ይሆን ምነው ቀረብኝ

5. መኪና ይሄዳል ሹፌር ሲነዳው
   ተዋዶ መለየት እንዴት መከራ ነው

6. ምን አለች የሺ ምን አለች
   እንትናን ለሰው አልሰጥም አለች

7. ብፈልግ ባስፈልግ አጣሁሽ

   የኔማ አስካሌ እንደምን አለሽ

8. ከበሮውን ምቱት ደመቅ አድርጉት

   እኛ በምንወደው በደስዬ ሞት

9. አንቺ አበባ አበባ የኔ አበባ

   አንቺ ውብ አበባ የኔ አበባ

   የኔ ውብ አበባ የኔ አበባ

   ነይማ ነይማ

10. አይኗ በላይ በላይ

   ጥርሷ በላይ በላይ

   ኬላ ላይ ያለሽው አስካልዬ በላይ

11. ትላንትና ማታ ኸረ እናናዬ

   ኬላ ላይ ሁነሽ ኸረ እናናዬ

   ኸረ እንደምን ልሁን ደህው ወንድምሽ

12. እንዲያው እማምዬ እንዲያው እማምዬ

   እንዲያው እመጣለሁ አስካልየን ብዬ

13. የኔ ውድ በደሌ እንደምን አለህ

   በባህርዳር ከተማ ከዚህ ላይ ሁነህ

   አንተን የመሰለ ሞተርም ገዝተህ

   እንዲያው ተቀምጨ እኔ ላጫውትህ

14. አለም አለም ሲመጣ ነው እንጂ

   ሲቀርስ አልወድም

15. ሆድ አያልማ ሸበልማ ሸበልማ

   ሆድ አያልማ ሸበልማ ሸበልማ

   ኸረ ዙምአለም ኸረ ዙም አለም

   ወይን አበባዬ ወለላዬ ወለላዬ

   ሁዴ አያሌው ሸበላው ሸበላው

   ኸረ ገዳሜ ገዳሜ ኸረ ገዳሜ ገዳሜ

ዙማለም ዙማለም እንዳች ያለ የለም

16. ጎጃም እና ጎንደር ማዶ ለማዶ ነው
ፍቅር ያለቦታው አባጨጓሬ ነው

17. አገሯ ያውና ይታያል እና
አገሯ ያውና ይታያል እና
አገሯ ላይ ሳንደርስ እንዴት ሊነጋ

18. አይናማው ገዳዬ አሀ ገዳዬ
ማምዬው ማምዬው ሀመምተኝት
ቆንጂት እኔ አልሆንልኝ አለ ልጣራ ነው ሌሊት

19. የሰው የለው ሞኝ የሰው የለው ሞኝ
በተወለደበት ባሀገሩ ሲገኝ የሰው የለው ሞኝ
ዙማለም ዙማለም እንደአንቺ ያለ የለም

20. ኸረ ሙናሙኔ ኸረሙናሙኔ አንተን ማመኔ
ኸረ ሙናሙኔ ኸረ ሙናሙኔ አንቺን ማመኔ
ኸረ ምንም አንቺን አላምንም
ሞንሚናዬ ሞንሚናዬ

የሙገሳ ቃል ግጥሞች

1. የጎፈሬን ነገር አየነው መላ ነው
ሀገር የሚመራ እረስ በራ ነው

2. ጫቱን ቅሜ ቅሜ ሲያመረቅነኝ
የበደሌ ሞተር የኔ መሰለኝ

3. ለመንዳት ሌላም ይነዳታል
ምስግዬማ ሲነዳት ነፍስ ይዘራበታል

4. ገላውን አይነካውም ካኪ.
የኔማ በደሌ አስመጭና ላኪ.

5. ማን ይነካኛል ብዬ ይሳሳል ገላዬ
እንትናዬ ካለልኝ ለኔስ ከኋላዬ

6. እስኪ ጠጡ ጮማውን ቁረጡ
የኔማ እንትናዬ አመለ መልካሙ

7. እስቲ ንኩት እና ቀጥ ይበል ደሙ
የነ ሽሜ አካሉ የንጉስ ወንድሙ

8. የሙሽራው ማማር የሚዜው ውበት
ልቤን አደረገው ዘርዛራ ወንፊት

9. በስለት ያረዱት አይንፈራገጥም
የደስዬስ ምላስ አይወላብድም

10. እስቲ በእጃችሁም አጨብጭቡበት
እኛ በምንወደው በደስዬ ሞት

11. የኔማ እንትናየ የኔማ ባይሆን
እሞት ነበር ታምሜ የማልድን

12. ስጠይቅ ሳስጠይቅ ኬላ ላይ ሁነሽ
የኔ ውድ አስካሌ አንጀቴን በላሽ

13. አስካል ማር ኬላ ላይ ሁነሽ
እኔ ወንድምሽ ብፈልግ አጣሁሽ

14. ሀብታሙም ደሀውም ሲመኝሽ
ከዚህ ተቀምጬ ደሀው ወንድምሽ

15. ሀብታሙ ዳኛውም ሲመኝሽ
እኔ ምልሁን ደሀው ወንድምሽ

16. ማኛ ነው ማኛ ነው ጎጀምስ ማኛ ነው
አስካል አበባ ነው

17. አንቺ ባህርዳር ጎድጓዳዋ መሬት
ታበቂያለሽ አሉ ሽጋ እንደ ሰንበሌጥ

18. እመቤቴ ማሪያም እመቤቴ ሆይ
አንቺን ያመነ ሰው ይጎልበታል ወይ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

19.የኔማ የእንትናየ የነእንትና ወንድም
እንበለው ነው እንጂ እንሸሽ አይወድም

20.አውራጃ ቀበሌን ሳይፈራ
እንደኮራ ገባ እንደ ተንጠራራ

21.የኔማ እንትናዬ በጣም ታድለሻል
የተማረ ሙሁር እንትናዬን አግኝተሻል

22.ለስለት ያሉት አይፈራገጥም
እንትናዬ የያዘው አይገላበጥም

23. የኔማ እንትናዬ የጎበዝ ልጅ
የተማረ ሙሁር ያስደስታል እንጂ

24.የምስግዬ ወንድም የእንትናዬ ልጅ
የሚበላው ጮማ የሚጠጣው ጠጅ

25.እንትናዬ የትላንቱ ልጅ
መንገድ ያስተማረው ምስግዬ ነው እንጅ

26.የኔ አለም የኔ አለም የኔ አለም
የሚመስልህ የለህም

27.የኔማ የእንትናዬ ወንድም
በፀባይ ነው እንጂ ሲነኩት አይወዱም

28.ከኛ አገር አለ ቢራ
ሙያችን ያሳየ ያኮራ

29.ጎረድ ጎረድ ያለው እንደ ሰንበሌጣ
እኛን ደስ ይለናል ደስዬ ሲመጣ

30.ኸረ እርዬው ኸረ እርዬው
በስለት ያረዱት ኸረ እርዬው
አይፈራገጥም ኸረ እርዬው
የደስዬስ አፍ ኸረ እርዬው
አይገላበጥም

31.ቢያምኑህ አይደል ወይ ባይጠረጥሩህ

ፍቃዱን በሙሉ ለአንተ የሰጡህ

32.አሸበል ገዳዬ አሀ ገዳዬአሸበል ገዳዬ አሀ ገዳዬ

አይናማው ገዳዬ አሀ ገዳዬ

አይናማው ገዳዬ አሀ ገዳዬ

ኸረ ጎጃም ጎጃም አሀ ገዳዬ

ጎጃም ወለላው አሀ ገዳዬ

ጎጃም ወለላው አሀ ገዳዬ

ዳማይ ዳማይ ዳማይ ዳማይ

ስለ ሀገር የተገጠመ ቃል ግጥም

1. ምንም ደሀ ብሆን የማበላው ባጣ

ምንም ደሀ ብሆን የማበላው ባጣ

እንግዳ እወዳለሁ ከቡርቧክስ የመጣ

2. አማሪካ ጀርመን ፈረንሳይ ቢሆን

ኢትዮጵያን የሚያስንቅ በአለም ላይ የለም

3. ህዝቡ ሰራተኛ መሪዉ ጥበበኛ

ኢትዮጵያ ትሆናለች ያለም መገናኛ

4. ከሰው ሀገር ሄጀ ከሰው ሀገር ሄጀ

ጮማ ከምበላ ይሻለኛል እኔ አባይ እና ጣና

5. ምስግዬ የነእንትና ወንድም

እኔን ደስ ይለኛል ዘልዘልማ ግድም

6. ቢመቻት ነው እንጂ በሀርዳር ማደሯ

እንዲያ ባለ ጊዜ ገርጂ ነው ሀገሯ

7. ጋዜጣው በሙሉ የሚገኝብሽ

ገርጂ እና ቦሌ እንደምን አለሽ

8. ደርሰንም ነበርነ ካሳንችስ ባቢስ ላይ

ቦሌ ላይ ነበርነ ማዞሪያ ሀያ ሁለት መገናኛ ላይ

ለገሀር ነበርነ ሲገፉ ሲገፉ ወረብ ላይ ጣሉን

9. ማርቆስ በግራ ነው ቢቸና በቀኝ

የእናት ሀገር ልጅ መጣ መሰለኝ

10.ጠጅ ሞላ በብርሌ

ከተወለዱ አይቀር ጎንደር አባጃሌ

11.አይናማው ገዳዬ አሀ ገዳዬ

አይናማው አይናማው

ጎጃም ወለላው ጎጃም ወለላው

12.አሸበል ገዳዬ አሀ ገዳዬ

ለምን ምንጃር አይሆን አሀ ገዳዬ አይበላ እሸቱ

ይምጣ የጎጃም ልጅ የቡሬ ዳሞቱ

13.ደሞ ነይ ጎንደሬ ደሞ ነይ ጎንደሬ

እንዴት ነሽ ሀገሬ

14.እንዴት ነሽ ጎንደሬ እንዴት ነሽ ጎንደሬ

ትዝ አለኝ ሀገሬ

15.አዲስ አበባ አምባ መቼም አበባ ነው

ባህር ዳር እንዴት ነው

ውጭ እያኮራ ነው

16.ከሰው ሀገር ስንዴ ከተበጠረው

ይሻላል የሀገር ልጅ ከነገለባው

17.ውጭ ሀገር ቢሄድ ጭብጥ ጤፍ አይገኝ

ሀገሬ ኢትዮጵያ ካንቺ ውጭስ አያድርገኝ

18.ኸረ ባቲ ባቲ ባቲ ከተማው

አለ የሚቆጠር ድል አድርገው ሲገቡ

19.አበባዬ አበባዬ ነይ ሳዱላዬ

አበባዬ አበባዬ ነይ ከተማዬ

20.እንዴት ነሽ ኢትዮጵያ የታጠርሽው በአጋም

እሪ ይላል እንጂ ምስለኔ አይዋጋም

21.በሰው እንበል ለቁልቁለቱ

ወደ ገጠርና ይቀራል ከብቱ

22.እንዲህ ያለ ቦታ ገጠር ለገጠር

የከተማ ጥሪ አይደለም ወይ ቀርቶ

23.ሆይ መላ ነሽ አሉ ሆይ መላ

እንዴው መላ መላ

እመጣለሁ ጎጃም ሆይ መላ

እንዴው መላ መላ

አድራለሁ ቢቸና ሆይ መላ

24.ሰውነቱ አንድ ነው

ጨርቁም ምናምን ነው

ሀሞቱም ኩሩ ነው

ሰባራው ይቅርብኝ ዘሬ ጎንደሬ ነው

25.የሰው የለው ሞኝ የሰው የለው ሞኝ

ማን ይሆናል ሞኝ በተወለደበት በሀገሩ ሲገኝ

ማን ይሆናል ሞኝ

26.ኸረ ጎጃም ጎጃም ጎጃም ወለላው

ከቆሎ ከጥሬ የሰው እንጀራው

ስለ ገጠሩ ኑሮ የተገጠመቃል ግጥም

1. በጣም ደስ ይለኛል የአርሶ አደሩ ኑሮ

ወተቱ ከማጀት እሸቱ ከጓሮ

የእንጉርጉሮ ቃል ግጥም

1. በሀምሌ በነሀሴ እንዲያ ስወትት

እንዴት በመስከረም በተስፋ ልሙት

2. ይበላል ይጠጣል ጠጅ

ማሩ አያሌው ጉድጓድ ላይ ነው እንጂ

3. እሸት እሸት አድርጎ ይመጠጣል ሎሚ

ፀባዩ ይገርማል ሚች እና ከራሚ

4. ላሚቱ ና ጥጃው አብረው እየዋሉ
አሁን የት ይገኛል ወተት ወተት ቢሉ

5. ካሉም ተሸምቶ ይበላል እንጀራ
እንደምን ነው ጥጋብ የሞት ባልጀራ

6. ተስፋዬ አንተ ራስ በራ
ዳር ዳሩን መንጥረህ መሀሉን ጤፍ ዝራ
የደኸየ ሁሉ ሸምቶ እንዲበላ

7. እየቸገረው ነው ሰው ሁሉ ብልሀቱን
ወዳጅ የሚያደርገው ጠላቱን

8. የኔ ውድ በደሌ አንት ወደል አንት ወደል
ደሞ እንደለመድከው ሰበብ ውስጥ ይግደል

ስለ አዝማሪዋ የተገጠመ ቃል ግጥም

1. አይኔም ደነዘዘ እግሮቸም ፈዘዙ
ምግብ እና ቢራ ከዚህ ቤት ካልጠፉ

2. ድፍን አለማዊ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ አለም ያወቃት
ያውራባዋ ዘፋኝ ምግቤ ይህች ናት

3. እንዲሁ እንዳማረባት ጎንደር ያደገች
የአውራባዋ ዘፋኝ ምግቤ ግድ የለው ይህቺ ናች

ምክራዊ ቃል ግጥሞች

1. የኔማ እንትናዬ አትበላም በርበሬ
ምንም አይጠቅምም ጣፋጭ እና ወሬ

2. ሲነግዱ አትነግድና ሲማሩ አትማርና
ሰው ውሎብኛል በል ከጥላው ሁንና

3. ቶሎ ቶሎ ብሎ እራስን መቻል ነው
ከዘመድ መጠጋት በኂላ ጠብ ነው

ስለ ባህል የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. አለው አለውና አለው አለውና

ባህላችን ፀና

2. ቅርብ ለቅርብ ነው ጎጃም እና ጎንደር
   በጣም ደስ ይለናል ባህሉ ሲከበር

3. እንዲህ ያለ ጨዋታ ባህላዊው
   የሀገር ልጅ ተቀምጦ የውጭው

4. ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ
   ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ
   እንዲህ ነው ባሀሉ ጎንደር አባ ጃሌ

5. አለው አለው እና አለው አለው እና
   በመሀበር ፀና

ስለ ሰርግ የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. አለም አለም አለም ሶስት ነው
   አለም አራት ነው
   አንድም ክርስትና አንድም ተድሮ ነው

2. ለእናትሽ ደስ ይበላቸው
   ላባትሽ ደስ ይበላቸው
   ኦሆሆ እቴ ልጃቸው

3. አለገና አለገና አለገና ገና
   ገና ገና አለ ገና
   የትንሿም አለ ገና
   አለገና ገና ገና ገና

4. አለሚ ዛሬ ነው ዛሬ
   አለሚ ዛሬ ነው ዛሬ
   ኦሆሆ እቴ ሽንኮሬ

5. ምን አለ ደሴ ምን አለ
   የሺዬን ለሰው የሺዬን ለሰው አልሰጥም አለ

6. ምን አለ ደሴ ምን አለ
   ለሰው ሀገሬ

7. አሸሙናና አሸሙናና

መሽራው ናና

ሰርገኛው ናና

8. ያውና ይታያል እና

ያውና ሙሽራው ናና

9. ሙሽሪት ሙሽራው እናኳን ድስ ያላችሁ

ያብርሀም የሳራ ይሁን ጋብቻችሁ

10. ኸረ ሚዜው እህምለው ኸረ ሚዜው እህምለው

ፊዛዛ ነው እህምለው

11. ጨሰ አቧራው ጨሰ

ጨሰ አቧራው ጨሰ

12. ሁለቱም ተገኙ እህ ከናት ካባታቸው እህ

ትዳር መሰረቱ እህ አንድ ሆነ ቤታቸው እህ

ሙሽራዬ ሙሽራዬ የወይን አበባዬ

13. አንቺ ውብ አበባ የኔ አበባ

አንቺ ውብ አበባ የኔ አበባ

ኸረ ውብ አበባ የኔ አበባ

አንቺ ውብ አበባ የኔ አበባ

አንቺ ውብ አበባ የኔ አበባ

14. ኸረ ሚዜው እህምለው

ገጠሬ ነው እህምለው

15. እርግጥ እርግጥ አድርገው በእግርህ

መኪና የለህም ሙሽራ ነህ

16. አሸ ወይና አሸ ወይና

አሸ ወይና ነሽ ወይ

ትመጫለሽ ወይ

17. ሆይ መላ ነሽ አሉ ሆይ መላ

ሆይ መላ ነሽ አሉ ሆይ መላ

እዬዬው ደሜ እዬዬው ደሜ

ተይዶ ተይ ደሜ ተይደሜ ተይደሜ

ገዳዬ ጋዳዬ ገዳዬ ገዳዬ

ኸረ ገዳሙ ገዳሙ ጋዳሙ

ኸረ ገዳሙ ገዳሙ ገዳሙ

አንቺ ሆዬ ሽሙንሙን የሚለው

18. ይትባረክ እንደ አብርሀም

ይትባረክ እንደ አብርሀም

ኸሀ ዘልአለም ዘለአለም ዘለአለም ዘለአለም

ይትባረክ እንደ አብርሀም

19. የቄሱ ልጅ እህምለው ደብተራው

ለደንቡ ነው እህምለው

20. ያውና ይታያልእና

ያውና ይታያል እና

ያውና ሙሽራው ናና

ያውና ሚዜው ቶሎና

አገዳይ ደሞ አገዳይ ደሞ

አገዳይዶ አገዳይ ደሞ

21. አይፈራም ጋም አይፈራም

አይፈራም ጋም አይፈራም

ወገቧ ልክ አይሰራም

ያውና ሙሽራው ናና

ያውና ሚዜው ቶሎ ና

22. አባው ጃልዬ እያሆ አባው ጃልዬ እያሆ

ግሼ በል እያሆ ግሼ በል እያሆ

ግሼ በል እያሆ ግሼ በል እያሆ

23. አለሙ ዘሬ ነው ዛሬ አለሙ ዛሬ ነው ዛሬ

ኦሆሆ እቴ ሙሽሬ

## ትችታዊ ቃል ግጥሞች

1. አንድ ሁለት በጥፊ አንድም በእርግጫ
   ኽረ ተው በደሌ ነበረ ልማዳቸው
   ህጉ ጠበቀና ፈሰሰ አንጀታቸው

2. ይወሰድ እና እያሆ እግረ ሰፋፊ እያሆ
   ይዞ ይማታል እያሆ በጫማ ጥፊ እያሆ

3. ያገባም አገባ ያላገባም አጨ
   አንዳንዱ ቀረ እንጅ ፂሙን እየላጨ

4. ይወሰድ እና ጉልበት ጉልበቱ
   ጋን ይሸከማል ከነ ድፍድፉ

5. ኽረ ሚዜው ሚዜው ፈዟል
   ለሙሽራው እጣን መች ይዟል

6. ኽረ ሚዜው በለው በለው
   ወደላ ነው

7. ሀይሎጋ ከበሮውን ምቱት እያስማማችሁ
   እነማን ነበሩ ታስኙናላችሁ

8. ኽረ ጃሌው እህምለው
   ወደላ ነው እህምለው

9. ያገባም አገባ ያላገባም ታጨ
   ሚዜው ብቻ ቀረ እየተበሳጨ

## የጀግነት ቃል ግጥም

1. ሀይሎጋ ሀይሎጋዬ ሆ ሀይሎጋ ሀይሎጋ ሆ
   ሀይሎጋ ተዋጋ ብዬ ሀይሎጋ ሀይሎጋዬ ሆ
   ሀይሎጋ ብሰጠው ጋሻ ሀይሎጋ ሀይሎጋዬ
   ሀይሎጋ ለእናቱ ሰጣት ሀይሎጋ ሀይሎጋዬ ሆ

2. ሀይሎጋ ሀይሎጋዬ ሀይሎጋ ሀይሎጋ ሆ
   ሀይሎጋ ከበሮውን ምቱት ሀይሎጋ ሀይሎጋዬ ሆ
   ሀይሎጋ እነማን ነበሩ ሀይሎጋ ሀይሎጋዬ ሆ

ሀይሎሎጋ ታሰኙናላችሁ ሀይሎጋ ሀይሎጋዬ ሆ

3. ኸረ ጎበዝ እህምለው ኸረ ወንዱ እህምለው
   በለው በለው እህምለው

4. ገጠሬው እህምለው እርገጠው እህምለው
   እንደ ዳንኪራ እህምለው እርገጠው እህምለው

## በአዝማሪ ማሾ የተከወኑ ቃል ግጥሞች

### ስለ አባይ የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

1. አባይ ጠመዝማዛ ሁሌ መንገደኛ
   ያለፈው ይበቃል ተመለስ ወደ እኛ።

2. ውጭ መሄድ እንግዲህ ለምናችን
   ዱባይም መሄድ እንግዲህ ለምናችን
   ሱዳንም መሄድ እንግዲህ ለምናችን
   አባይን ገድበን እናለማለን።

### የሙገሳ ቃል ግጥሞች

1. የኔማ እንትናዬ የትልቅ ሰው ልጅ
   ተከትላ አትሄድም አስከትላ እንጅ።

2. የኔማ እንትናዬ የምርጤ የከሌ ልጅ
   ተከትላ አትሄድም አስከትላ ነው እንጅ።

3. ለቅላት ለቅላት በርበሬ ይበልጣል
   ለቅላት ለቅላት በርበሬ ይበልጣል
   የእንትናዬ ኩራት ጉድ መቼ ይቻላል

4. አንደበተ መልካም የተደላደለ
   አጥተነው ቢሆን ይቆጨን ነበረ።

5. የውጩ ካምፓኒ እኛ ለምናችን
   የውጩ ድርጅት እኛ ለምናችን
   የኔማ እንትናዬ የጀርባ አጥንታችን።

6. ጌጥ ነው እዚህ አይቀመጥ
   እንትና ይበቃል ሌሊቱ እንዲያጌጥ።

7. ሁለት ደና ተኳሽ የሚሆነውን
   ሁለት ደና ጀግና የሚሆነውን
   አንድ አድርገው ፈጠሩት ወንድሜ ሆዴን።

8. ሰው ሁላ ሞኝ ነው ለቁመት ይሳሳል
   ወንድሜ እረጅም ነው ካሰበው ይደርሳል።

9. ዝቅ በል ምድር ነው ቀና በል ሰማይ
   ከወንድሜ ወዲያ ሰው ይገኛል ወይ።

10. የኔማ እንትናዬ አትጨናነቂ
    የኔማ እንትናዬ አትጨናነቂ
    ፓሪስም አለልሽ ችግር አላቃቂ።

11. የራሱን እንጂ የሰውን አይነካ
    ወንድማችን መጣ አሪጅናል አፍሪካ።

12. አይገኝም እንጂ ሲገኝማ እንዴታ
    አይገኝም እንጂ ሲገኝማ እንዴታ
    ከሚወዱት ጋራ በአንድ አብሮ ጨዋታ።

13. ከመልከ መልከኛ ተወራርጃለሁ
    የኔማ እንትናዬ ዝቅ በል ብያለሁ

14. በባህር ዳር አድርጎ በእጁ የኮራው
    እንትናዬ አካሌ ደሞዜ እንዴት ነው

15. የባላገር ሱሪ ያልቃል ከጉልበቱ
    እቴ የሀገሬ ልጅ ተባቱ ተባቱ

16. ሆዴ አያል አለም ማር ላለም ማራ አላለም
    አያል ሲገለኝ ሹርቤዋ ገላገለኝ

17. የኔማ የእነትናዬ ወንድም
    እንበለው ነው እንጀ የሚሸሽ አይወድም

## የፍቅር ቃል ግጥም

1. አይኑ ትላልቅ ነው እጅግ አያስዋሽም
   ትላልቅ ነው እጅግ አያስዋሽም
   ከተወረወረ ሳይጠብስ አያመሽም።

2. እቴ እንደምን አለህ እኔማ ታምሜ
ለምን ትመጣለህ ሌሊት ሌሊት በህልሜ

3. እንኳን ያንተ ፍቅር ተጨምሮበት
እንዲውም ይሞቃል ሰኔ እና ግንቦት

4. እንዳልመጣ ፈራሁ እንዳልቀር ጨነቀኝ
ኸረ ተው ሙሽራው

5. ኸረ ሙኔ ኸረ ሙናሙኔ አንተን ማመኔ
ኸረ ሙኔ ኸረ ሙናሙኔ አንቺን ሚመኔ
ሞንሟኔ ሞንሟኔ አንተን ማመኔ
ሞንሟኔ ሞንሟኔ አንቺን ማመኔ
ኸረ ምንም ምንም አንተን አላምንም
ኸረ ምንም ምንም አንቺን አላምንም

ትችታዊ ቃል ግጥም

1. እዚህ አከባቢ በጣም ታምራላችሁ
ታዲያ ምን ያደርጋል ቦይ ፍሬንድ የላችሁ።

2. አቤት ወግና መልክና ቁመና(ወንዱ)
አሟልቶ ካልሰጠሽ ምን ዋጋ አለውና
የሚቻል ከሆነ ለህኪም ንገሪና
ካስተካከሉልሽ በቀዶ ጥገና

3. እኔ የምወድህ በቁመትህ ነው(ሴቷ)
እኔ የምወድህ በቁመናህ ነው
እኔ የምወድህ በማሲንቆ አያያዝህ ነው
ከወገብህ በታች ሁለመናህ የሞተ ነው።

4. አንቺ ምትወጅው የነንንጉርን ነው(ወንዱ)
አንቺ የምትወጅው የነታከለን ነው
እኔ ላንቺ ስልስ አህያ ልሆን ነው።

5. የዚህን ልጅ ነገር እኔ ነኝ የማውቀው
የዚህን ልጅ ታሪክ እኔ ነኝ የማውቀው
እንኳንስ ያህያ የሰውም የለው።

6. ግራንጣ ዘርታበት ጫካ አስመስላው
   መንጥሬው ገባሁ ከነጎፊሬው
   ልክ እንደ ሲጋራ በክብሪት ለኩሼው
   ፊቴን ዞሬ ተኛሁ አጭሼው አጭሼው።

7. ይሄ ሁሉ ጀግና ይሄ ሁሉ ቆንጆ ሳይለንት የሚመስለው አይ የሚመስለው
   ሌሊት በየአልጋው ላይ አቤት ሲያምር ያየው ሰው

8. የሀረር መንደር ልጅ የመሰለች ልጅ
   እንኳን ለጓደኛ ለማንም አይበጅ
   እንዲያው ደመቅ አድርጎ መኮምኮም ነው እንጅ

9. አለምየው ናና እህ
   አለምየው ናና እህ
   ትመጣ እንደሆነ ናልኝ ወደ ማታ
   ያሰራህልኝን ይዘህልኝ ያችን ነጭ ኩታ

10. ሆድ አያላለም ሆድ አያላለም
    ና ማር አላለም ና ማር አላለም

11. መርካቶ ገቢያ ይሸጣል ነጭ ላም
    ጨዋታ አይገባውም አንዳንዱ ግጭ ይላል

ስለ ሴቶች የተገጠመ ቃል ግጥም

1. የአምስት አመት እቅድ አልቀረም ተለፍቶ
   መጣ እየጨመረ የሴቶች ተሳትፎ።

2. ይሄ ተሳትፎአችን ይቀጥል ካላችሁ
   ሂሳቡንም ሼር ሼር እያረጋችሁ።

ስለ ሀገር የተገጠመ ቃል ግጥም

1. አገራችን ይደግ እንበርታ በእውነቱ
   የሰው ምን ያደርጋል ከኛ እያለ ሀብቱ

2. አገሬ ኢትዮጵያ የተባረከች
   አሁን ሰው አግኝታ በጣም አድጋለች

ስለ ፖለቲካ የተገጠመ ቃል ግጥም

1. ከእንግዲህ ወዲህ እንገት መድፋት ቀርቷል
   በኢህዴግ እኩልነት መጥቷል

የሰርግ ቃል ግጥሞች

1. አለሙ ዛሬ ነው ዛሬ
   እቴ ሙሽሬ

2. ሞንሟኔ ሞንሟኔ
   ሞላ በብርሌ

3. አሽ ወይና ኩቱ
   ነይ በመስኩቱ

4. መምሬ ግዝቱ
   ንፋግ እንዳይገባ ቶሎ ይገዝቱ

5. አገዳይ ደሞ አገዳይ ደሞ
   አይፈራም ጋም አይፈራም
   ወገቧ ልክ አይሰራም

6. ኸረ መሌ መሌ
   ኸረ መሌ መሌ
   ዋሸኝ እንዳመሌ

7. እንትናዬ ክለላዬ
   ሆድ ድማምዬ ሆድ ድማምዬ

8. የወይን አበባዬ የወይን አበባዬ
   የኔማ እንትናዬ የወይን አበባዬ
   እኛ ካላንተ ማን አለን

ስለ ሀገር የተገጠመ ቃል ግጥም

1. እንዴት ነሽ በሀር ዳር የኔ አበባ
   ያለሽው ከዳር የኔ አበባ

# አባሪ ሁለት

## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር


ሀ. የቁልፍ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | መኖሪያ | ስራ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ወርቁ ታዬ | ወ | 52 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | አዝማሪ | |
| 2 | ወ.ሮ ምግብ ግድ የለው | ወ | 50 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | አዝማሪ | |
| 3 | ወ.ሮ ማሾ ፋንታዬ | ወ | 49 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | አዝማሪ | |
| 4 | አቶ ትእዛዙ አስናቀዉ | ወ | 31 | 10+2 ቴክኒክ | ባህር ዳር | አዝማሪ | የእዝራ አዝማሪያን ማህበር ሀላፊ |

ለ. ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | መኖሪያ | ስራ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ስርግው ገላው | ወ | | ዶክትሬት ድግሪ | አዲስ አበባ | ሌክቸረ- | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ |
| 2 | አቶ አበባው | ወ | 26 | ድግሪ | ባህር ዳር | የሙዚቃ ባሙያ | ባህል እና ቱሪዝም |
| 3 | አቶ ስለሽ አስናቀው | ወ | 27 | 5 | ባህር ዳር | አዝማሪ | |
| 4 | አቶ ባየልኝ እንደሻዉ | ወ | 20 | 4 | ባህር ዳር | አዝማሪ | |
| 5 | አቶ ወርቁ ታዬ | ወ | 50 | ማስተርስ ድግሪ | ባህር ዳር | አስተማሪ | |
| 6 | ወ/ሮ ወርቅነሽ ዘለቀ | ሴ | 36 | 10ኛ ክፍል | ባህር ዳር | የግል ስራ | |
| 7 | ወ/ሮ ሰተይ ክንፈ | ሴ | 48 | ቲታይ | ባህር ዳር | መምህር | |
| 8 | አቶ ዳንኤል ከፈላ | ወ | 24 | ድግሪ | ባህር ዳር | ጋዜጠኛ | አለም አቀፍ ህዝብ ግንኙነት |
| 9 | አቶ ወንደሰን አዳሙ | ወ | | ማስተርስ ድግሪ | አዲስ አበባ | ሌክቸረር | አዲስ አበባ ዩኒቨር ስቲ |

የኢትዮጵያና የአማራ ክልል ካርታ




ምንጭ፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ


አባሪ አራት

የፎቶ ግራፎች ዝርዝር

ቁልፍ እና ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች ፎቶ ግራፍ በከፊል



ወ.ሮ ወርቅነሽ ዘለቀ



አዝማሪ ወርቁ ታዬ



አዝማሪ ምግብ ግድ የለው



አዝማሪ ወርቁ ታዬ እና አዝማሪ ምግብ ግድየለው በዳሞት ባህል ምሽት ቤት ሲከውኑ



አዝማሪ ወርቁ ታዬ እና አዝማሪ ምግብ ግድ የለው



አዝማሪ ምግብ ግድየለው እና የአዝማሪ ማህበር ሀላፊ የሆነው አቶ ትእዛዙ እስናቀው



እዝማሪ ምግብ ግዮ የለጡ



አዝማሪ ምግብ ግድ የለው በክወና ወቅት



የዳሞት ባህል ምሽት ቤት አውዳዊ ክዋኔ



አዝማሪ ምግባ ግድ የለው በባህል ምሽት ቤት ውስጥ



አዝማሪ ምግብ ግድ የለው እና አዝማሪ ወርቁ ታዬ በዳሞት ምሽት ቤት ክዋና ወቅት



የአዝማሪ ወርቁ እና የአዝማሪ ምግብ ግድ የለው ክዋኔ እና አውዳዊ ሁኔታ



አዝማሪ ማሾ ፋንታዬ



አዝማሪ ማሾ ፋንታዬ



የጊዮርጊስ ሰባሩ ጥምቀት አውዳዊ ክብረ በአል



አዝማሪ ወርቁ እና ሌሎች አዝማሪዎች በጊዮርጊስ ሰባሩ የጥምቀት ክዋና ላይ



አዝማሪ ወርቁ እና ሌሎች አዝማሪዎች በጊዮርጊስ ሰባሩ የጥምቀት እውዳዊ  ክዋኔ

# 5. አዝማሪነት

## 5.1. ነባራዊ ሁኔታ

የአዝማሪነት የሥራ ዘርፍ በግል ወይም በቡድን በመደራጀት ገቢ ለማግኘት በራሳቸው ወይም በግል ባህላዊ ምሽት ቤቶች ባህላዊ ጨዋታዎችን የሚያቀርብ ነው። በአማራ ክልል በአዝማሪነት የሥራ ዘርፍ በርካታ ሰዎች እየተንቀሳቀሱ እንዳሉ ይታወቃል። ሆኖም ግን ይህ ጥናት በክልሉ እንደሚንቀሳቀሱ ያረጋገጣቸው 322 አዝማሪዎች ሲሆኑ ከነኝህ ውስጥ 240ዎቹ በማህበራት ተደራጅተው እንደሚገኙ በጥናቱ ለማጋገጥ ተችሏል። ቀሪዎቹ በተናጠልና በቡድን ተለያዩ የክልላችን ከተሞች እየተንቀሳቀሱ በሙያው የሚተዳደሩ /የሚኖሩ/ መሆናቸውን ጥናቱ አረጋግጧል።

ጥናቱ እንደሚያመለክተው ይህ ዘርፍ ለ322 ሰዎች የሥራ ዕድል የፈጠረና ለሚያስተዳድሯቸው የቤተሰብ አባላት የኑሮ መሠረት የሆነ የሙያ ዘርፍ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል። በሙያው በማህበር የተደራጁ ግለሰቦች ከሙያቸው ለመንግሥት የሚጠበቅባቸውን ግብር በመክፈል ላይ ይገኛሉ። አዝማሪነት በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና የመዝናኛ ዘርፍ እየሆነ የመጣ ሲሆን ለህብረተሰቡ ሃዘኑን ደስታውንና የባህል ትውፊቱን ለመድረክ የሚያቀርብበት እራሱንም የሚያይበት ተመራጭ የመዝናኛ አማራጭ እየሆነለት ይገኛል። የአዝማሪነት ሙያ ከቱሪዝም ገበያ ጋር እየተሳሰረ ወደ ክልላችን የሚመጡ ቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ የሚያራዝም እንደሆነ መረጃው /ጥናቱ/ ያመለክታል።

በክልላችን የሚገኙ አዝማሪዎች ሥራቸውን የሚያቀርቡበት የተለየ ምቹ ሁኔታዎች ለግለሰቦች ለባለሃብቶችና በራሳቸው በአዝማሪዎች እየተፈጠረላቸው ጥበባቸውን ለሠርግ ቤት ለባህል ምሽት ቤቶችና በተለይም በብሔራዊና ክልላዊ በዓላትና የቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች እያቀረቡ በሙያው ተጠቃሚ እንደሆኑ አመላክቷል። ዘርፉ የህብረተሰቡን ቱባ ባህል በመድረክ የሚያሳይ ጠራካራ የባህል ሙዚቃ ዘርፍ ሲሆን ይህን ጥንካሬ የሚያጉላ አደረጃጀቶች በመፍጠራቸው ህብረተሰባችን እያደነቀና ለጥበቡ ተደራሽ እየሆነ መምጣቱ ለሙያው ማደግ የራሱን አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል። ይሁንና አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች ዘርፉን ከመዝናኛነት በተቃራኒ በመፈረጅ ሙያውን የሚኮንኑ አላስፈላጊ አመለካከቶች በማራመድ ለእድገቱ እንቅፋት የሆኑ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን እንደሚያራምዱ ጥናቱ አመላክቷል።

## 5.2. የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት

በጎንደር ከተማ 80 አዝማሪዎች በማህበር ተደራጅተው እየሰሩ የሚገኙ ሲሆን የአዝማሪዎች ገቢ የተመሠረተው በሙያቸው በተደራጁበት ማህበር በከተማው ውስጥ በባህል የምሽት መዝናኛ ከተሰማሩ ቤቶች በመቀጠር ሲሆን ገቢያቸው በወር ደሞዝ ከ500 እስከ 3000 ብር ተቀጥረው እየሰሩ የሚገኙ ሲሆንም የተሻለ ጥቅም የሚያገኙት ከታዳሚው በሚያገኙት የሽልማት ጉርሻ እንደሆነ አዝማሪዎች ይገልፃሉ።

የጎንደር ከተማ በስፋት ለአዝማሪዎች የሥራ ዕድል ምቹ ሁኔታ የፈጠረ በመሆኑ አዝማሪዎች በተለያዩ የምሽት ቤቶች እየተዘዋወሩ በመስራትና የሰርግ ስነ ሥርአቶችን በማጀብና በተለይም ሃይማኖታዊና አገራዊ በዓላቶችን በማጀብ ተጠቃሚ እንደሆኑ በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል።

በተመሳሳይ በባህር ዳር ከተማ በአዝማሪነት ሙያ የተሰማሩ 150 አዝማሪዎች የሥራ ዕድል የፈጠረ መስክ እንደሆነ ጥናቱ ይጠቁማል። እነኚህ አዝማሪዎች ከምሽት ቤት ባለንብረቶት ጋር የገበያ ትስስር ፈጥረው በወር ከብር 800 ጀምሮ እየተከፈላቸው እየሰሩ እንደሚገኙ መረጃው ያመላክታል። በክልላችን ከተሞች ውስጥ በደሴ ከተማም አዝማሪዎች በሙያቸው ኑሮአቸውን መሥርተው እንደሚገኙ ከጥናቱ ለማወቅ ተችሏል። በደሴ ከተማ በዓላትና የሠርግ ሥነ ሥርዓቶች ላይ በመሥራት በወር ከ500 እስከ 1500 እያገኙ ተቀጥረው እንደሚሰሩና በብዛት የሚጠቀሙት ግን በሙያቸው እርካታ ከሚያገኘው ታዳሚ በሚያገኙት የማበረታቻ ሽልማት ገቢ መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል።

በላሊበላ ከተማ ለአዝማሪዎች ምቹ የሥራ ዕድል የሚፈጥር የቱሪስት ፍሰት ያለውና ህብረተሰቡ የኪነ ጥበብ ፍቅር የተላበሰ መሆኑ አካባቢው ለአዝማሪዎች ጥሩ የሆነ የሥራ ዕድል ለመፍጠር መቻሉን መረጃው ያመላክታል። አዝማሪዎች በሙያቸው ተደራጅተው በከተማው በሚገኙ የምሽት ቤቶችና የመዝናኛ ቦታዎች ለቱሪስቶች አገልግሎት በሚሰጡ ሆቴሎች ተቀጥረው በመስራት በወር የሚያገኙትን ደሞዝ፣ በሽልማት የሚያገኙትን ጉርሻ ለማህበራቸው ገቢ በማድረግና እኩል ለእያንዳንዳቸው በመክፈል በወር ከ2500 እስከ 3000 ብር ገቢ እንደሚያገኙ በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል።

አዝማሪዎች ሙያቸውን ህዝብን በማዝናናት የህዝብን ጥያቄና የጥበብ ፍቅር በሚያረካ መልኩ ማቅረባቸው ከህዝቡ በሚያገኙት የሽልማት ገንዘብ ከህዝብ ለሚሰጣቸው ሙያዊ እስተያየትና

# አባሪ ስድስት

## ሙዳዬ ቃላት

እደበድባለሁ - እለማመዳለሁ

የግጥሙ ወይራ ቃል - ድብቅ ትርጉም

ቢት -የሙዚቃው ምት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY